

ጎዳናን የሚያስናፍቁ ቤቶች

ገጽ 16



የአንጋፋው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል የማስፋፊያ ፕሮጀክት

ገጽ 14

አዲስ ዘመን
82ኛ ዓመት ቁጥር 154 የካቲት 4 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ



# በበጋ መስኖ ስንዴ

## . ከአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ተሸፍኗል

## . ከ52 ሚሊየን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይገኛል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ ዓመት የበጋ መስኖ ስንዴ አንድ ሚሊዮን 336 ሺህ 511 ሄክታር መሬት የተሸፈነ ሲሆን ከ52 ሚሊዮን በላይ ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ግብርና ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ግብርና ኢንስቲትዩት የመስኖ ስንዴ ፕሮጀክት አስተባባሪ ዶክተር ዳንኤል ሙለታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዘንድሮ ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ የበጋ መስኖ ስንዴ ፕሮጀክት በአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ታቅዶ አንድ ሚሊዮን 336 ሺህ 511 ሄክታር መሬት ላይ ዘር መዝራት ተችሏል። በዚህም ከ52 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

ከጥቅምት ወር አጋማሽ ጀምሮ በበጋ መስኖ ስንዴ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል ያሉት አስተባባሪው፤ የመሬት ዝግጅቱ መጠናቀቁንና በዘር መዝራት ሂደቱ ከአንድ ሚሊዮን 336 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን መቻሉን አብራርተዋል። ይህም ዕቅዱ ከመቶ ፐርሰንት በላይ መሳካቱን እንደሚያሳይ አክለዋል።

ዶክተር ዳንኤል እንደገለጹት፤ የበጋ መስኖ ስንዴ በክላስተር እየተዘራ ነው። ይህም የሚዘራው ዘር በአንድ ጊዜ እንዲዘራ ያደርጋል። ከዚህም ባለፈ የግብርና ሜካናይዜሽን፣ የማዳበሪያ አጠቃቀም እና የምርት አሰባሰብ ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚጠቅም ነው። አሁን እየተሠራ ያለው በመስኖ ስንዴ የተዘራውን ዘር መንከባከብ ነው።

ጥራት ያለው የበጋ መስኖ ስንዴ እንዲኖር እየተሠራ መሆኑንና ሌሎች የግብርና መሣሪያዎችን መጠቀም እንደተጀመረ የገለጹት አስተባባሪው፤ የግብርና ሚኒስቴር እና የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ሚኒስቴር ለልማቱ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

በበጋ መስኖ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ባበከር ሀሊፋ

# በክልሉ 64 ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፍን የተፋሰስ ሥራ ይከናወናል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- 64 ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፍን የተፋሰስ ሥራ ለመሥራት አቅዶ ወደ ሥራ መግባቱን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በተፋሰስ ሥራው 300 ሺህ ሕዝብ እንደሚሳተፍም ተገልጿል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበከር ሀሊፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የተፋሰስ ሥራ ለመሥራት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ ተገብቷል። በዚህም 64 ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፍን የተፋሰስ ሥራ ለመሥራት ታቅዷል።

የተፋሰስ ሥራው በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ዞኖች እና ወረዳዎች በተጠናከረ መልኩ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ባበከር፤ ሥራው ለሁለት ወራት በሳምንት ለሁለት ቀናት የሚሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

በክልሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN MEDIA AUTHORITY

# የዲጂታል ማስታወቂያዎችን ቁጥጥር ያካተተ ፖሊሲ እየተዘጋጀ ነው

ገጽ 4




ገጽ 3

እንቦጭን ለማጥፋት የ10 አመት እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል





አቶ ማስረሻ በላቸው

## በደቡብ ምዕራብ ክልል ከአምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰበሰበ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከአምስት ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰቡ ተገለጸ።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ እና ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ማስረሻ በላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በመኸር ወቅት 297 ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት የታቀደ ቢሆንም 303 ሺህ 776 ሄክታር መሬት በሰብል መሸፈን ተችሏል። በምርት ደረጃም ሰባት ሚሊዮን 303 ሺህ 263 ኩንታል ምርት በመኸር ወቅት ለማግኘት ነው የታቀደው። በተደረገው ሙያዊ ግምገማም ለማግኘት የታቀደው ምርት እንደሚገኝ ይጠበቃል።

በአጠቃላይ ከተመረተው የመኸር ምርት 273 ሺህ 083 ሄክታር ላይ ከሚገኝ ሰብል አምስት ሚሊዮን 377 ሺህ 402 ኩንታል ምርት እስካሁን በተካሄዱ ሥራዎች መሰብሰቡን አቶ ማስረሻ ተናግረዋል። ደጋማ በሆኑ አካባቢዎች እንዲሁም ዘግይተው የተዘሩ ሰብሎች በቀጣይ የሚሰበሰቡ ሲሆን የሰብል ስብሰባው ሂደት በአጭር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ሲሉ ገልጸዋል።

በክልሉ በቆሎ እና የአገዳ ሰብሎች በስፋት የሚመረቱ ሲሆን ስንዴ እና ገብስ የሚመረትባቸው አካባቢዎች አሉ። በዘንድሮው ዓመት ለስንዴ ምርት ትኩረት በመስጠት በመኸር ወቅት ከለማው መሬት ውስጥ 23 ሺህ 763 ሄክታሩን በስንዴ ምርት በመሸፈን 704 ሺህ ኩንታል ስንዴ ማምረት መቻሉን አቶ ማስረሻ ተናግረዋል።

በዘንድሮ ዓመት እንደ አገር የስንዴ ምርትን ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት በክልሉ የተሻለ ምርት እንደተመረተ የተናገሩት ኃላፊው፤ የገበያ ትስስር መፍጠሩ ላይ ቀሪ ሥራዎች እንደሚያስፈልጉም ተናግረዋል።

ክልሉ ከምሥረታው ጀምሮ ወደ አርሶ አደሩ ቀረብ ብሎ በመሥራት በተለይም በተቋማት አካባቢ ያሉ ከዚህ በፊት ያልታረሱ መሬቶች ሳይታረሱ እንዳይከርሙ መደረጉ ከዕቅድ በላይ መሬት በሰብል መሸፈን መቻሉን ጠቁመው፤ በቀጣይም በክልሉ መታረስ የሚችሉ መሬቶች ሁሉ እንዲታረሱ እንደሚደረግም ጠቁመዋል።

አቶ ማስረሻ እንደሚሉት፤ በክልሉ አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ያለው ፍላጎት አናሳ መሆን በዋናነት ያጋጠመ ችግር ነው። አካባቢው ዝናባማ የሚባል በመሆኑም ለመሬት ለምነት ጠቃሚ የሚባሉ ንጥረ ነገሮች እየታጠቡ የሚሄዱና 60 በመቶ የሚሆነው በክልሉ ያለው መሬት አሲዳማ በመሆኑ መሬቱን በኖራ ማከም ያስፈልጋል።

የኖራ ምርት እንደ አገር ከፍተኛ የሆነ እጥረት በመኖሩ ተግዳሮት መፍጠሩን የተናገሩት አቶ ማስረሻ፤ የአፈር ማዳበሪያም በሚፈለገው መጠን ማሰራጨት አለመቻሉ ያጋጠሙ ችግሮች እንደሆኑ ተናግረዋል።

በየቀበሌው የሚሠሩ የግብርና ባለሙያዎችን በዕውቀት እና በስልጠና አቅማቸውን በመገንባት በጋራ መሥራት ከተቻለ በግብርናው ዘርፍ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል የተናገሩት ኃላፊው፤ በተጨማሪም የአርሶ አደሩን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የአመለካከት እና የአቅርቦት ችግርን እየፈቱ መሄድ ከተቻለ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ይቻላል ብለዋል።

## ኢንስቲትዩቱ ብዝሃ ሕይወትን ለመታደግ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር እየሠራ ነው

**በሪሁ አረጋ**

አዲስ አበባ፡- ብዝሃ ሕይወትን ለመታደግና ለመንከባከብ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መለሰ ማርዮ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ኢንስቲትዩቱ 20 እና ከዚያ በላይ ከሚሆኑ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ሥራዎችን እየሠራ ነው። ባሳለፍነው ሳምንት በተመሳሳይ መልኩ በዓባይ ግድብ ዙሪያ የሚገኙ ብዝሃ ሕይወት ለመጠበቅና ለመንከባከብ ከአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር አብረው ለመሥራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የአገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አሻራ የሆነው የዓባይ ግድብ ያለበት ክልል ውስጥ በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ በግድቡ ዙሪያ የሚገኙ ብዝሃ ሕይወቶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በቅንጅት መሥራቱ ትልቅ ፋይዳ መኖሩን ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፣ ኢንስቲትዩቱ ቀደም ሲል በግድቡ አካባቢ የሚገኙ እፅዋትንና እንስሳትን የመለየት ሥራ ሠርቷል። ብዝሃ ሕይወቶችን በዘላቂነት ለመጠበቅና ለመንከባከብም እንቅስቃሴ ጀምሯል። ብዝሃ ሕይወቱ ተፈጥሯዊነታቸው ጠብቀው እንዲቆዩ በጥናት የተደገፈ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ሚናው ጉልህ ነው።

ግድቡ ረጅም ዕድሜ እንዲኖረው በቀጣይ ሥርዓተ ምህዳርን የማደስ ሥራ እንዲሁም ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የአካባቢውን ሥርዓተ ምህዳር የመንከባከብ ሥራ በቅንጅት ይሠራል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የበርካታ ብዝሃ ሕይወት ሀብት ባለቤት እንደመሆኗ መጠን አንዱ አካባቢ ያለው በሌላው አካባቢ ስለማይኖር ስለጉዳዩ ግንዛቤን



ዶክተር መለሰ ማርዮ

ለማዳበር በትብብር መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ለዚህም ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጋራ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል።

ኢንስቲትዩቱ የምርምር ተቋም ከመሆኑም በተጨማሪ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የማማከርና የስልጠና ሥራዎችንም እያከናወነ ነው ብለዋል።

ብዝሃ ሕይወት ከመጠበቅም አልፎ የይዘት ቦታ ጥበቃ ላይ በተለይም የመድኃኒት እፅዋት የመለየት፣ ደኖችን የመጠበቅ እንዲሁም ቦታኒክ ጋርደን በማዘጋጀት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እያስጎበኙ መሆኑንም አክለው ተናግረዋል።

ዶክተር መለሰ፣ በቦታኒክ ጋርደኑ ብዝሃ ሕይወትን መጠበቅ የሚያስችል ተሞክሮ የሚገኝበት ከመሆኑም በላይ ከእፅዋት መድኃኒት ለመቀመም እና ምርምር ለማካሄድ አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ ነው ብለዋል።

## ዘመናዊ የቅድመ አደጋ ጥቆማ ዘዴ ተግባራዊ ሊደረግ ነው

**ገመቹ ከድር**

አዳማ፡- በመላው አገሪቱ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በዓይነትና በጥልቀቱ ለይቶ የቅድመ አደጋ ጥቆማ መልዕክት መስጠት የሚያስችል ዘመናዊ ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ላይ መሆኑን የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር አስታወቀ።

ዘዴው አገር በቀል እውቀቶችን መሠረት በማድረግና ከኢትዮጵያ ሜትሪዮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚገኙ መረጃዎችን በመቀበል ለውሳኔ ሰጪ አካላት ግብዓት የሚሆን መልዕክት እንደሚሰጥም ተገልጿል።

በማኅበሩ የአደጋ ምላሽ መምሪያ የፈጠራ አቀራረብ ቅድመ አደጋ ምላሽ ዝግጁነት ፕሮጀክት ኃላፊ አቶ አብርሃም ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እየተዘጋጀ ያለው ዘዴ ከኢትዮጵያ ሜትሪዮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚገኙ መረጃዎችን በአገር በቀል እውቀቶችን በማጣመር የቅድመ አደጋ መልዕክቶችን በዓይነትና በጥልቀት ለይቶ የሚያደርስ ነው። እስከ አሁን በተደረገው የሙከራ ትግበራ በተላኩ ቅድመ አደጋ መልዕክቶች የኅብረተሰቡን ሕይወት ማዳን ተችሏል።

የቀይ መስቀል ማኅበር ሴክተር ተቋማትንና የዓለም አቀፍ ርዳታ ቡድን በአሠራሩ ውስጥ እንዲሳተፉ ድጋፍ በማድረግ አደጋ ከመድረሱ በፊት በራሱ መልዕክት ማድረስ የሚችል ሲስተም ለአራት ዓመታት ሲሠራበት መቆየቱንም አውስተዋል።

ለሥራው ስኬታማነት የኢትዮጵያ ሜትሪዮሎጂ ኢንስትቲዩት በአጋርነት ከማኅበሩ ጋር በመስራት ላይ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው፤ ከዝናብ ጋር በተያያዘ ወደ ኋላ በመመለስ የ20 ዓመታት ልምዶችና ወቅታዊ የአየር ጠባይ መረጃዎች ወደ አሠራሩ እንዲገቡ ይደረጋል ብለዋል።

አሠራሩ ተጽዕኖ ፈጣሪ መረጃዎችን በማንበብ አደጋው ከመድረሱ በፊት አንድ ወር አስቀድሞ የማስጠንቀቂያ መልዕክት በመላክ በጎርፍ፣ በድርቅ፣ በዝናብ ስርጭት መቋረጥ አርሶ እና አብርቶ አደሩ ተዘናግቶ አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ለማድረግ ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

እንደ አቶ አብርሃም ገለጻ፣ ማኅበሩ ከተዘረጋው አሠራር የሚደርሱትን መልዕክቶችን መሠረት በማድረግ አደጋው ከመድረሱ በፊት ኅብረተሰቡ የሚሰፍርበትን ቦታ እና ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ ይሠራል። ድርቅ እና የዝናብ መቋረጥ የሚከሰትባቸው አካባቢዎች ኅብረተሰቡ ያለውን ውሃ ቆጥቦ እንዲጠቀም፣ ከዝናብ ሁኔታ ጋር የሚሄድ አዝርዕት እንዲተከሉ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንዲሠሩ ዕድል የሚሰጥ ነው።

ማኅበሩ እስከ አሁን ድረስ ከተዘረጋው አሠራር በደረሰው መልዕክት መነሻነት በተሰራው የሙከራ ትግበራ ዘርፈ ብዙ ቅድመ አደጋ መከላከል ሥራዎችን መስራቱን ያብራሩት አቶ አብርሃም፤ ከዚህም አንጻር በአፋር ክልል ዱብቲ አካባቢ በጎርፍ በተጎዱ ለ1ሺህ 900 አባ ወራዎች ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በመስጠትና በጀኒያ አፈር ሞልቶ ጎርፍ የሚከላከሉበት እርከን በመስራት የመታደግ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

በምሥራቅ ባሌ በሰዌና ወረዳ በድርቅ በተጎዱ ለ1ሺህ አባወራዎች 6 ሚሊዮን ብር እንዲያገኙ ማስቻላቸውን አስታውቀዋል።

አሠራሩ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲሆን ለመንግሥት እንደሚያስረክቡ የገለጹት ኃላፊው፤ በቀጣይ ከሲስተሙ በሚገኙ መልዕክቶች መሠረት የቅድመ አደጋ መከላከል ሥራዎች ላይ በትኩረት እንደሚሠራ አመልክተዋል።

ማኅበሩ አገራዊ ችግሮችን ለመፍታት በ72 ዞኖችና በ170 ወረዳዎች ቢሮ በመክፈት ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል።

ዜና

# «በሕዝብ መሰብሰቢያ ስፍራ ትምባሆ የሚያጨሱ ሰዎች ተበራክተዋል»

*- የመዲናዋ ነዋሪዎች*

# «ጠንካራ ቅጣት የሚጥል ደንብ እየተዘጋጀ ነው»

*- የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን*

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ትምባሆ የሚያጨሱ ሰዎች ቁጥር በመበራከቱ ጉዳዩ ሊስተካከል ይገባል ሲሉ ነዋሪዎች ቅሬታቸውን አቀረቡ፡፡

ችግሩን ለመከላከል የሚደረገው ቁጥጥር እንደቀጠለ ቢሆንም በሕዝብ መሰብሰቢያና ባልተፈቀዱ ቦታዎች ሲጋራ በሚያጨሱ ግለሰቦች ላይ ጠንከር ያለ ቅጣት የሚጥል ደንብ እየተዘጋጀ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የአዲስአበባ ነዋሪ የሆነው ወጣት ዮናታን ተፈራ፤ የሕዝብ መገልገያ ቦታዎች ላይ ሲጋራን የሚያጨሱ ሰዎች በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ላይ በብዛት እያስተዋለ መሆኑን ተናግሯል።

የትንባሆ ቁጥጥር አዋጅ በአገር አቀፍ ደረጃ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ቁጥጥሩ ላይ ትልቅ መሻሻል ያመጣ ቢሆንም፤ አሁን ላይ ግን ችግሩ እንዳገረሸ የሚገልጸው ወጣቱ፤ በአሁኑ ወቅት በትምባሆ ማጨስ ሱስ በተለይም ታዳጊ ወጣቶችን ተጎጂ ያደረገ ችግር በተስፋፋ መልኩ መከሰቱን ጠቁሟል።

በሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች በነፃነት ትምባሆ የሚጨስበት መንገድ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ ካልተቻለ የሚጎዳው ሕዝብ ብዙ ነው ያሉት ደግሞ ሌላኛው የከተማዋ ነዋሪ አቶ ብሩክ አያሌው ናቸው፡፡

ችግሩ በተለይም ከመተንፈሻ አካላት ጋር በተያያዘ ተጓዳኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ላይ ትልቅ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል። ሰዎች በገበያ ስፍራዎች፣ በመዝናኛ ስፍራዎችና በተለያዩ የሕዝብ መገልገያ ቦታዎች፣ ሲጋራ በማጨሳቸው በአካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎች ጤና ላይ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአዲስአበባ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን የትንባሆ ቁጥጥር ዘርፍ አስተባባሪ አቶ አሸናፊ ደመቀ በበኩላቸው ትንባሆ ላይ የሚደረገው ቁጥጥር አለመቋረጡን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል።

በዘላቂነት ችግሩን ለመፍታት ቁጥጥሩንና ቅጣቱን ለማጠናከር የሚረዳ ደንብ እየተዘጋጀ ይገኛል ያሉት አቶ አሸናፊ፤ ሕጉን በከተማዋ ምክር ቤት አቅርቦ ለማጸደቅ ዝግጅት መደረጉን አስታውቀዋል።

ከደንብ አስከባሪ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው 16 መሥሪያ ቤቶች ጋር ቁጥጥሩን ለማጠናከር ስምምነት ላይ ደርሰናል ብለዋል። በምሽት ወቅት በተለያዩ ቦታዎች ሕዝብ በተሰበሰበበት ስፍራ ሲጋራ የሚያስጨሱ ድርጅቶች መኖራቸውን የገለጹት አስተባባሪው፤ ቁጥጥር በማድረግ ጥፋቱ በተገኘባቸው ድርጅቶች ላይ ርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ባለፈው ዓመት ብቻ ከሕገወጥ የሲጋራ አጠቃቀምና ዝውውር ጋር በተያያዘ በተደረገ ክትትልና ቁጥጥር ከ27 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የትንባሆ ምርት መወረሱን አስታውቀዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ስለችግሩ አሳሳቢነት የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እየተዘጋጁ ነው። በሁለት ክፍለ ከተሞች በተመረጡ በስድስት ወረዳዎች ላይ የተጀመረው የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ ወደ 11 ክፍለከተሞች ከፍ እንዲል ተደርጓል ብለዋል።

ስለትንባሆ ጉዳት የሚያሳውቁ 12 ትልልቅ ማስታወቂያዎች በከተማዋ የተለያዩ ስፍራዎች በማዘጋጀት ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እየተሠራ ነው፡፡ በሚዲያዎች ላይ ዘጋቢ ፊልሞችን እና የማስታወቂያ ሥራዎችን በማስተላለፍ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችል ተግባር ማከናወን ተችሏል ሲሉም ተናግረዋል።

ሲጋራ አምራቾች በምርት ሽፋናቸው ላይ በጽሑፍም ሆነ በምልክት ስለጤና ጎጂነቱ የሚያትት ማስጠንቀቂያ እንዲያስቀምጡ ተደርጓል፤ በጉዳዩ ላይ ችግር ሲገኝም ማስተካከያ ይደረጋል ሲሉም ተናግረዋል።

በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 መሠረት ከበር መልስ ባለ ለሕዝብ ክፍት በሆነ ማንኛውም ቦታና የሥራ ቦታን ጨምሮ ሲጋራ ማጨስ የተከለከለ ነው።



# እንቦጭን ለማጥፋት የ10 አመት እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ከጣና ሐይቅ ላይ የእንቦጭ አረምን በዘላቂነት ለማጥፋት የሚረዳ የ10 ዓመት ስትራቴጂካዊ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ መገባቱን የጣና ሐይቅና ሌሎች የውሃ አካላት ጥበቃና ልማት ኤጀንሲ አስታወቀ።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጣና ሐይቅና ሌሎች የውሃ አካላት ጥበቃና ልማት ኤጀንሲ መጤና ተስፋፊ ዝርያ ክትትልና ቁጥጥር ተወካይ ዳይሬክተር አቶ መዝገቡ ዳኜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዕቅዱ ዋና አላማ እንቦጭን በ10 ዓመት ከጣና ሐይቅ ማጥፋት ነው።

የእንቦጭ አረም እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ አረሙን በቋሚነት ከጣና ሐይቅ ላይ ለማጥፋት የሚረዳ ስትራቴጂካዊ እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ተገብቷል ሲሉ ተናግረዋል።

እንቦጭ ራሱን በእጥፍ እያስፋፋ የሚያድግ ስለሆነ የተጠናከረ ዘመቻ ያስፈልገዋል። ባለፉት ዓመታት አረሙን ለማጥፋት እየተገለገልን ያለነው አካላዊ የማስወገድ ዘዴዎችን ነው፤ ይሁንና ለውጤታማነቱ የተሻሉ አማራጮችን መጠቀም አለብን ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ አረሙን ለማስወገድ የተለያዩ አማራጮች አሉ ያሉት አቶ መዝገቡ፤ በእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ በዋናነት የምንከተለው እንቦጭን በእጅ በመንቀል የማስወገድ ተግባር ከሐይቁ ስፋትና ከአረሙ ስርጭት አንጻር የሚፈለገውን ውጤት እንዳይመጣ ማድረጉን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ መዝገቡ ገለጻ፤ ለእንቦጭ ማስወገጃነት የሚውሉ ማሽኖች ከውጭ አገራት ወደ አገራችን መጥተዋል። ነገርግን ማሽኖቹ አረሙን ለማስወገድ በከፍተኛ የውሃ ጥልቀትና መንሳፈፍን ይጠይቃሉ። በጣና ሐይቅ ላይ ያለው እንቦጭ ደግሞ አነስተኛ ጥልቀት ያለበት የሐይቁ ዳር ላይ በመዛመቱ ማሽኖቹን በአግባቡ ለመጠቀም አዳጋች ሆኗል።

በመሆኑም በዋናነት የሰው ኃይልን በማስተባበር አረሙን ከስሩ ነቅሎ ማጥፋት ላይ የተመረኮዘ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

አረሙ ከተነቀለ በኋላ ስፍራው ላይ የመልሶ ማገገም ሥራዎች በማስፈለጋቸው አገር በቀል የሳር ዝርያዎችንና በአረሙ እድገት ላይ ጫና የሚያሳድሩ ተክሎችን የመተካት ሥራ ይከናወናል ብለዋል። በስፍራው የሚተከለው ሣር ለእንስሳት መኖ እንዲውል በማድረግ የአረሙን እንቅስቃሴ ለመግታት መታቀዱን አስታውቀዋል።

አቶ መዝገቡ እንደገለጹት፤ በጣና ሐይቅ ዙሪያ የተለያዩ ብዘሀ ሕይወቶች በመኖራቸው የእንቦጭ አረም መከሰቱ በአካባቢው ስነምህዳር ላይ ያሳደረው ጉዳት ከፍተኛ ነው። የሐይቁ የውሃ መጠንና የዓሣ ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል።

አረሙ በመስፋፋቱ ሐይቁንና በሐይቁ መሃል የሚገኙ ገዳማትን በተለይም ጣና ቂርቆስ ገዳምን ለመጎብኘት የሚመጡ ቱርስቶች ቁጥር አሽቆልቁሏል። በዚህም የቱሪዝም እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ጫና እየደረሰ ይገኛል ብለዋል።

ኅብረተሰቡ የጣና ሐይቅ ላይ የተጋረጠውን የእንቦጭ አረም ለማጥፋት በቻለው አቅም ድጋፍ እንዲያደረግ የቴሌቶን ገቢ ማሰባሰቢያ መርሃግብር ለማዘጋጀት እቅድ ተይዟል ያሉት አቶ መዝገቡ፤ የገንዘብ አቅምን በማጠናከር የ10 ዓመቱ መሪ እቅድ ለማሳካት ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

የአረሙን አስከፊነት ለኅብረተሰቡ ከማስገንዘብ አኳያ ሰፊ ሥራ ይጠይቃል። መገናኛ ብዙኃን፣ የማኅበረሰብ አንቂዎችና ባለሀብቶች ጣና ሐይቅ የመላው ኢትዮጵያውያን ሀብት መሆኑን በመገንዘብ አረሙን እስከመጨረሻው ለማጥፋት እንዲረባረቡ ጥሪ አቅርበዋል።

# ውል የተገባለት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት የጤና ተቋማትን አገልግሎት ለማሻሻል አግዟል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ውል የተገባለት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረጋችን የጤና ተቋማትን የግብዓት ጥያቄ በወቅቱ በመመለስ አገልግሎታቸው እንዲሻሻል ያግዛል ሲል የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት ገለፀ፡፡

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አቡዱልቃድር ገልገሎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከዚህ ቀደም መድኃኒትና የህክምና መሣሪያዎች ተገዝተው ያለውል ለጤና ተቋማት ሲቀርቡ ቆይቷል።

የመድኃኒት አቅርቦቱ ሆስፒታሎች በሚያቀርቡት የፍላጎት ትንበያ መሠረት የሚዘጋጅ በመሆኑ ፍላጎትና አቅርቦቱ ሳይመጣጠን ሲቀር ዘርፈ ብዙ የአገልግሎት ጥራት መጓደሎች ይከሰቱ እንደነበር ገልጸዋል።

የቀደመው አሠራር የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ያለጥቅም ረጅም ጊዜ እንዲቆዩና እንዲበላሹ ማድረጉን ጠቁመው፤ ችግሩ የመንግሥትንና የጤና ተቋማትን ሀብት እንዲባክን ያደርጋል ብለዋል፡፡



ዶክተር አቡዱልቃድር ገልገሉ

አሁን ላይ ግን ፍላጎትና አቅርቦትን መሠረት ባደረገ መልኩ ውል በመፈጸም ግብዓት ለማቅረብ የሚያስችል ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉን አስታውቀዋል።

አሠራሩ የመድኃኒት አቅርቦት በተፈለገው ዓይነትና መጠን እንዲሆን በማገዝ ግልጸኝነትንና ተጠያቂነት ለማስፈን የሚረዳ ነው ሲሉ ዶክተር አቡዱልቃድር ተናግረዋል።

የውል ሥርዓቱ ዋና አላማ የጤና ተቋማት ግብዓቶችን በታቀደ ወቅትና በተጠና መጠን የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት መሆኑን ጠቁመዋል።

የመድኃኒት አቅርቦት ፍላጎት በመጨመሩና የጤና ሥርዓታችን አገልግሎት ለማኅበረሰቡ ፈጣን ምላሽ ሰጪ እንዲሆን ለማስቻል ውል ወደተገባለት ሥርዓት መሸጋገራችን ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎትና በጤና ተቋማት መካከል በሚፈረም ውል አማካኝነት ለሚያገኙት አገልግሎት ክፍያ ይፈጽማሉ ያሉት ኃላፊው፤ ሆስፒታሎቹ በሚፈልጉት መጠን አቅርቦቱ ሲመቻችላቸው አገልግሎታቸውን ማሻሻል ይችላሉ ሲሉ ገልጸዋል።

ቀደም ብሎ ያለው አሠራር ችግር ነበረበት፤ በተደረገው ጥናት ለጤና ተቋማት ተብለው ከሚቀርቡ ግብዓቶች ጥቅም ላይ የሚውሉት ከ30 በመቶ እንደማይበልጡም አስታውሰዋል።

አሁን ላይ ግን በውል ሥርዓቱ መሠረት በተለዩ ግብዓቶች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ለሆስፒታሎች ጥያቄ ምላሽ መስጠትና ግብዓቱን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል አሠራር ተፈጥሯል ብለዋል።

ሆስፒታሎች ካሏቸው የተገልጋይ ቁጥር፣ ከሚያገለግሉት ሰፊ አካባቢና ከሚያከናውኑት ትልቅ ግዥ አንጻር የውል ሥርዓቱ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ዶክተር አቡዱልቃድር ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዶክተር አቡዱልቃድር ገለጻ፤ የመድኃኒት አቅርቦት ተደራሽነት ላይ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ የጤና ተቋማት ጠንካራ የፋይናንስ አቅም ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ዜና

# የዲጂታል ማስታወቂያዎችን ቁጥጥር ያካተተ ፖሊሲ እየተዘጋጀ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- እየተስፋፋ የመጣውን የዲጂታል ማስታወቂያን ጭምር የሚቆጣጠር የማስታወቂያ ፖሊሲ እየተዘጋጀ መሆኑን የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን አስታወቀ።

የባለስልጣኑ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ደሴ ከፋለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ የማስታወቂያ አዋጅ እንጂ የማስታወቂያ ፖሊሲ የላትም። በዚህ ምክንያት አዋጁ ያላካተታቸው ጉዳዮችን ለማካተትና በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመሙላት ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል።

እየሰፋ የመጣውን የማስታወቂያ ዘርፍ ለመቆጣጠር እንዲመች የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ጠቃሚ መሆኑን የተናገሩት አቶ ደሴ፤ ባለስልጣኑ እያዘጋጀ ያለው ፖሊሲ ከዚህ ቀደም የነበሩትን ችግሮች እንደሚቀርፍ ገልጸዋል።

አሁን በኢትዮጵያ ሥራ ላይ ያለው 759/2011 የማስታወቂያ አዋጅ ከ10 ዓመት በፊት የወጣ አዋጅ መሆኑን አንስተው፤ አዋጁ በፖስታ፣ በህትመት፣ በፊልምና በመሳሰሉት ስለሚሰራጩ ማስታወቂዎች የሚያትት እንጂ የዲጂታል ማስታወቂያን ያላከተተ በመሆኑ ከጊዜው ጋር የሚሄድ ማስታወቂያ ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል።

እየተዘጋጀ ያለው ፖሊሲም በዘርፉ ያሉ አካላትን ሁሉ ያካትታል የተባለ ሲሆን፤ ማስታወቂያ አስነጋሪ፣ ማስታወቂያ አሰራጭ እና መገናኛ ዘዴዎች ምን ምን መያዝ እንዳለባቸው የሚያትት ሰነድ እንደሆነ አቶ ደሴ ገልጸዋል።

አሁን ላይ የፖሊሲው ረቂቅ የመጀመሪያ ድራፍት የሚባለው ደረጃ ላይ ሲሆን የህግ ሰንሰለቱን፣ የፖሊሲ ማዕቀፎች የሚወጡበትን አግባብ ተከትሎ ተግባራዊ ይደረጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የማስታወቂያ ፖሊሲው በባለስልጣኑ ባለሙያዎችና ሌሎች በሚመለከታቸው አካላት ተዘጋጅቶ ውይይት ከተደረገ በኋላ ሥራውን በማጠናቀቅ በዚሁ ዓመት ወደ ፍትሕ ሚኒስቴር ለመላክ መታቀዱንም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ደሴ ማብራሪያ፣ የማስታወቂያ ዘርፉ የአገሪቱን ጠቅላላ ምርት 2 በመቶውን የሚሸፍን ነው። ነገር ግን ሁሉን አቀፍ ፖሊሲ በማዘጋጀት ከዘርፉ በይበልጥ ተጠቃሚ አንድ ነገር ሆኖ ከነጭራሹ እንደ አገር የማስታወቂያ ፖሊሲ አለመኖሩ ክፍተቶችን ፈጥሯል።

ፖሊሲው ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሲሆን ግን የዘርፉን ተጠቃሚነት ከማጉላት ባሻገር ብዙ ደንበኞች ያለውን የዲጂታል ማስታወቂያ ዘርፍ በአግባቡ ለመቆጣጠር እንደሚረዳም ተናግረዋል። በጥቅሉ ሁሉም የማስታወቂያ ዘርፎች በህግና በሥርዓት እንዲመሩ ፖሊሲው ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

# ጉባዔው በምግብ ዋስትና ላይ ማተኮሩ ለአህጉሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት የሚጥል ነው

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- 36ኛው የአፍሪካ ህብረት ጉባዔ በምግብ ዋስትና ላይ ማተኮሩ የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ችግር ለመሻገር መሠረት የሚጥል መሆኑ ተጠቆመ።

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የምጣኔ ሀብት ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ጀማል መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ 36ኛው የአፍሪካ ህብረት ጉባዔ የአየር ንብረት ለውጥ ተጠቂ የሆኑ የአፍሪካ አገራት የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እያጋጠሙ ያሉ ፈተናዎችን ለመሻገር የሚያስችል አቅም ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በርካታ የአፍሪካ አገራት ወደ ኋላ የቀሩበት ሁኔታ እንዳለ በመጠቆም፤ ጉዳዩ ብዙ ሥራ የሚጠይቅ እንደሆነ አመላክተዋል። በተለይ የአፍሪካ አገራት የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራቸውም አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል አርሶ አደር እንደመሆኑም የምግብ ዋስትናቸውን ያላረጋገጡ ስለመኖራቸው ነው ዶክተር ጀማል የገለጹት።

በአሁኑ ወቅት ችግሩን እያባባሰ የሚገኘው የአየር ንብረት ለውጥ መሆኑንና በዚህም የተነሳ የውሃና የዝናብ መጠን መቀነሱን፤ የእርሻ ምርታማነትን እየቀነሰ በመሄዱ በምግብ ዋስትና ላይ ችግሮች እየተስተዋሉ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል። ውጤቱ ድርቅን ጨምሮ ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎችን እያስከተለ መሆኑን ነው ዶክተር ጀማል የሚያነሱት።

አፍሪካ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብቱ ቢኖርም አብዛኛው ምርት የሚመረተው በአውሮፓና አሜሪካ ውስጥ ነው ያሉት ዶክተር ጀማል፤ በዚህ ወቅት በዩክሬንና በሩሲያ ጦርነት ምክንያት ታዳጊ አገራት የባሰ ችግር ውስጥ መግባታቸውንም አንስተዋል።

ስንዴ፣ በቆሎና ማዳበሪያ የሚመረተው በአብዛኛው በእነዚህ አካባቢዎች እንደሆነና በጦርነቱ ቀውስ ምክንያት ምርት መቀነሱን ጠቅሰዋል። በተጨማሪም በምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ከፍተኛ ድርቅ መከሰቱን በመግለጽ፤ የኅብረቱ ጉባዔ የምግብ ዋስትናን አጀንዳ ማድረጉ አህጉሪቱ የምትፈተንበትን የግብርና ችግር ለመፍታት መልካም አጋጣሚ እንደሆነ አስታውቀዋል። አጀንዳው ወቅቱን የጠበቀ መሆኑንና ኢትዮጵያን ጨምሮ ለየአገራቱ የኢኮኖሚ ፋይዳን ይዞ ይመጣል ሲሉ ነው የገለጹት።

በጉባዔው በዋናነት የእርሻ ምርትን በማሻሻል ምርታማነትን መጨመርና የምርት ዝውውር እንዲኖር የሚያስችሉ ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ ጠቁመዋል። የአፈርና የውሃ አጠባበቅን፣ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ የሚያደርጉ ጉዳዮችን መቀነስና ጉዳዩ ላይ ኢንቨስት አድርጎ ለመስራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚንሸራሸሩበት ሊሆን እንደሚችልም አመላክተዋል።

እንደ ዶክተር ጀማል ገለጻ፤ አፍሪካ ውስጥ ሰፋፊ መሬቶች ቢኖሩም ኢንቨስትመንትና መሠረተ ልማቱ በቂ አይደለም። ስለዚህም መስኖ ላይ ኢንቨስት መደረግ ይኖርበታል። በካይ ጋዞች ወደ አየር የሚለቁ አገራት የሙቀት መጠኑን እየጨመሩ በውሃ ትነት የውሃ መጠን እንዲቀንስ እያደረጉ ነው። የአፍሪካ ኅብረት ጉባዔም በዚህ ዙሪያ ጠለቅ ያለ ሀሳብ ያነሳል ተብሎ ይጠበቃል።

አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገራት እርሻ ላይ ጥገኛ እንደመሆናቸውና የአየር ንብረት ለውጥ የሚጎዳው እርሻን ስለሆነ በተለይ ውሃን ከብክለት በመከላከል ረገድ ጠንካራ ውሳኔዎች ሊተላለፉ ይገባል ነው ያሉት።

## በበጋ መስኖ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደ ዶክተር ዳንኤል ገለፃ፤ የኢትዮጵያ ግብርና ኢንስቲትዩት ለበጋ መስኖ ስንዴ ሙያዊ ድጋፍ እያደረገ ነው። ኢንስቲትዩቱ በተለያዩ ማዕከላት ያሉትን ባለሙያዎች በሁለት ቡድን የከፈለ ሲሆን አንደኛው ቡድን ፕሮጀክቱ ሲጀመር በመሬት ዝግጅት፣ በውሃ አያያዝ፣ በሰብል እንክብካቤና ጥበቃ ሙያዊ ድጋፍ የሚያደርግ ነው። ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ለበጋ መስኖ ስንዴ ተስማሚ የስንዴ ዘር እንዲመረጥ የሚያግዝ ነው።

የኢትዮጵያ ግብርና ኢንስቲትዩት በበጋ መስኖ ስንዴ ከፍተኛ ውጤት እንዲገኝና ቀጣይነት እንዲኖረው በትኩረት እየሠራ ነው ያሉት ዶክተር ዳንኤል፤ ከሦስት ሺህ 500 ሄክታር መሬት ተነስቶ አሁን ከአንድ ሚሊዮን 336 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት መድረስ ችሏል ብለዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ አጀማመር አዲስ እንደመሆኑ መጠን በመስኖ አጠቃቀም ዙሪያ አንዳንድ ክፍተቶች ይስተዋላሉ። በተለይ በቆላማው አካባቢ የበጋ መስኖ ስንዴው በጎርፍ መልክ ውሃ የሚጠጣ በመሆኑ ውጤቱን ሊቀንስ ይችላል። ስለዚህ ይህንን በማስተካከል ወደ ፊት በዘመናዊ መንገድ እንዲከናወን ይደረጋል።

ሌላው የበጋ መስኖ ስንዴ ጥቅምት ወር አጋማሽ ላይ የሚጀመር ሲሆን ከምርጥ ዘር ማነስ፣ ከበጀትና በሌሎች ምክንያቶች ክልሎች በወቅቱ ወደ ሥራ መግባት አልተቻለም። ይህም በሂደት የሚፈታ ችግር እንደሆነ ተናግረዋል።

ከበጋ መስኖ ስንዴ 40 ኩንታል በሄክታር ለማግኘት እየተሠራ ሲሆን ይህንን ለማድረግ የአረም፣ የተባይና የወፍ ቁጥጥር እንዲሁም የማዳበሪያ አጠቃቀምን ሁሉም ክልል እንዲያሻሽል እና ሜካናይዜሽን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ተናግረው የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

## በክልሉ 64 ሺህ ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በክልሉ የተፋሰስ ሥራዎችን የሚደግፉ ድርጅቶች መኖራቸውን ያስታወሱት የቢሮ ኃላፊው፤ ለሥራው ተግባራዊነት ኅብረተሰቡን የሚደግፍና የሚያስተባብር የክልሉ የሥራ ኃላፊዎችን ያካተተ የባለሙያዎች ቡድን በየአካባቢው ለማሰማራት አስፈላጊው ዝግጅት መጠናቀቁንም አስታውቀዋል።

ኅብረተሰቡ ለተፋሰስ ሥራው ያለውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ባለፉት ዓመታት በተሰሩ ሰፋፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ውጤት መገኘቱን የጠቆሙት አቶ ባበከር፤ በተፋሰስ ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራው «የከልብ ፕሮጀክት» በ88 አካባቢዎች ላይ የሚሠሩ ሥራዎችን እየደገፈና ሕዝቡ በሚያስመዘግበው ውጤት ልክ ክፍያ እየፈጸመ ለሥራው ስኬታማነት እያገዘ ነው ብለዋል።

የተፋሰስ ሥራው በመጪው ክረምት ከሚከናወነው የአረንጓዴ አሻራ ቅድመ ዝግጅት ሥራ ጋር በተቀናጀ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህም በችግኝ ጣቢያዎች ቀደም ብለው መዘጋጀት ያለባቸውና የሚተከሉ ችግኞችን የማዘጋጀትና በሚቀጥሉት ሦስት ወራት የሚደርሱ ችግኞችን ለማፍላት ዘሮችን የማዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ባለፉት ዓመታት የተሠሩት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎች ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች መልሰው ያገገሙ ሲሆን ደርቀው የነበሩ ወንዞችም ተመልሰው ለሕዝቡ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን አመላክተው፤ እያንዳንዱ ሥራ ሊሳካ የሚችለው ኅብረተሰቡ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ ነው ብለዋል።

የተጀመረው የ2015 ዓ.ም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ የታለመለትን ግብ እንዲመታ ኅብረተሰቡ አካባቢዎችን ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በማድረግና ያልተሰበሰቡ ሰብሎችን በቶሎ በመሰብሰብ ከባለሙያዎችና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የበኩሉን ሚና እንዲወጣ አቶ ባበከር ጥሪ አቅርበዋል።

የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ንቅናቄ ሥራው እንደ ክልል የጀመረው በአሶሳ ዞን ባምባሲ ወረዳ ከጥር 15/2015 ዓ.ም ጀምሮ ነው።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሄት



## "ሙስናን ስለመዋጋት ከምርመራ ጋዜጠኝነት የበለጠ መድኃኒት አይገኝም"

የቀድሞ የቢቢሲ ጋዜጠኛ አቶ መኮንን እሳቱ ሚካኤል

ገጽ 6



## ልጅ አይውጣልህ የተባለው አባት

ገጽ 10

## ጎዳናን የሚያስናፍቁ ቤቶች



ገጽ 16




ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “ሙስናን ለመዋጋት ከምርመራ ጋዜጠኝነት የበለጠ መድኃኒት አይገኝም”

## የቀድሞ የቢቢሲ ጋዜጠኛ አቶ መኮንን እሳቱ ሚካኤል

አስመረት ብስራት

**የዛሬ የዘመን እንግዳችን አቶ መኮንን እሳቱ ሚካኤል ይባላሉ። አቶ መኮንን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመካኒካል ኢንጂነሪንግ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ በነበሩበት ወቅት ብሔራዊ ውትድርና ዘመቻን በመሸሽ፤ ወደ ኬኒያ ተሰደዱ። ከኬኒያ ወደ እንግሊዝ ሀገር በመሄድ የቋንቋና የቢዝነስ ትምህርት ተከታተሉ። በመቀጠል እዛው በእንግሊዝ ሀገር የጋዜጠኝነት ትምህርትን ከተከታተሉ በኋላ፤ ቢቢሲ ትሬኒንግ ኤንድ ዴቨሎፕመንት የሚባል ቡድን ከተማሪዎቹ ውስጥ ለማሰልጠን ሶስት ልጆች ሲመለምሉ አቶ መኮንን አንዱ ሆነው ይመረጣሉ። በዛም አጭር የጋዜጠኝነት ቴክኖሎጂ ሙያ ትምህርት ወሰዱ። በመቀጠል በአፍሪካ እስተዲ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ያዙ።**

**በቢቢሲ ለአስራ አራት ዓመት፤ የቤን ቴሌቪዥን በሚባል የአፍሪካ ቴሌቪዥን ውስጥ ለአምስት አመታት፤ አፍሪካን ስፔክተር የሚባል የሬዲዮ ፕሮግራምን በመምራት ለ3 አመታት ሰርተዋል። በዶክመንተሪ ፊልሞችና በጋዜጠኝነት ሙያ ውስጥ ለሰለሳ ዓመታት የስራ ልምድ ካላቸው አቶ መኮንን ጋር እንዲህ አውግተናል። መልካም ቆይታ፡-**

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ በጋዜጠኝነት ሙያ ያሳለፉትን የሕይወት ልምድ ቢያካፍሉን?**

**አቶ መኮንን፤-** *ከልምዴ በፊት ጋዜጠኛ ምን መሆን አለበት? የሚለውን ላብራራ። ጋዜጠኝነት ከሃይማኖት ከፖለቲካና ከሌሎች ወገንተኝነት የፀዳ መሆን ይኖርበታል። ጋዜጠኛ እራሱን ከአድሎ አፅድቶ ለሚያገለገለው ማህበረሰብ ታማኝ መሆን አለበት። የጋዜጠኝነት መመሪያዎች መርህ ሆኖ እድሜ ልኬን አብሮኝ እንዲኖር የሆነው እንግሊዝ ሀገር ባገኘሁት የስራ ልምድና ትምህርት ነው።*

*ይሄን ስል እኔ ለበርካታ አመታት ያገለገልኩበት ቢቢሲ የመጨረሻ ነፃና ገለልተኛ ነው ማለት አይደለም። ይህ ሲባል ለሚፈለጉት አካል ወገንተኞች መሆናቸው፤ በሀገራዊ ጥቅማቸው የማይደራደሩ መሆናቸው፤ ከፖለቲካ አስተሳሰባቸው ጋር ለሚቃረኑ ነገሮች ቦታ የሌላቸው መሆናቸው የሚካድ አይደለም። ቢቢሲ የእንግሊዝ መንግስት አፍ ማለት ነው። ሁሉም ሀገር በዚህ ደረጃ ሀገሩን የሚጠብቅ ጠንካራ መገናኛ ብዙሃን ያስፈልገዋል።*

*በዚህ ሁሉ ውስጥ የጋዜጠኝነት አኗኗርን የጋዜጠኝነት ቁመናን በተገቢው እንዲኖረኝና ተቋሙን እንዳገለግል ተቃኝቻለሁ። ከቢቢሲ ቆይታዬ በኋላ በርካታ መገናኛ ብዙሃን ውስጥ ሰርቻለሁ። በቢቢሲ አስራ አራት አመት ከሰራሁ በኋላ፤ የአፍሪካ ቴሌቪዥን ውስጥ የቤን ቴሌቪዥን ላይ ከበርካታ ኬኒያዊያን ጓደኞቼ ጋር ለአምስት አመታት ሰርቻለሁ። አፍሪካን ስፔክተር ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ከተውጣጡ ጋዜጠኞች ጋር የሬዲዮ ፕሮግራም ስንሠራ የምመራው እኔ ነበርኩ። በዛም ለሶስት ዓመታት ሰርቻለሁ።*

*በተለያዩ የስራ ልምዶችና በወሰድኳቸው ሙያዊ ትምህርቶች ጋዜጠኛ ዜና ወደ እሱ እንዲመጣ የሚፈልግ ሳይሆን እራሱ ዜናውን ፈልጎ የሚያገኝ የአነፍናፊ ባህሪ ሊኖረው የሚገባ መሆኑን ተምሪያለሁ። ጋዜጠኛ ከቤቱ ወጥቶ ስራው እስኪደርስ ያለውን ማህበራዊ ችግሮችን የሚያይ ነው። የትም ቦታ ላይ ቢሆኑ የጋዜጠኝነት ዓይን ካለ ጋዜጠኝነት በደንብ የሚሠራ የሚወደድ ሙያ መሆኑን ባሳለፍኩት ልምድ ተመልክቻለሁ።*

**አዲስ ዘመን፤- የምርመራ ጋዜጠኝነት ስንል ምን ማለታችን ነው?**

**አቶ መኮንን፤-** *የምርመራ ጋዜጠኝነት (Investigative Journalism) የምንለው ከጋዜጠኝነት ሥራ መካከል አንዱ ነው። የምርመራ አዘጋገብ በሚያካትታቸው ነጥቦች ሥልታዊ፣ ጥልቀት ያለው፣ ያልተቀዳ ጥናትና ዘገባ፣ ብዙ ጊዜ በምስጢር የተያዙ ጉዳዮችን የሚያጋልጥ የጋዜጠኝነት የሥራ ዓይነት ነው። ሥራውን የሚሰሩ ጋዜጠኞች ተግባራዊነቱ ላይ የሕዝብ የሆኑ መዝገቦችንና መረጃዎችን በከፍተኛ ደረጃ አካትተው አትኩሮታቸውን ማኅበራዊ ፍትህና ተጠያቂነት እንደሆነ አጽንዖት ሰጥተው ይሰራሉ።*

*በዩኔስኮ የታተመ ‹ስቶሪ ቤዝን-ኢንኳየሪ› የተሰኘ የምርመራ ጋዜጠኝነት መመሪያ መጽሐፍ፣ የምርመራ ዘገባን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል። ‹‹የምርመራ ጋዜጠኝነት ኃይል ባለው ሥልጣን ሆነ ተብሎ አልያም በድንገት በእውነታዎች መደበላለቅና ለመረዳት ግልጽ ባልሆኑ ሁኔታዎች የተደበቁ ጉዳዮችን ለሕዝብ መግለጥን ያካትታል። በምስጢር የተያዙ እንዲሁም በግልጽ የሚገኙ ምንጮችንና ሰነዶችን መጠቀምንም ይጠይቃል።›› በተጓዳኝ የ‹ደች- ፍሌሚሽ› የምርመራ ጋዜጠኝነት ማኅበር (VVOJ) የምርመራ ዘገባን በቀላሉ ‹ወሳኝ እና ጥልቀት ያለው ጋዜጠኝነት› ሲልም ይተረጉመዋል።*

*በምርመራ ጋዜጠኝነት ከፍተኛ ሽልማቶችን ያገኙ ዘገባዎች፣ ሙያው ምን ያህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለ ጥናታዊ ምርምርና አዘጋገብ እንደሚፈልግ ማሳያ ናቸው። እነዚህም የተዘረፈ የሕዝብ ገንዘብ፣ ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም፣ የአካባቢ ብክለት፣ የጤና ዘርፍ ላይ ያሉ አሳፋሪ ጥፋቶችንና መሰል ሌሎች ጉዳዮችን የሚከተሉ ጥልቀት ባለው መልኩ በጥንቃቄ የተሠሩ ምርመራዎች ናቸው።*

*በሙያው አንጋፋ የሆኑ አሠልጣኞች እንደሚሉት፣ ምርጥ የሚባል የምርመራ ጋዜጠኝነት በጥንቃቄ የተመራ፣ ከመጀመሪያ ደረጃ ምንጭ የተገኙ መረጃዎች ላይ መሠረቱን የጣለ፣ መላ ምት ያለውና ያንንም የሚፈትሽ እንዲሁም ማስረጃዎችን በተደጋጋሚ ማጣራትን የሚያካትት ነው። መዝገበ ቃላቱም ‹ምርመራ› የሚለውን ቃል ‹ሥልታዊ ምርምር› ሲል ይተረጉመዋል። ይህም በአንድ ቀን ወይም በኹለት ቀን ተሠርቶ የሚጠናቀቅ አይደለም፤ ሰፊ ጊዜን ይፈልጋል።*

*በእንግሊዝ ሀገር ከጋዜጠኝነት የስራ መደቦች ውስጥ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው የስራ ዘርፍ ነው። ዩኒቨርሲቲ ገብቶ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ለመማር ከፍተኛ ውጤት ማምጣት የግድ ነው። መገናኛ ብዙኃን አራተኛ መንግስት መሆናቸውን የተቀበሉት ሀገሮች የምርመራ ጋዜጠኝነትን በዚህ ልክ እንዲሰፋፉ እየሰሩ ነው።*

**አዲስ ዘመን፤- የምርመራ ጋዜጠኝነት ከሌላው የጋዜጠኝነት በምን ይለያል?**

**አቶ መኮንን፤-** *የምርመራ ጋዜጠኝነት ጋዜጠኛው ያስብና አንድ ፕሮጀክት ይነድፋል፤ ይሄን ፕሮጀክት እንደ እራሱ ጉዳይ በመያዝ ጥናት ይሠራል። በጥናቱ ምንን ይይዛል? ምን ተፈጠረ? ማን ፈጠረው? ለምን ተፈጠረ? እንዴት ተፈጠረ? ለሚሉት ጥያቄዎች በሙሉ መልስ ይሰጣል። የምርመራ ጋዜጠኝነት ይሔ ነው።*

*አንድ ሰው የምርመራ ጋዜጠኝነትን ሰርቶ ማንም አያቀርብለትም፤ የሚያቀርበው ራሱ ነው። የሚፈጀው ጊዜም ከወራት እስከ አመታት ሊሆን ይችላል። ሁሉም ጋዜጠኝነት የራሱ አላማ ቢኖረውም የምርመራ ጋዜጠኝነት አንድ የትኩረት አቅጣጫ ላይ በመመሥረት የሚሠራ የጋዜጠኝነት ከፍል ነው። ጥልቅ የሆነ መረጃን የያዘ፤ ለማንም ያላዳላ የጋዜጠኝነት ዘርፍ ነው።*

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ ካልዎት ሰፊ የጋዜጠኝነት ልምድ አኳያ የሀገራችንን የምርመራ ጋዜጠኝነት እንዴት ያዩታል?**

**አቶ መኮንን፤-** *ወደ ሀገራችን ስንመጣ ጋዜጠኝነት በኢትዮጵያ በቂ ትኩረት እየተሰጠው አይደለም። ሁሉም ሰው እየተነሳ ጋዜጠኛ የሚሆንበት አግባብ አለ። ማንም ሰው በሆነ ዘርፍ ዲግሪ ካለው ከየትም ተነስቶ ጋዜጠኛ መሆን ይችላል። ይህ ደግሞ እጅግ አደገኛ ነው። አንድ ጋዜጠኛ ጋዜጠኛ ከመሆኑ በፊት*



ፎቶ፡ አሸናፊ ጉደታ

*መታነፅ አለበት። በትምህርት የጋዜጠኝነት ስነምግባርን መያዝ አለበት። የጋዜጠኝነት ስራ ምን እንደሚፈልግ ጋዜጠኛው ከትምህርት ማግኘት አለበት።*

*ከእንግሊዝ ሀገር የአርትስ ቴሌቪዥን መስራች በመሆን ለመስራት መጥቼ እያለ የታዘበኩት ብቃት ያለው ሰራተኛ ማግኘት እጅግ ፈታኝ እንደሆነ ነው። ጋዜጠኞችን ለመቅጠር የቀረበውን ፈተና ማለፍ አይደለም መሞከር የከበዳቸው ልጆች ነበሩ፤ እንደ ምንም አስልጥነን ስራ ውስጥ ከገቡ በኋላም በግል የፖለቲካ አመለካከት የሚፈጥሩት ሽኩቻ ስራቸውን ይገድልባቸው ነበር።*

*የቴሌቪዥን ባለቤት በመሆን ገንዘብ ስላወጡ ራሳቸውን እንደ ቴሌቪዥን አስተዳዳሪ የሚያስቡ ሰዎች አሉ። ሀገር ውስጥ ከመጣሁ ሁለት ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ላይ ሠርቻለሁ። በቲቪ ጣቢያዎቹ በጣም የሚያሳዝን ቆይታ ነበረኝ። ይህን ስል እድሉን አግኝቼ ሀገር ውስጥ ያለውን ሚዲያ እንድተዋወቅ ላደረጉኝ ሰዎች ምስጋና ቢስ እየሆንኩ አይደለም። መንግስትም ሆነ ባለሀብቶች ገንዘባቸውን አውጥተው ሙያውን ለባለሙያው መስጠት አለባቸው።*

*ሀገሪቱ መቀየር ያለባት በርካታ ጉዳይ አላት። የፖለቲካ ወገንተኝነቱ ከሚዲያው መውጣት አለበት። የትምህርት ካሪኩለሙም የጋዜጠኝነት ትምህርት ላይ በቂ ትኩረት መስጠት አለበት።*

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ጊዜ ጋዜጠኝነት ከተለያዩ ፈተናዎች ጋር ይነሳል፤ እርስዎ የገጠሞት ነገር ነበር? ከገጠምዎትስ እንዴት አለፉት?**

**አቶ መኮንን፤-** *እኔ ዶክመንተሪ ፊልሞችን እሰራለሁ። እዚህ ላይ ለፊልም ቀረፃ በጣም ገጠራማ የሆኑ የአፍሪካ መሬቶችን ረግጫለሁ። ከከተማ ሲወጣ ጫካ ውስጥ ሲኬድ የሚገጥሙ የተለያዩ ችግሮች ይኖራሉ። በጋዜጠኝነት ግን እንደ እድል ሆኖ ምንም አይነት ችግር ሳይገጥመኝ ሥራዬን ለዓመታት አከናውኛለሁ።*

**አዲስ ዘመን፤- አሁን ባለንበት የሚዲያ ዘመን በሀገራችን የምርመራ ጋዜጠኝነት እየተተገበረ ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ መኮንን፡-** *እንዳየሁት ከሆነ ከበርካታ ጋዜጠኞች ጋር ስወያይ እንደታዘብኩት በተለይም ወጣት ጋዜጠኞች ላይ መነሳሳት ይታያል። የምርመራ ጋዜጠኝነት እየተተገበረ ነው ወይ ለሚለው ጥያቄ ግን መልሴ ‹‹ አይደለም የሚል ነው።›› የምርመራ ጋዜጠኝነት ማንኛውም ጋዜጠኝነት በተቀመጠለት የስነ ምግባር ሁኔታ እየተተገበረ ነው ለማለት አልደፈርም።*

*የጋዜጠኝነት ትምህርት በአግባቡ ተማሪዎች ማግኘት የሚጠበቅባቸውን እውቀት መጨበጥ እንዲችሉ የሚያደርግ ትምህርት ያስፈልጋል። የምርመራ ጋዜጠኝነትም ራሱን የቻለ ኮርስ ሆኖ ለብቻው መሰጠት ይኖርበታል። ይህም የጋዜጠኝነት ልምምዱ ከፍ እንዲል ያደርጋል።*

*በስራ ደረጃ ግን የተለያዩ ሙከራዎች ቢኖርም በምርመራ ጋዜጠኝነት መርህ የተመራ ስራ ተሰርቷል ለማለት አያስደፍርም። በአብዛኛው የሰውን ሮሮ በመስማት የሚሰሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ የሚሰሩ ስራዎች አሉ። እውቀቱ አለ፤ ፍላጎቱ አለ፤ መንግስት የበለጠ ትኩረት ቢሰጠው ውጤታማ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

የሚሆን መስከ ነው።

**አዲስ ዘመን፤- በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ትምህርትና ስራ የተለያየ መሆኑን በርካታ ጋዜጠኞች ይናገራሉ፤ ትምህርቱና ሥራው እንዲጣጣም ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አቶ መኮንን፤-** የጋዜጠኝነት ትምህርት በራሱ በጣም ደስ የሚል ከዩኒቨርስቲ ወጥተው በተግባር እስኪገልጡት የሚቸኩሉበት አይነት ነው። ከዩኒቨርሲቲ ይዘው የወጡትን እውቀት በተግባር ለመግለፅ ከራሱ ከጋዜጠኛው የበለጠ ማንም ሀላፊነት ሊወስድ አይገባም። በተቻለ መጠን መመሪያዎችን ተከትሎ ለመስራት መጣር የጋዜጠኛው ሀላፊነት ነው።

ምንም እንኳን የተቋማቱ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ቢወስነውም ጋዜጠኛው በራሱ ጥረት ይህ እንዲቀየር ማድረግ ይገባዋል። ሀገሪቱ ውስጥም ለጋዜጠኞች ክብር መስጠት አለበት። እንግሊዝ ሀገር ጋዜጠኛ ታወቂ ግለሰብ ነው። ከፊልም አክተሮች እኩል የሚታይ ነው። እዚህ ሀገር ግን ክብር ሲሰጠው አይታይም።

መንግስት ነፃና ገለልተኛ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን እንዲኖሩ እድል ሊሰጥ ይገባል። ነፃና ገለልተኛ ሲባል ግን ብሄራዊ ጥቅምን ባከበረ መልኩ መሆን አለበት። ምንም እንኳን የመናገር ነፃነት ያለገደብ የሆነበት ሀገር ኖሬ ብመጣም እንኳን ለአንድ ማህበረሰብ ነፃና ገለልተኛ እሆናለሁ ተብሎ ማህበረሰብን የሚጎዳ የሀገር ሉዓላዊነትን የሚፃረር ተግባር መከናወን አለበት ብዬ አላምን።

ስለዚህ መንግስትም፤ ማህበረሰቡም፤ ጋዜጠኞችም ማህበረሰቡን በመረዳት የህዝብን ጥቅም ባስጠበቀ የሀገር ሉዓላዊነትን ያከበረ በሆነ መልኩ ነፃና ገለልተኛ፤ አድሎ የሌለበት የሚዲያ ተቋም እንዲሆን ግን የሁሉም ጥረት ይጠይቃል።

**አዲስ ዘመን፤- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የምርመራ ጋዜጠኝነት ሲሰራ እንደሚገባ ሲናገሩ ይሰማል፤ አሁን በሀገራችን የተንሰራፋው የመልካም አስተዳደር ችግር፤ በልሹ አሰራርን ለማስተካከል ይህ የጋዜጠኝነት መንገድ ሲያደርገው የሚችለው አስተዋፅኦ እንዴት ይታያል?**

**አቶ መኮንን፤-** ጠቅላይ ሚኒስትሩ እየገነቡ ያሉት ተቋም ነው። ሀገሪቱ በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ውስጥ ሆና ተቋም እየሰሩ ነው። ይህ ንግግራቸው ለመገናኛ ብዙኃኑ እድገት፤ አራተኛው መንግስት የመገነባበት መንገድ እንዲኖር የሚፈለግ መሆኑን የሚያሳይ ነው። አሁን በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ተቋማት በሙሉ ከሙስና የፀዱ እንዲሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እየሰሩ ነው።

ሙስናን ለመዋጋት ከምርመራ ጋዜጠኝነት የበለጠ መድሃኒት አይገኝም። በሀገሪቱ ብልሹ አሰራር ውስጥ የተገኙ፤ በሙስና የተያዙ፤ ተይዘው ምን እንደደረሰባቸው ማሳየት ዳግም ሙስና እንዳይፈፀም ያደርገዋል። የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን በተቀናጀ ሁኔታ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ሊሰሩ ይገባል የሚባለው ለዚህም ነው።

ነገር ግን በቂ ስልጠና ለጋዜጠኞች መስጠት አለበት። ሙያው ጥንቃቄን የሚጠይቅ ስለሆነ ሙያተኛው ምን አይነት መንገዶችን መሄድ እንደሚኖርበት፤ በቂ ከህሎት ያለው የራሱ ቡድን ተዋቅሮ በሰርዓት መሰራት ይኖርበታል። መንግስትም ለአራተኛው መንግስት ምስረታ ማለትም ለመገናኛ ብዙኃኑ እድገት ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፤- የምርመራ ጋዜጠኝነት ለአንድ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ መሻሻል ምን አስተዋፅኦ ይኖረዋል?**

**አቶ መኮንን፤-** ለአንድ ሀገር የምርመራ ጋዜጠኝነት እጅግ ጠቃሚ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትኩረት የሰጡበት ዋና ምክንያት ይሔ ነው። ህዝቡ የሚዲያን ጥቅም መረዳት አለበት። መንግስትም በንቃት ይህን ዘርፍ መገንባትም ሆነ መደገፉ የሀገር ስጋት የሆኑ ጉዳዮች ባሉበት እንዲቀሩ ያደርጋቸዋል። የማህበረሰብ ሰንኮፍን ለመነቀስ፤ ለሀገር እድገት ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን አጥርቶ ሀገር እንደ ሀገር እንዲቀጥል ለማድረግ ከምርመራ ጋዜጠኝነት የላቀ አመራጭ የለም።

በእንግሊዝ ሀገር የሚኖር የእግር ኳስ ደጋፊ አንድ ቡድን፤ የአውሮፓ ሻምፒዮንን እየተከተለ በመዞር ሁከት ይፈጥራል። ይህ ቡድን የሚያደርጋቸው ነገሮች በሀገር ገፅታ ላይ ጥላ የጣለ ኢኮኖሚውንም ባልተገባ መንገድ ያደቀቀ ነበር። አንድ ጋዜጠኛ ፑሊጋንስ እየተባሉ ከሚጠሩት ከደጋፊዎች ጋር በመቀላቀል ይህን ቡድን የሚመሩ አካላት እነማን እንደሆኑ በማጋለጥ



የምርመራ ጋዜጠኝነት ምን ያህል ዋጋ ተከፍሎበት ችግሮችን እንደሚነቀሱ ለመመልከት ችለናል።

በዚህም ያንን መረጃ የሚያስተላልፈው መገናኛ ብዙኃን የተመልካች ቁጥሩን ከፍ አድርጓል። ሌላው ደግሞ ህዝብ እውነትን በመመልከት መንግስትና ህዝብ መካከል ያለውን ተአማኒነት ያረጋግጣል። ስለዚህ የሀገርን ችግሮች ለመቅረፍ ከዚህ የበለጠ አማራጭ የለም እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፤- ጋዜጠኞች ካላቸው አቅም፣ ለሙያው ከሚሰጡት ክብርና ቁርጠኝነት ጋር ተያይዞ ሙያውን በትክክል ሲወጡት ይችላሉ ? ካልሆነስ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አቶ መኮንን፤-** ለጋዜጠኝነት ትምህርት ከሚሰጠው ትኩረት አንስቶ በርካታ ችግሮች ይታዩኛል። በሀገሪቱ ትላልቅ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የሚመደቡት እንደ ህክምና ዶክተር፤ ኢንጂነር ያሉ ትምህርቶች ላይ ነው። ደረጃ በደረጃ ሌሎቹ የትምህርት ዘርፎች ላይ ተመድበው ሲያልቁ ዝቅ ያለ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ለጋዜጠኝነት የትምህርት ዘርፍ እንዲመደቡ ይደረጋል። ይህ ደግሞ ለዘርፉ ምንም አይነት ክብር እንዳልተሰጠ የሚመለከተው ነው። ሚዲያ አራተኛው መንግስት ከሆነ ዘርፍ በተገቢው መልኩ ከትምህርት ስርዓቱ ጀምሮ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

አንድ ጋዜጠኛ ጋዜጠኛ ሲሆን፤ ፖለቲከኛ ሳይሆን ጋዜጠኛ እንዲሆን መደረግ አለበት። ከአድሎ የፀዳ ጋዜጠኛ የሚሆነው በበቂ ሁኔታ ሥነ ምግባርን ተምሮ ሲወጣ ነው።

**አዲስ ዘመን፤- ከጋዜጠኝነት ሙያ ሥነ-ምግባር አንጻር ምን ሀሳብ አልዎት?**

**አቶ መኮንን፤-** የጋዜጠኝነት የሙያ ሥነ-ምግባር ዋና ዋና መርሆዎች አሉ። አንደኛው እውነትን መፈለግ (Seeking the Truth) እውነትን መዘገብ ማለት ከትክክለኛ ምንጭ የተገኘ መረጃ ላይ የራስ ሃሳብ ሳይጨምሩ ወይም ሳይቀንሱ ማቅረብ ማለት ነው። እውነትን ለህዝብ ለማቅረብ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ድፍረትም ይጠይቃል። ጋዜጠኛ ለእውነት ሲል ዋጋ ይከፍላል። ድፍረትና ብቃት ወሳኝ መሣሪያዎች ናቸው። ጋዜጠኛው የሚያውቀውና የመረጃ ምንጮች የሚሰጡት መረጃ ባይጣጣም ከሶስተኛ ወገን አጣርቶ እውነቱን መዘገብ ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛው ትክክለኛነት እና ህጋዊነት ነው። ዜናው ትክክለኛ መሆን ስላለበት የዜናውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የዜና ምንጩን ማለትም የመሥሪያ ቤቱን ወይም የተቋሙን ትክክለኛ ስም፣ ዜና የሰጠውን ሰው ስም፣ የኃላፊነት ደረጃ በትክክል መዝግቦ መያዝ አለበት። ትክክለኛነቱ ከመረጃው ምንጭ እስከ መልዕክቱ ጭብጥ ያለውን ያጠቃልላል። ይሄንን መተላለፍ የሙያውን ሥነ-ምግባር እንዳለ ማክበር ይቆጠራል፡፡

ሶስተኛው ፍትሃዊነትና ሚዛናዊነት (Fairness and Balance) ፍትሃዊነት የአንድን ወገን ብቻ ማስተላለፍ ሳይሆን የሁለት ወገኖችን ሃሳብና አመለካከት ማስተላለፍ ይጠይቃል። በእኩል ዓይን ማየት ፍትሃዊነት ነው። ከቋንቋ አጠቃቀምና የፎቶግራፍ አጠቃቀምን ጨምሮ ለዜናው የተሰጠው አንቀፅ መጠንና ጊዜ ፍትሃዊነትን ያሳያል። ሚዛናዊነት ደግሞ ስለሁለቱ ወገኖች ስንዘግብ አንዱን የሚያጥላላ፤ ሌላውን የሚያወድስ፤ ወይም አንዱን ጭራቅ ሌላውን ቅዱስ አለማድረግን ይመለከታል፡፡

አራተኛው ገለልተኝነት ነው። አንዱን ወገን ለመጥቀምና ሌላውን ለመጉዳት መሥራት አይፈቀድም። ዜናና የግል አስተያየት መለያየት አለባቸው። በዜና ውስጥ የግል አስተያየትን መስጠት ፈፅሞ አይፈቀድም፤ አስተያየትን ለህዝቡ መተው ይሻላል፡፡

ሌላው ስም ማጥፋትና ትክክለኛ ያልሆነ ገጽታ (Defamation) ነው። ስም ማጥፋት የሰዎችን መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፍ ነገር መፃፍ/ መዘገብ በሥነ-ምግባር የተከለከለ ነው። ያልሆነውን ነገር እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ስም ማጥፋት ነው። መልካም ስምንና ዝናን ማጥፋት ወንጀል ነው። ይህን መርህ ያልተማረ፣ ያላወቀ እና የማይተገብር ጋዜጠኛ ደግሞ ጋዜጠኛ ሲሆን እጅግ አደገኛ ይሆናል። በአጠቃላይ ጋዜጠኞች የጥልቅ እውቀት ባለቤት መሆን አለባቸው እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፤- በመጨረሻ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ምን እየሰሩ ነው?**

**አቶ መኮንን፤-** ባለፈው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ላይ አንድ ሀሳብ አቅርበው ነበር። አፍሪካ የራሷ ሚዲያ ያስፈልጋታል፤ ምክንያቱም የአፍሪካን ታሪክ የውጭ የመገናኛ ብዙኃን በፈለጉት መልኩ እየተናገሩት ነው። ይህንን ሀሳብ ከሰማሁ በኋላ የአፍሪካን ሚዲያ ፕሮጀክት ይዤ መጥቻለሁ።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረትን እንደ መመስረቷ ከፊት ሆና የአፍሪካ ሚዲያን ለማቋቋም መብት ይኖራታል። ይህን በማለት ከቢቢሲ ተቃራኒ ከቆሙት

> **መንግስት ነፃና ገለልተኛ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን እንዲኖሩ እድል ሊሰጥ ይገባል። ነፃና ገለልተኛ ሲባል ግን ብሄራዊ ጥቅምን ባከበረ መልኩ መሆን አለበት። ምንም እንኳን የመናገር ነፃነት ያለገደብ የሆነበት ሀገር ኖሬ ብመጣም እንኳን ለአንድ ማህበረሰብ ነፃና ገለልተኛ እሆናለሁ ተብሎ ማህበረሰብን የሚጎዳ የሀገር ሉዓላዊነትን የሚፃረር ተግባር መከናወን አለበት ብዬ አላምን**

ተቋማት ጋር፤ ፓይኒሰት እና ላቲኖ ፕሮዳክሽን ከሚባሉ ተቋማት ጋር ቅንጅት ካምፓኒ በማቋቋም ፕሮጀክቱን ይዤ ሀገር ውስጥ መጥቻለሁ።

አፍሪካ ካሉ ከተለያዩ መንግስታትና ከተለያዩ ታላላቅ መገናኛ ብዙኃን ጋር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ግንኙነት እየፈጠርን እንገኛለን። ይህን ፕሮጀክት በተጨማሪ የጋዜጠኝነት ስነ ምግባርና አተገባባር ላይ ትኩረት በመስጠት እየሰራሁ እገኛለሁ።

**አዲስ ዘመን፤- ውድ ጊዜዎን ሰውተው ረጅሙን የጋዜጠኝነት ልምዶን ስላካፈሉን በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስም የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።**

**አቶ መኮንን፤-** እኔም ሀሳብህ ይጠቅማል ብላችሁ ልታናግሩኝ ስለወደዳችሁ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## አሳሳቢ የሆነው የህጻናት ካንሰር

**እፀገነት አክሊሉ**

ልጁ ገና የሶስት ዓመት ህጻን ሆና በተደጋጋሚ እየታመመች ስታስቸግረው ወደ ህክምና ተቋም ይዟት ይሄዳል፤ ህጻኗ የደም ካንሰር እንዳለባትና ወደ አዲስ አበባ ከተማ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄዳ ካልታከመች ችግሩ እንደሚከፋ ይነገረዋል። እሱም ያለውን ንብረት ሽጦ ጥሪቱን ይዞ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ያቀናል፡፡ ሆኖም ከወሎ አዲስ አበባ ከተማ ከመጣ እንደ ቀልድ ሶስት ዓመታት ሆነውታል።

ስሙን መግለጽ ያልፈለገው አባት ምንም እንኳን አዲስ አበባ ሲገባ ለአንድ ቀን እንኳን ተጠልሎ የሚያርፍበት ዘመድ አልነበረውም፡፡ ቢሆንም ልጁን አሳክሞ ለማዳን ሲል ያለችውን ቋጥሮ ከመምጣት አልቦዘነም። እንደተባለው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ደርሶ ልጁን አስመረመረ፤ ህጻኗ ልጁም የደም ካንሰር ታማሚ መሆኗንና ሰፋ ያለ የህክምና ክትትል እንደሚያስፈልጋት ተነገረው።

የሰማው ነገር ለእሱም ሆነ ለያዛት ህጻን ልጁ ከባድ ቢሆንም አሳክሞ የማዳን ህልሙ ግን ከውስጡ አልጠፋም፤ እስከ ጥቂት ጊዜ ድረስም ያለችውን ለአልጋና ለምግብ እየከፈለ ልጁን በቀጠሯዋ ቀን ሀኪም ቤት እያመላለሰ ታገለ፤ ነገር ግን የህክምናው አስቸጋሪነት፤ ከልጅቷ ሁኔታ፤ እሱም በኪሱ ያለው ገንዝብ እያለቀ መሄዱ ሃሳብ ላይ ጣለው። ጭንቀቱን ይዞ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ሲንከራተት ለእሱም ሆነ ለልጁ ታላቅ ነገርን ሊያደርጉ ያሰቡ ቅን ኢትዮጵያውያንን አገኘ።

በዚህም ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድሁድ ካንሰር ድርጅት (ታፕኮ) እኛ እናግዝሃለን መጠለያም ምግብም አንዳንድ የህክምና ወጪህንም እንሸፍናለን ልጅህም ትድናለች የሚል ተስፋን ሲሰጡት ማመን ተቸግሮ እንደነበር ይናገራል።

አባትና ልጅም በድርጅቱ ማደሪያ ምግብ እንዲሁም ወደ ሆስፒታል ለመመላለስ የሚያስችል ትራንስፖርትና አንዳንድ የህክምና ወጪዎቻቸው ተሸፍነው ልጁ ህክምናውን መከታተል እሱም ከሀሳብ መዳን ቻለ።

የሕፃኗ አባት አሁን የሚያስጨንቀው ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት ትቷቸው የመጡት ቤተሰቦቹ ሁኔታ ነው። በቅርብ ሆኖ የአባትነት ሚናውን አለመወጣቱ ያሳዝነዋል። መለስ ሲል ደግሞ ታማሚዋ ልጁ አሁን ላይ ያለችበት የማገገም ሁኔታ ያስደስተዋል። ይህ ሁሉ ነገር አልፎ ደግሞ ልጁን በጤና ይዞ አገሩ በመግባት ከቤተሰቦቹ እንደሚቀላቀል ሲያስብ ተስፋው ያብባል።

“አዲስ ተስፋ ባይኖር ልጄን እንኳን ላሳክማት ላስበውም እንኳን እቸገር ነበር፤ አንድ ቀን ማደሩም ከባድ ይሆንብኛል። መኝታ፣ ምግብ፣ መድሃኒትን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎች እየተደረጉልን ነው፤ በእውነት እንዲህ ያሉ ደጋጎች ሊመሰገኑ ይገባል” ይላል።

ወጣት ወርቅዬ መልካሙ በኩላሊት ካንሰር የታመመች ትንሽ እህቷን ለማሳከም ከራያ ቆቦ ነው የመጣችው። ወርቅዬ የአስረኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ እህቴን አድናለሁ ብላ ከአገሯ ከወጣችም ወራቶች ተቆጥረዋል። ወርቅዬም አዲስ አበባ የምታርፍበትና የምታውቀው አንድም ሰው ባይኖርም እህቴን ማዳን አለብኝ ብላ ቤተሰቦቿ የሰጧትን ይዛ ነበር የመጣችው።

እሷም በተመሳሳይ በጥቁር አንበሳ ጠቋሚነት ወደተስፋ አዲስ ድርጅት በመምጣት ለእሷም ለእህቷም ማረፊያ ምግብ አግኝታ፤ በቀጠሮዋ ቀን እህቷን ይዛ ሄዳ አሳክማ እየመጣች ነው። “ ይህ ትልቅ እድል ነው፤ የምትለው ወርቅዬ እንደዚህ አይነት ድርጅት ባይኖር ኖሮ ህክምናውን ለመከታተል አቅማችን አይችልም ነበር። እህቴም እስከ አሁን ትጎዳብኝ ነበር” በማለት ሁኔታውን ትናገራለች።

ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድሁድ ካንሰር ድርጅት (ታፕኮ) ተርፋማ ያልሆነ ግብረ ሰናይ ድርጅት ሲሆን ህጋዊ ህልውና ያለውና ከተመሰረተ ከ10 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ነው። ድርጅቱ የተመሰረተው በወላጆችና አላማውን በሚደግፉ ግለሰቦች ነው፡፡ የካንሰር ታማሚ ሕጻናት በሆስፒታል ቆይታቸው በቂ ህክምናና እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠር በቀጣይነት ህክምናቸውን እንዲከታተሉ ጥረት የሚያደርግ ድርጅት ነው።

የማህበራዊ ዘርፍ ሰራተኛ የሆኑት ፋንቱ ሃዋዝ ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድሁድ ካንሰር ድርጅት በወላጆች የተመሰረተና የህጻናት ካንሰር ላይ የሚሰራ እንደመሆኑ እስከ አሁንም በርካታ ህመሙ ያለባቸውን ህጻናት በተለያዩ መንገዶች እያገዘና እየደገፈ መገኘቱን ያወሳሉ።

ድርጅቱ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በጅማ፣ በጎንደር እንዲሁም በመቀሌ ቅርንጫፎችን በመክፈት ህመሙ ያለባቸው ህጻናት በወቅቱ ህክምና እንዲያገኙ በማድረግ ለወላጆቻቸው የምክርና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች ላይ መስጠቱንም ያነሳሉ።



ፋንቱ ሃዋዝ

እንደ ፋንቱ ማብራርያ ድርጅቱ ከጥቁር አንበሳና ከጳውሎስ ሆስፒታሎች ጋር በጥምረት የሚሰራ ሲሆን ህመሙ ያለባቸውንና መረዳት የሚያስፈልጋቸውን ህጻናትም ከእነዚህ ሆስፒታሎች የሚላኩ ናቸው። በመረጣው በኩልም በሆስፒታሎቹ ውስጥ የሚሰሩ የድርጅቱ ሰራተኞች መኖራቸውን የሚናገሩት ፋንቱ በዳታና በስነ ልቦና አማካሪነት እየሰሩ ህጻናቱም የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እየለዩ ወደ ድርጅቱ እንደሚልኩም ይናገራሉ።

በተለይም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ታማሚ ህጻናቱ እየተመላለሱ ህክምናቸውን በሚያገኙበት ማዕከል ላይ የምግብ አገልግሎትና የስነ ልቦና ማማከር ስራ እንደሚሰራ ገልጸው፤ እነዚህ ባለሙያዎች ደግሞ የልጆቹንና የወላጆቻቸውን ሁኔታ በማየት እንዲሁም ከህክምና ባለሙያዎቹ ጋር በመነጋገር እገዛ ያስፈልጋቸዋል ሲሉ ማስረጃ በማስያዝ ወደ ድርጅቱ ይልኳቸዋል። በድርጅቱ በኩልም አስፈላጊው ድጋፍ እንዲያገኙ ይሆናል።

“እኛ በአብዛኛው የክልል ታማሚዎች ላይ ነው ትኩረት አድርገን የምንሰራው። ጎን ለጎን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እየኖሩ የአቅም ውስንነት ያለባቸውንና የካንሰር ታማሚ ህጻን ያላቸውን ሰዎች እናግዛለን። እዚህ ላይ ትኩረታችንን ክልሎች ላይ የማድረጋችን ዋናው ምክንያት እነዚህ ሰዎች ካሉበት አገር መጥተው አንዴ ህክምና አግኝተው ወደ አገራቸው ሊሄዱ አልያም ደግሞ ተደጋጋሚ ቀጠሮዎች ሊሰጧቸው ይችላሉ፤ በዚህን ጊዜ ብዙዎቹ አቅም ስለማይኖራቸው አገራቸውም ላይ ቤተሰብ መበተን ስላለባቸው አንዴ ከሄዱ ዳግም አይመጡም። ይህ ደግሞ ህክምናው እንዲቋረጥ ያደርጋል። እኛም ይህንን የመከላከል ስራን ነው የምንሰራው” ይላሉ።

በመሆኑም ከሆስፒታል በህክምና ባለሙያዎች እንዲሁም በእኛ ሰራተኞች የተላኩልንን ህመምተኛ ህጻንና ወላጆቻቸውን በመቀበል ፎርም አስሞልተን የመጠለያ፣ የምግብ፣ ንጽህና እንዲጠብቁ የማድረግ አብዛኞቹ ደግሞ ከቤታቸው ሲወጡ ቶሎ እንመለሳለን የሚል ሀሳብ ስለሚይዙ ቅያሪ ልብስ አይኖራቸውምና እሱን የመሸፈን ፣ በቀጠሯቸው ቀንም ታክሲ በመኮናተር ህክምናቸው ጋር ደርሰው የሚመጡበትን ሁኔታ የማመቻቸት ስራ እንሰራለን ይላሉ።

ህጻናቱም ሆኑ ወላጆቻቸው ቀጠሮ ከሌላቸው ሆስፒታል አይሄዱም በመሆኑ በድርጅቱ ውስጥ ሲቀመጡ ይበልጥ የተረጂነት ስሜት እንዳያዳብሩ ህጻናቱ ትምህርት አቋርጠው ከሆነ እሱን እንዲያስታውሱ የሚያደርግ ትምህርት፤ ያልጀመሩትም ቢሆኑ ከፊደሎች ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ህመማቸውን እንዳያስታውሱ የልጅነት ጊዜ እንዲኖራቸው ተጫወትኩ ጓደኛ ኖረኝ የሚለውን ነገር እንዲያዳብሩ በመጫወቻ ክፍላቸው የተለያዩ ጨዋታዎች እንዲጫወቱ ፣ ስዕሎችን እንዲስሉ እርስ በእርሳቸው ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራቸው የማድረግ ስራ እየተሰራ መሆኑን ይናገራሉ ።

ወላጆቻቸውም ቢሆኑ በሚችሉት መጠን የእጅ ስራዎችን እየሰሩ ራሳቸውን እንዲደግፉ የማድረግ ስራ እንደሚሰራም ያክላሉ።

ድርጅቱ ወላጆችን በቀን ሶሰት ጊዜ ህጻናቱ ደግሞ በቀን አምስት ጊዜ ይመግባል። በተለይም ህጻናቱ ፕሮቲን ቅባት ያላቸውና ሌሎች ሰውነት ገንቢና በሽታ ተከላካይ ምግቦችን እንዲያገኙ ያደረጋል።

ድርጅቱ በአፍንጮ በር በኩል ባለው የጥቁር አንበሳ ቅርንጫፍ ማዕከል ላይ የካንሰር ህክምናውን ለሚከታተሉ ህጻናት ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት እንቁላል፣ ዳቦና ወተት በማቅረብ የድርጅቱን ህጻናት ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ህክምን ሊከታተሉ ለመጡና የፈለጉ ህጻናት በሙሉ ቁርስ ያበላል። በተጨማሪም የምሳ ሰዓትም ላይ በተመሳሳይ ምሳ እንዲያገኙ እንደሚደረግም ይናገራሉ።

በሌላ በኩልም አብዛኛው የካንሰር ታማሚ ህጻናት የሚታከሙበትን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታልን እያገዘን ነው በምንችለው አቅም የልጆች ህክምን ክፍሎችና መኝታ ክፍሎች መታደስ ሲፈልጉ እናድሳለን፣ ባሉበት ሁኔታ ስዕል የመሳል ቀለም የመቀባት በጠቅላላው ሳቢ የማድረግ ስራ ይሰራል፤ አቅም ሲፈቅድና ለጋሽ አካላት ሲገኙ ደግሞ የጎደሉ የህክምን መሳሪያዎች እንዲሟሉ የማድረግ ስራም ይሰራል።

ድርጅቱ ድጋፍ የሚደረግላቸውን ህጻናትና የህክምና ቀጠሯቸው እንዳያልፍ ከፍ ያለ ጥንቃቄ እንደሚያደርግ ገልጸው ምንም እንኳን የራሱ የሆነ መኪና ባይኖረውም በቀጠሯቸው ቀን ታክሲ በመኮናተር አድርሶ የመመለስ ስርም እንደሚሰራ ይናገራሉ።

በሌላ በኩልም ህጻናት ይዘው እዚህ የተቀመጡ ወላጆች አገራቸው ላይ ሌሎች ልጆች፣ ቤተሰብ፣ ስራም አላቸው እናም ሁሉንም እኩል ማስኬድ እንዲችሉ በተለይም ልጆቹ የወር ቀጠሮ በሚሰጣቸው ጊዜ አገራቸው ደርሰው እንዲመጡ ድርጅቱ የትራንስፖርት ወጪያቸውን ይሸፍናል። እዚህ ላይ ግን ሰዎች ለእኔ ነው ብለው እንዲያስቡና ጥገኝነትንም አብዝተው እንዳይለማመዱ መመለሻ የትራንስፖርት ወጪያቸውን የሚችሉት ራሳቸው ናቸው።

“ ...... ሁሉም እንዲያወቅ የምፈልገው ድርጅቱ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥና አምስት ኪሎ ጥቁር አንበሳ ካንሰር ማዕከል ላይ የስነ ልቦና አማካሪዎችን ቀጥሮ በድርጅቱ ለሚታገዙት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ካንሰር ታማሚ ልጅ ላላቸው ቦታ የመምራት ፣ መድሃኒት የማገዝ ፣ እንዳይጨነቁ ምክር የመስጠት ድጋፎችን ያደርጋል” ይላሉ።

ድርጅቱ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ላይ አንዲት እናት ጓደኞቿን ይዛ ቡና ጠጡ እያለች ወላጆችንን በማወያየት የመሰረተችው ነው። ከዛ በኋላ ግን አሜሪካን አገር በኢትዮጵያዊ ልጅ ምክንያት የተመሰረተ ዘ- አዝላን የሚባል ፕሮጀክትን የመሰረቱት አሜሪካውያን ነርሶች ዶክተሮች ፕሮፌሰሮች ተሰባስበው ገንዘብ በመሰብሰብ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ይህንንም ድርጅት በጣም እያገዙ ይገኛሉ። በተጨማሪም አሜሪካን ካንሰር ሶሳይቲ ይረዳናል። በአገር ውስጥ ያሉ አቅም ያላቸው ግለሰቦች ካምፓኒዎች ብዙ ድጋፎችን ያደርጉልናል ብለውናል።

‹‹ለምሳሌ አሁን ላይ ትልቁን ችግራችን የሆነውን የመድሃኒት ወጪ የሚያግዘን የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት ነው›› ይላሉ፡፡ እንዳከሉት በጀት መድቦ የሚፈልጉትን መድሃኒት በሙሉ እያገዛላቸው ይገኛል ፤ ኢንተርናሽናል ክሊኒካል ላብራቶሪ ላለፉት ረጅም አመታት የላብራቶሪ ስራዎችን በነጻ ሰርቶላቸዋልም ፤ ውዳሴ ዳያግኖስቲክስ ማዕከል በግማሽ አልያም አንዳንዴ በነጻ ምርመራዎችን በመሥራት ያግዛቸዋል።

ፋንቱ እንደሚሉት እነዚህ ድርጅቶች በህክምናው በኩል መሟላት ያለባቸውን ያግዙ እንጂ ጠዋት ጠዋት በጥቁር አንበሳና አምስት ኪሎ ማዕከል የሚቀርበውን ቁርስ ሙልሙል ዳቦ በማቅረብ ለረጅም ዓመት አብሯቸው እየሰራ ነው፤ ሞዬ ቡና ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ልደት ምርቃትና ሌሎች ዝግጅቶችን በድርጅቱ ውስጥ በማክበር ያግዛል፤ በተነሳሽነት ምሳ እራት የሚያበሉ በርካታ ደጋጎች አሉ፤ ጤፍ፣ ወተት፣ ዘይት፣ ስጋ፣ እንቁላልና ሌሎችንም እያመጡ የሚሰጡ አሉ፤ ይህ በጣም የሚያስደስትና ሊበረታታ የሚገባው ነው። እንደዚህ ዓይነት ድጋፎች ባይኖሩ ደግሞ ድርጅቱም ባለው አቅም መቀጠል ይከብደዋል ባይ ናቸው።

ድርጅቱ እስከ 50 ህጻናት ከነወላጆቻቸው የሚያስተናግድ አቅም ያለው ሲሆን ቁጥሩ እንደ ሁኔታው ከፍም ዝቅም ሊል ይችላል፤ ምክንያቱም በረጅም ቀጠሮ አገራቸው የሚሄዱ ሊኖሩ ይችላሉ ሆስፒታል ይተኛሉ ዛሬ ላይ 40 ገደማ ህጻናት ከወላጆቻቸው ጋር ይገኛሉ። ድርጅቱ ከጀመረ ጀምሮ አገልግሎቱን አግኝተው የዳኑ ልጆች ግን ከ 2ሺ ይበልጣሉ።

የህጻናት ካንሰር ከአዋቂዎች ጋር ስናወዳድረው በተሻለ ሁኔታ የመዳን እድሉ ከፍ ያለ ነው፤ ብዙ የተደረጉ ጥናቶችም የሚያሳዩት ይህንን ነው። ነገር ግን በህብረተሰቡ ውስጥ ይድናል የሚለው ግንዛቤ ገና ስለሆነ ወደ ህክምና ቦታ የሚሄዱት ዘግይተው ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ የካንሰር ደረጃውን ከፍ ስለሚያደርገው ለማከምም ሆነ ለመዳን ብዙ ህክምናና ወጪን ይጠይቃል። በመሆኑም ግንዛቤ ላይ መስራቱ ገና ይቀረዋል የሚል ግምት አላቸው።

“..... አሁን ላይ ለህጻናት ካንሰር ህመም የተሰጠው ትኩረት ካለፉት ጊዜያት ጋር ሲነጻጸር መሻሻሎች ያሉት ነው። ዘ -አዝላን ፕሮጀክት ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሰራው ስራ ለምሳሌ ጳውሎስና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታሎች እያንዳንዳቸው ሁለትና ሶስት የህክምን ባለሙያዎች ኖሯቸዋል፤ ጅማ አንድ፣ ጎንደር አንድ፣ መቀሌ አንድ የካንሰር ስፔሻሊስቶች አሉ። ይህ በጣም ትልቅ ለውጥ ነው። አሁን ደግሞ እየተማሩ ያሉና በጥቂት ዓመታት ውስጥ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደስራው የሚቀላቀሉ በርካቶች አሉ” በማለት ይገልጻሉ።

በሌላ በኩልም ባለሙያዎችን ከማሰልጠን አልፎ ጤና ሚኒስተር ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት ራሱን የቻለ የስራ ዘርፍ በማድረግ ከእኛ ድርጅት ጋርም ጥሩ የስራ ግንኙነትን በመፍጠር አብሮ እየሰራ መሆኑ እኛንም የሚያበረታታና ለተሻለ ስራ የሚያነሳሳ ነው ብለዋል።

“50 ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሀምሳ ሰው ጌጡ” እንደሚባለው ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድሁድ ካንሰር ድርጅት የማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፎችን ለህጻናቱና ለወላጆቻቸው ያደርጋል። እኛስ ለእነዚህ ህጻናትና ወላጆች አለንላችሁ ብንላቸው መልካም ነው።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "የነፃ ገበያው ነፃ ሽፍትነት"

የሀገራችን የግብይት ሥርዓት ስሙ "ነፃ"፣ ባህርይው ባርነት፣ ተግባሩ ሽፍትነት መሆኑን በድፍረትና በአደባባይ የምንመሰክረው እኛ የእለት እንጀራ አሮብን ጦም ማደርን ባህል ያደረግን ዜጎች እንጂ በቁጥር እንቆቅልሽ የሚያማልሉን መንግሥታዊና ምሁራዊ እስታስቲክሶች አይደሉም። ርሃባችን የዳቦ እጦት ጠኔ ብቻ ሳይሆን የፍቅር ርሃቡም ተጨምሮ ስምና ትርጉም አልባ ክስተት ከሆነብን ሰነባብቷል።

"ምግብማ ሞልቷል አምላክ መች ነሳኝ፣
የፍቅር ርሃብ ነው እንዲህ ያከሳኝ።
ሁልጊዜ እበላለሁ ሆዴ መች ጎደለ
ፍቅራችን ብቻ ነው ያልተደላደለ። "

በማለት ያዜመው ነፍሰ ሄሩ ጥላሁን ገሠሠ ዛሬ በሕይወት ኖሮ "ይህንን የዜማ ግጥም በአስረቅራቂው ድምጽህ አንጎራጉርበት" ቢሉት "እጄን ለካቴና፤ እግሬን ለብረት ሰንሰለት" እሰጣለሁ በማለት ጨክኖ እምቢታውን ሳይገልጽ የሚቀር አይመስልም።

ምክንያቱም፡- ሌሎች ስንኞች እንኳን እንዳሉ ቢሆኑ፤ "ሁልጊዜ እበላለሁ ሆዴ መች ጎደለ" የሚለውን ስንኝ እንደነበረ አዜመዋለሁ ቢል ቁርሱን ጥሬ ቢቆረጥምም ለምሣና ለእራቱ ይቺንው አጥቶ ድፍት ብሎ የሚያድረው የሀገሬ አዳሜና ሔዋኔ ወፈ ሰማዩ ሕዝባችን በሰላማዊ ጥሪ ድምጻዊውን ለመቃወም አደባባዩን ማጥለቅለቁ አይቀርም። ለሠልፍ ለሠልፍማ እኛን ማን ብሎን! "ምግብማ ሞልቷል ወዘተ." የሚሉ ፉከራዎች ከእነ ጥላሁን ገሠሠ ጋር ሳይቀበሩ የቀሩ አይመስልም።

አንድ ኪሎ ሥጋ የአንድ ምስኪን ዜጋን የወር ደመወዝ ያህል ተቆርጦለት ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር በላይ ባሻቀበበት በዚህ ለጉድ በጎለተን ዘመን የተወለዱት ልጆቻችን፤

"ሞልቷል በሀገራችን የምግብ ዓይነቶች፣
አትክልትና ፍሬ የሥጋ ብልቶች"

የሚለውን ሙዚቃ በትዝታ እየተብከነከንን ስናንጎራጉር ቢሰሙን "በስብስቴ ዘመን የተረት ትዝታ የምንብከነከን" እየመሰላቸው ሳይሳለቁብን አይቀሩም።

"በንጉሡ ዘመን ተሸሞንምኖ በላስቲክ እየታሸገ በአሥር ሳንቲም ይሸጥ የነበረው የወንጂ ስኳር ይተዋወቅ የነበረው በመኪና እየተዞረ ሰዎች ገዝተው እንዲሞክሩት በልምምጭሽ ጭምር እየተለመኑ ነበር። በዘመነ ደርግም እንዲሁ ሀገሪቱን እያንገበገበ የነበረው ጦርነትና ድርቅ እያለ እንኳን የአንድ ኪሎ ስኳር ዋጋ ሁለት ብር ከአሥራ አምስት ሣንቲም ነበር። አንድ ኪሎ ጨውም በሃያ አምስት ሣንቲም ገዢ አልነበረውም።

አንድ ኪሎ ሥጋ በአምስት ብር፣ ሩዝ በተፈለገው መጠን ከሌላ ሸቀጥ ጋር በመጣያነት ያውም የአብዮት ጠባቂዎች ማስፈራሪያ ታክሎበት ጭምር ይሸጥ የነበረው በግዴታ ነበር…ወዘተ." እያልን ብናላዝን ልጆቻችን "እሺ ተረቱ አለቀ!?" ብለው ኩም አድርገው እንደሚያሳፍሩን አንጠራጠርም። ልጆቻችን ብቻም ሳይሆኑ ዘመንኞቹ የዛሬዎቹ ፖለቲከኞችም "በዱሮ በሬ ያረሰ የለም" እያሉ ሊያፌዙ እንደሚችሉ ቀልብያችን ይነግረናል።

ዛሬ ዛሬማ ባህርይው ያልሆነውን ገበያ በስም ብቻ "ነፃነት" አጎናጽፎ ከማሞካሸት ይልቅ ከባርነቱ ነፃ እንዲወጣ መዋጀት ቢቻል በእጅጉ በተሻለ ነበር። በባርነት የተያዘው በየጊዜው መንግሥት በሚያወጣቸው የይስሙላ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ተጠፍንጎ መሆኑን እንኳን እኛ የቤተሰብ ቀለብ አቅራቢ ወላጆች ቀርተን ከጡጦ ያልተላቀቁ ልጆቻችንም ቢሆኑ በደመ ነፍስም ቢሆን በሚገባ ይረዱት ይመስለናል።

እንዴት ቢሉ እኛ ወላጆች የኑሮ ውድነቱን ጫና መቋቋም ተስኖን ሌት ተቀን እንባችንን ስናፈስ እነሱም ጡጦ ጎደለብን ብለው እሪ እያሉ ሲያለቅሱ አብረን ስለምናላቅሳቸው አንድ ሀገራዊ ችግር እንዳለብን ሳይረዱ አይቀርም፤ ያውም በጨቅላ አእምሯቸው። ምናልባትም ጠባቂ መላእክቶቻቸው እውነቱን በሚገባቸው ቋንቋ ሹክ ሊሏቸው ይችሉ ይሆናል። ማን ያውቃል!

ለአባባሉ ይቅርታ ጠይቀን "ባሪያና ቃሪያ እንዳቃጠለ ይኖራል" የሚለውን የአበው አባባል "በነፃነት ስም ባርነት ለገባው የግብይት ሥርዓት" ብሂሉን ብንዋስ ጡንቸኞቹ "አትንኩን ባይ ሹሞቻችን" የሚቆጡን አይመስልም። ቢቆጡንስ ማን ያደምጣቸዋል፤ ምንስ የሞራል ብቃት ይኖራቸዋል።

የትናንቱን አንድ አብነት ብቻ እናስታውስ። ካስፈለገም ከትናንትናና ከትናንት ወዲያ ተሞክራችን ሰባት ጊዜ ሰባ የሚደርሱ መረጃዎችን ማቅረብ እንችላለን። ለምሳሌ፡- የመብል ዘይት ከመንግሥት እጅ እንደማይወጣ በሥልጣን የተበየነብን ውሳኔ ጭራሹኑ ችግሩን አባብሶ ምን ደረጃ ላይ እያደረሰን እንዳለ የምናየው ነው። ይህ መንግሥታዊ የኢኮኖሚ ቁጥጥር ሊፈረጅ የሚገባው "በነፃ ገበያ ስያሜ ወይንስ በባርነት!?" ባርነት የነፃነት ተለዋጭ ስም ከሆነ ደግ፤ እንዳሉን እንቀበላለን።

ከባርነት ግዞት ዛሬም ድረስ "ነፃ ያልወጣው" የስኳር ጉዳይም "ሻሂ! ሻሂ" እንዳሉ ማለዳ ላይ ወደ ትምህርት ቤታቸው እያነቡ የምንሸኛቸው ልጆቻችን እምባቸው ተሟጦ እርማቸውን ስላወጡና "ባዶ ሻሂ" መጣጣትን ስለለመዱልን ሸክማችንን አቃለውልናል። ደግነቱ ዘመናዊዎቹ ሐኪሞቻችን ከጤንነት ጋር አያይዘው "ስኳርን" ስለሚኮንኑ ልጆቻችንን ማሞኛ ዘዴ ስላላጣን እናመሰግናቸዋለን።

እግረ መንገዱን ግን የሕክምናው ወጪና የመድኃኒቱ ዋጋ ንረትም ንብረትም ተሸጦ ቢሆን ስለማይመከት የሚሻለው የሕመም ሁሉ መቅሰፍት እንደ እስራኤላውያን ፋሲካ ሳይነካን እንዲያልፈን በጾምና በጸሎት መቃተት ብቻ ነው።

በኢኮኖሚክሱ የጥናት ዘርፍ "ነፃ" ተብሎ የሚጠራው የግብይት ሥርዓት በንግድ ልውውጦች ሂደት የመንግሥት ቁጥጥር ወይንም ፖሊሲ ጫና ሳይኖርበት በአምራች/አቅራቢ እና በሸማች/ተጠቃሚ መካከል ምንም ዓይነት ቁጥጥር ያለመኖሩን ለማመልከት ነው። በነፃ የገበያ ሥርዓት ውስጥ የሸቀጦችና የአገልግሎቶች ዋጋ የሚወሰነው በፍላጎትና በአቅርቦት ሕግ መሠረት እንጂ "በደንብ አስከባሪዎች ወይንም በፖሊሶች" የዱላ ማስፈራሪያ ወይንም ሱቅን በማሸግ በሚወሰድ እርምጃ አይደለም።

በነፃ የገበያ ሥርዓት ውስጥ ተዋንያኑ ተግባብተው የሚገበያዩት በድርድር እንጂ "የምንትስ ቢሮ ሹመኞች" ፈርመው በሰጡት የሸቀጦች ዋጋ ዝርዝርና ሻጩም ለይምሰል ያህል በፍሬም ውስጥ አቆነጃጅቶ ለይስሙላ ያህል በሚለጥፈው ሰንጠረዥ መሠረት አይደለም። "አንዳንዴ መንግሥትም እኮ ገበያውን ለማረጋጋት መብትም ግዴታም አለበት" የሚለው መከራከሪያ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሚጨበጥ እውነት አይደለም፤ ሲሆንም አላየንም።

የሀገራችን ነፃ ገበያ በምን መስፈርት ተለክቶ "አርነት" እንደታወጀለት ቢብራራልን አንጠላም። የሰሞኑን የሲሚንቶ ገበያ ትራጄዲ ውሎ ብቻ ለአብነት ማስታወስ ይቻላል። መንግሥት "የሲሚንቶ ስርጭቱንና ግብይቱን እቆጣጠራለሁ" ባለ ማግሥት አንዲት ከረጢት ሲሚንቶ ለቀብር ማስፈጸሚያ ማግኘት የተሳናቸው ቤተሰቦች እንደምን ኀዘኑ እንደከፋባቸው ደጋግመን ያየነው ነው። ለቤት ግንባታማ ምን ሲደረግ ሲሚንቶ በገበያ ላይ ተገኝቶ።

መንግሥት የሲሚንቶ ቁጥጥሩ አላዋጣ ብሎ ናላውን ሲያዞረው "ለቅቄዋለሁ እንዳሻችሁ ተገበያዩ" ብሎ በወሰነበት ማግሥት ገበያው "ሕግን ሽፋን ባደረጉ ሽፍቶች" እጅ ወድቆ እንደምን ሕዝቡ እንደሚሰቃይ እያስተዋልን ነው። "ቤተ ሰሪ ደም የለውም" የሚለው የተለመደ አባባል "እምባንም" ቢያክልበት ተገቢ ይሆናል።

"የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል" እንዲሉ ወደ ዳቦ ጉዳያችን እንመለስ። በቅርቡ ይህ ጸሐፊ አዘውትሮ የማለዳ ቁርሱን የሚገዛበት ዳቦ ቤት በአንድ እሽግ የተሸነሸነ ዳቦ ላይ ስድስት ብር እንደጨመረ ለደንበኞቹ የገለጸው በኩራት ነው። "ስመ ገብስ" መልክ ባለው ጠይም ዳቦ ላይ ደግሞ አሥር ብር ተጨምሯል።

ይህ የሆነው በሙስና ድርጊት ስሙ በጎደፈው በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ውስጥ ነው። ያገባኛል ባይ አካል ሄዶ ዳቦ ቤቶቹን ይፈትሽ። የግራሙ ጉዳይማ ባይነሳ ይሻላል። የቀድሞዎቹ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "ዳቦ ለተራበ!" እያሉ የተሟገቱበትን መፈክር ዳግም አንስተን በካርዳችን መንበረ ሥልጣኑን ባነጣፍንለት መንግሥታችን ላይ ብንፈክርና ብንጮኽ አግባብ ይመስለናል።

የዚህን ጸሐፊ ልብ በእጅጉ ያቆሰለን አንድ ሁኔታ ልጥቀስ። ድርጊቱ እንኳን በኢትዮጵያ ምድር ቀርቶ በየትም ዓለም የማይደረግ መሆኑ እንደ ሀገር እፍረት ነው ቢባል ማጋነን አይገባም። አንዲት ብላቴና የሃያ አምስት ሳንቲም ቆሎ ሰፍራ ስትሸጥ ያስተዋልኳት በቆርኪ ወይም በቆርኪ መሰል መስፈሪያ ነበር።

በአጭሩ የቆርኪውን ስፍር እንቁጠረው ካልን ከሃያ አምስት ጥሬ መብለጡን እጠራጠራለሁ። በአጭሩ ለነፃ ገበያችን ትሩፋት ማሳያነት ይህ ልብ ሰባሪ ገጠመኝ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል። ምኑን ከምኑ ጋር አመሳሰልክ እንደማልባል ተስፋ አደርጋለሁ። ኑሮ ካሉት መቃብር መሞቁን ያመንነው በዘንድሮ ኑሯችን ነው።

የእስታስቲክሱ የቁጥር ጨዋታና የኑሯችን ገመና እንደተኳረፈ ኖረን የምናልፈው እስከ መቼ ድረስ ይሆን? ችግሩስ ስለምን በግልጽነትና በዝርዝር አይገለጽልንም? የንግድ ሥርዓቱን እመራለሁ የሚለው መንግሥታዊ ተቋምስ እስከ መቼ "ይህንን ያህል ቶን ስኳር ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቻለሁ፣ ይህንን ያህል ሜትሪክ ቶን ስንዴ አከፋፍያለሁ፣ ይህንን ያህል ሊትር ዘይት ለሕዝብ አቅርቤያለሁ በማለት እያማለለን ይኖራል?"፤ "ነገሩ ከሆነ የተገላቢጦሽ፤ አህያ ወደ ሣር ውሻ ወደ ግጦሽ" ይሏል ይሄኔ ነው።

መቼም መንግሥታት ሁሉ ሕዝባቸውን የሚደልሉበት ብልሃት አያጡም። አንዳንዴ በዓለም ገበያ ይመካኛል። አንዳንዴ በተፈጥሮ የአየር መዛባት ይኮነናል። አዘውትሮም የሂሳብ ቁጥሮች ለማደነጋሪያነት ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ይህ ከዘመን ጋር የሸበተው ዘዴ በእኛ ላይ ሲተገበር እያየን ነው። አሮጌ አስተሳሰብና ርእዮተ ዓለም ለማስተናገድ ማን ብሎን?

ዳቦ መጋገሪያ ፋብሪካዎች ተመረቁ የሚል ዜና ስናደምጥ እልልታችንን ሳንጨርስ በማግስቱ የዳቦው ግራም ተቀንሶ መጠኑ ቀንሶ ውስጡ ባዶ ሆኖ ወደ ዕንቁላል ደረጃ ዝቅ ሲል እናያለን። አብሮም የዋጋ ጭማሪ ተደርጎበት ተገልጋዩ ሕዝብ እንዲማርር ሲዘየድ እናስተውላለን።

ስኳርና ዘይት ገባ በተባለበት ቀን በከተማ ሽፍትነት የመሸጉ ጨካኞች እንዴት ባለ ዘዴ እንደሆነ በማይታወቅ ረቂቅ ስልት "ገባ" የተባለውን ሸቀጥ ሙልጭ አድርገው ወደ መጋዘናቸው በማስገባት በመቶ እጥፍ እየቆነጠሩ ለመከረኛው ሕዝብ እንዲቸረቸር ያደርጋሉ።

ይህ ጸሐፊ አንዳንዴ ለመንግሥታችን ምነው የደርግ መንግሥትን ያህል ጥቂት ኮስታራ ሀሞት በሰጠው እያለ ይመኛል። ይህ ምኞቱ የቢቸግር ዘዴ እንጂ በርግጥም ያ ሥርዓት የሚናፈቅ ሆኖ አልነበረም። በዚያ ዘመነ ደርግ "የሕዝብ ሱቅ" ይባል በነበረው መዋቅር ይገለገል የነበረው ሁሉም የማሕበረሰብ ክፍል ነበር። የኑሮ ከፍታና ዝቅታ እጅግም ፕሮቶኮሉ አይጠበቅም።

በቤተሰብ ቁጥር የስኳር ኮታ ይደለደላል። በቤተሰብ ቁጥር ዳቦ ይታደላል። በቤተሰብ ቁጥር ዱቄትም ጤፍም ይከፋፈላል። ይህንን አስተዳደር የሚመሩት ደግሞ በደመወዝ የተቀጠሩ ሠራተኞች ሳይሆኑ በነዋሪው ሕዝብ የተመረጡ አመራሮች ናቸው። ይህ ጸሐፊ የወጣትነቱ ዕድሜ ገደብ ሳይጥልበት በ25 ዓመት ዕድሜው ግድም በቅንነትና በታማኝነት በመኖሪያው አካባቢ (ከፍተኛ 25 ቀበሌ 02) የሕዝብ ሱቅ ሰብሳቢ በመሆን ማገልገሉን የሚያስታውሰው በኩራት ነው።

በዚሁ አገልግሎቱ ምክንያትም ሕዝቡ የሰጠው የክብር እውቅና በዘመኑ ሁሉ ማሕበረሰብን ሳይታክት እንዲያገለግል ትልቅ የሞራል ስንቅ ሆኖታል። በዛሬይቱ ኢትዮጵያስ በሕዝብ የተመከረባቸው አንዳንድ መሰል ወይንም የተሻሉ ዘዴዎች ቢተገበሩ አዋጭ አይሆን ይሆን? ሰሚ ጆሮ ካለ መመካከሩ አይከፋም።

### መንግሥታችን ሆይ!

የዴሞክራሲ መብታችንን ተጠቅመን እንድንማጸን ይፈቀድልን። ለመሆኑ በርግጡ የሀገራችን ገበያ "ነፃ" የሚል ስም ሊሰጠው ይገባል? ከመንግሥት ቁጥጥር ባርነትስ አርነት ወጥቷል? የገበያውን ሥርዓት እንደፈለጋቸው የሚያተረማምሱትንና የንግዱን ሥርዓት እንዳሻቸው የሚያምሱት የከተማ ሽፍቶችን በውኑ መቋጣጠር ከአቅምህና ከመዋቅርህ ውጭ ሆኖብሃል? ሕዝቡ ጮኾ ጮኾ ድምጹ ሰልሏል።

ከልማት ስኬቱ ዜና ጎን ለጎን ቢያንስ ገበያው ተረጋግቶለት በገፍ ባይሆንም የእለት ጉርሱን እንኳ ሳይሳቀቅ እንዲያገኝ የገበያ ሥርዓቱን ከእብደቱ ለመፈወስ ስለምን ተሳነህ። በቅርቡ እንኳን በሣምንቱ ቀናት እንዲቆሙ በተፈቀደላቸው የከተማችን የአደባባይ ገበያዎች ላይ ደላሎች እንደፈለጉ ሲፈነጩ ማስተዋል የተለመደ ሆኗል። አንዳንድ የወረዳና የክፍለ ከተማ ሹመኞች ላይ ክትትል ቢደረግ አይከፋም።

ለፖለቲካው የወገኑና በሁሉም ስብሰባ ላይ "የመንግሥትን እድሜ በሺህ ዓመት የሚመኙትን ቤተኞች ብቻ ከመጥራት በመቆጠብ" ከተርታው ሕዝብ የተመረጡ ግለሰቦች በገበያው እብደት ላይ እንዲወያዩና እንዲመክሩ መድረክ ቢመቻችላቸው እውነቱ ከመፍትሔ ጋር ተፍረጥርጦ ይወጣ ነበር።

ቢቻልም እነዚሁ "ነፃ" ነዋሪዎች ለየክፍለ ከተሞቹ፣ ወረዳዎቹና ቀበሌዎች በኮታ የሚደርሳቸው ሸቀጥ በግልጽነትና አሰልቺ ባልሆነ ተራና ወረፋ በየሸማቾቹ ጣቢያዎች እንዲከፋፈል የራሳቸውን ዘዴ ቀይሰው እንዲያስፈጽሙ ሙሉ መብት ቢሰጣቸው የተሸፋፈነው ጉድ ይገላለጥ ነበር።

ከላይ የተጠቀሰው ምክረ ሃሳብ ተግባራዊ እንዲሆን ካስፈለገ በሁሉም ሕዝባዊ ጉዳዮች ጥልቅ ካላልን የሚሉት የሠፈር ፖለቲከኞች ለጊዜው ከዚህን መሰሉ አሠራር እጃቸውንም ሆነ አፋቸውን እንዲሰበስቡ ማዕቀብ ይጣልባቸው። መንግሥቴ ሆይ! ያኔ ውጤቱን ታየዋለህ።

ይህ አንድ ዘለላ የመፍትሔ ጥቆማ አቅጣጫ እንጂ ለውስብስቡ ችግራችን ሁሉ መፍትሔ ይሆናል ማለት አይደለም። የሀገራዊ ችግሮቻችን ጉዳይ ቢዘረዘር አንድ ሺህ አንድ ሌሊት ስለሚፈጅ ሃሳባችንን በዚሁ እንቋጭ። "ቢቸግር ጤፍ ብድር" የተባለው ስለምን ነበር? አባባሉስ ለዛሬ ይሠራል። እንጃ። ሰላም ለሕዝባችን፤ በጎ ፈቃድ ለዜጎች ይሁን።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# ልጅ አይውጣልህ የተባለው አባት

**አስመረት ብስራት**

‹‹አባት›› የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የአንድ ነገር ምንጭ ወይም ጀማሪ የሚል ትርጓሜን ይይዛል። ‹‹አባት›› ማለት ተፈጥሮውን ‹‹ለልጆቹ›› የሚያስተላልፍ ማለት ነው። ‹‹አባት›› ማለት በልጆቹ ላይ ሥልጣን ያለው ማለት ነው። ምድራዊ ልጆች ሰውነታቸውንና ነፍሳቸውን ከወላጆቻቸው ይወስዳሉ። አባትነት በሰው ሰውኛ ሲገለፅም ልዩ ምስጢር አለው።

አባትነት እምነት፤ እናትነት እውነት በሚል ብሂልም አባት መሆኑን በእምነት አምኖ ተቀብሎ ለልጆቹ ጥላ ሆኖ ከመከራ ከልሎ ሲያሳርፍ፤ ማደጋቸውን በጉጉት እየተመለከተ ነጋቸውን በአይነ-ህሊናው ሲቃኝ፤ በእርጅናው ደግሞ በፀሎት የልጆቹን ቀና መንገድ ሲመኝ የሚኖር ታላቅ ገፀ በረከት ነው - አባትነት።

ታዲያ ይህን የአባትነት ምስጢር ያፈረሰ፣ ትስስሩን ባልተገባ መንገድ የበጠሰ ልጅን በአባት ላይ በጭካኔ እንዲነሳ ያደረገ ታሪክን ከፍትህ ሚኒስቴር የፌስቡክ ገጽ ተመለከትኩኝ። አባት ብቻ መኖሩ መከታ ለሚሆነን የእኔ አይነቷ አባት ወዳድ አሰቃቂ ቢሆንም አንባቢ ይማርበት ዘንድ በዚህ መልኩ አቅርበነዋል። መልካም ቆይታ።

### ልጅ አይውጣልህ የተባለው አባት

ዘላለም ገብረ ሚካኤል ይባላሉ። እድሜያቸው በስልሳዎቹ መጨረሻ የሚገመት አዛውንት፤ እንዲሁም፣ ሀብት ሞልቶ የተረፋቸው አይነት ባለፀጋ አባት ናቸው። ልጆቻቸውን ባላቸው የሀብት መጠን አንቀባርረው "ውድ" የሚባል ትምህርት ቤት አስተምረው አሳድገዋል። ልጆቹም አጀማመራቸው ላይ የት ይደርሳሉ የተባሉ፣ በጣም ጎበዝ፤ ለቤተሰቦቻቸው ታዛዥ፤ ሰውን አክባሪ ልጆች ነበሩ።

ልጆቹ እያደጉና እየጎረመሱ ሲሄዱና ያለስስት አባታቸው የሚሰጧቸውን ገንዘብ መጥፊያ ሆኗቸው እንደ አይን ጠፉ። የት ይደርሳሉ የተባሉት ወጣቶች ፊር ለቀው ያልተገባ ባህሪን ያሳዩ ጀመር። ይባስ ብሎ ያለምንም እፍረት ውጭ ማደርንና መዋልን የዘወትር ተግባራቸው አደረጉት። ከሶስት ልጆቻቸው አንዷ በከባድ የሱስ ሕይወት ውስጥ ገበታ መውጣት ተስኗት በአእምሮ ህመም ላይ ትገኛለች።

ሌላው ልጃቸው ደግሞ ከአባቱ ኪስ አንስቶ ያልፈተሸው ኪስ የለም በሚባል ደረጃ ለሱሱ ማስታገሻ የሚሆን ገንዘብ ፍለጋ ሲዘርፍና ሲቀማ ቆይቶ በአንድ የተረገመ አገጣሚ ገንዘብ ለመቀማት በትር የሰነዘረባቸው አዛውንት እንደወደቁ እስከ ወዲያኛው በማሸለባቸው የተነሳ በፖሊስ ሲታደን ቆይቶ ወህኒ ከወረደ ሰነባብቷል።

ሶስተኛው ልጃቸው ባህሪው መልካም ቢመስልም የገንዘብ ነገር የማይበቃው፣ ዘወትር ከአባቱ ጋር ብር ስጠኝ አትስጠኝ በሚል ሙገት የሚገጥም አይነት ልጅ ነው። እሳቸውም በልጆቻቸው አለመባረክ ዘወትር እያነቡ ጤናቸው ተጓድሏል።

"የቱ ጋ ነው የተሳሳትኩት?" እያሉ ሁል ጊዜ እራሳቸውን ይጠይቃሉ። አስበው አስበው ለበጎ ያሉት ወደ ክፉ ተቀይሮባቸው እንጂ ልጆቻቸው በእንዲህ አይነት ሥነምግባር ውስጥ እንዲወድቁ አስበው ምንም አለማድረጋቸው ደግሞ አንጀታቸውን ድብን ያደርጋቸዋል። ቀናና ተገቢ ነው ያሉት አስተዳደግ ልጆቻቸውን የማጣመሙ ነገር ከውስጣቸው አይወጣላቸውም።

ከሰው እንዳያነሱብኝ ሲሉ የሰጧቸው ገንዘብ ከሰው በታች ያዋላቸው ልጆቻቸው ለማንም የማይጠቅሙ ብኩን የመሆናቸው ነገር ቆሽታቸውን አድበኖ እኚያ በኩራት የሚጎማለሉት ታላቅ ባለፀጋ አባት አንገታቸውን የደፉ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

አዛውንቱ አባት በኀዘን ኩርምት ከማለታቸውም በላይ ሶስተኛ ልጃቸው ገንዘብ ካልሰጡት የሚያሳየው ያልተገባ ባህሪ በፍርሃት ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል። አይኑን ማጉረጥረጡን፤ ዛቻና ማስፈራራቱን ሲመለከቱ "እንደው አንድ ቀን ደፍሮ እጁን ያነሳብኝ ይሆን?" የሚለው የዘወትር ጥያቄያቸው ሆኖ ልባቸውን አስጨንቆታል። የፈሩት ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል አይነት ነገር ደርሶባቸው ዛሬ የዘወትር ስጋታቸው እውን ሆኗል ...

### ሱስ አቅሉን ያሳተው ወጣት ነቢዩ

የአቶ ዘላለም ሶስተኛ ልጅ ነቢዩ ዘላለም ከልጆቻቸው መካከል በአመለ ሸጋነቱ ነበር የሚታወቀው። ከእናቱ እቅፍ የማይወጣ የሳሎን ጌጥ አይነት ልጅ ነበር። በትምህርቱም ጎበዝ ከመሆኑ የተነሳ በየአመቱ ሽልማት ይዞ የሚመጣ፤ ከቤተሰብም አልፎ በዘመድ አዝማድ የተወደደ ልጅ ነበር። አባቱ በስስት ስለሚመለከቱት አርጉልኝ ያላቸውን በሙሉ ያደርጉለት ነበር።

ስምንተኛ ክፍል ሚኒስትሪን በከፍተኛ ውጤት አልፎ ዘጠነኛ ክፍል የገባ የመጀመሪያዎቹ ወራት ላይ ነበር ነቢዩ ያልተገባን ባህሪ ማሳየት የጀመረው። መጀመሪያ አካባቢ የጉርምስና ብቻ የሚመስሉ የባህሪ ለውጦችን ቢያሳይም፣ እየዋለ እያደር ግን ከዛ ትሁት ልጅ የማይጠበቁ ቃላትን ያወጣ ጀመር። ከፀያፍ ቃላቱ በላይም የትምህርቱን ነገር ቀስ በቀስ እርግፍ አድሮጎ ተወ።


ትምህርት ቤት ከሚገባበት ቀን የሚቀርባቸው ቀናት በለጡ። ውሎው ጫትና ሺሻ ቤት ሆነ። እሱ በሚያመጣው ገንዘብ እንዲያዝናናቸው ዙሪያውን የከበቡት ጓደኞቹ እሱ ከአባቱ ከሚሰጠው ትንሽ የኪስ ገንዘብ በላይ እንዲያመጣ ዘወትር ይገፋፉት ጀመር።

እንደ ቀልድ የገባበት የሱስ ሕይወትም እንዳይወጣ አድርጎ እግር ከወረች ያሰረው ወጣት ነቢዩ በአብዛኛው አባቱን ጨቅጭቆ፣ ገንዘብ ተቀብሎ፤ ይህ ካልሆነም ሰርቆ ለሱና ለጓደኞቹ የሚሆን ገንዘብ ይዞ ይወጣ ጀመር። እለት በእለት ከሱስ ቤት አካባቢ የማይጠፋው ከጫትና ከሲጋራ አልፎ ወደ አደንዛዥ ሱስ ውስጥ ገባ። ለዚህ ሱሱ የሚሆን ገንዘብ ባጣ ጊዜ ደግሞ እንደ እብድ የሚያደርገው ሲሆን፣ በዚሁ ምክንያትም ሰው እስከመግደል ድረስ ወንጀል ሊፈፅም የሚችል አይነት ወጣት ሆነ።

ነጋ ጠባ አባቱን አስፈራርቶ፤ ሲለውም ሰድቦና ዝቶ ገንዘብ ሲቀበላቸው ኖሯል። ገንዘብ ሲጨርስ ብቻ ወደ ቤት ብቅ የሚለው ወጣት ልጅ አይውጣሎት የተባሉ የሚመስሉትን አባት አቶ ዘላለም ቁም ስቅላቸውን ያሳያቸው ጀመረ።

ከስድብና ዛቻ አልፎ ሽጉጥ ይዞ በመምጣት እያስፈራራቸው በርካታ ገንዘብ እንዲሰጡት ማስገደድ ከጀመረ ሰነባብቷል። ላባቸውን ጠፍ አድርገው ለልጆቻቸው ሕይወት መቃናት ድጋፍ ያደርግልኛል፤ በእድሜዬ መጨረሻ እጦርበታለሁ ያሉትን ጥሪታቸውን ሊያሳጣቸው የተነሳውን ልጃቸውን በሽማግሌ ቢያስጠይቁት፣ ተንበርክከው ቢለምኑት አሻፈረኝ፣ ገንዘብ ወይም ሞት በማለት የጭካኔ እርምጃ ለመውሰድ እየፎከረ ገባ።

እሳቸውም "ዘመኔን ሙሉ ከኖርኩበት ቤት ሬሳዬ ይውጣ እንጂ ቤት ንብረቴን ሸጬ ለአንተ አልሰጥም" በማለት ቁርጠኛ አቋማቸውን አስቀመጡ። አባቱ ሃሳባቸውን እንደማይቀይሩ የተረዳው ልጅም ቂም ቋጥሮ ሊያጠፋቸው ተነሳ።



### ወላጅ አባት ላይ የተሳበው ቃታ

ወሩ ህዳር ነው። ህዳር 12 ቀን 2013 ዓ.ም ህዳር የሚታጠንበት ቀን። ሰው ሁሉ የቤቱን ቆሻሻ አውጥቶ በማቃጠል በሽታው ክፉ ሃሳቡ በሙሉ ከሕዝቡ ልብ ውስጥ ተጠራርጎ እንዲጠፋ የሚመኝበት ቀን። አቶ ዘላለምም እንደ ጎረቤቶቻቸው በጠዋት በመነሳት ግቢያቸውን ጠራርገው አቃጥለዋል። እለቱ የቅዱስ ሚካኤል የንግስ በዓል ስለነበር በአቅራቢያቸው ወዳለው ቦሌ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን ደርሰው ለመምጣት ከቤታቸው ይወጣሉ። መድረሻቸውን ቤተክርስቲያን እንዲሆን ተመኝተው ቢወጡም መንገድ ላይ ደካክሟቸው ወደ ቤት ይመለሳሉ።

"ምነው ያለወትሮዬ እንዲህ አቅም አነሰኝ?" በማለት ቤታቸው ተመልሰው ለንግስ በዓሉ የተዘጋጀውን ቀማምሰው አረፍ ይላሉ። ቀኑን ሙሉ ተኝተው የዋሉት አባት አመሻሹ ላይ ተነስተው ግቢያቸው ውስጥ ሲንቀሳቀሱ ነበር ልጃቸው ነቢዩ ወደ ግቢ የገባው። ከወትሮው በተለየ ተቆጥቷል፤ ገና በጊዜ መጠጥ እንደጠጣ አፉ ያስታውቃል። አባቱን ሊያናግራቸው እንደሚፈልግ አስረድቶ ወደ ውስጥ ይጋብዛቸዋል።

"ለመጨረሻ ጊዜ ልጠይቀህ ቤቱን ሽጠህ ትሰጠኛለህ ወይስ ...?" በማለት ይጠይቃቸዋል። እሳቸውም በምንም አይነት ሁኔታ አቋማቸውን እንደማይቀይሩ ያስረዱታል። ያኔ ነው እንግዲህ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ቦሌ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት፣ ቴዲ ባር አካባቢ ወላጅ አባቱን፣ ሟች ዘላለም ገ/ሚካኤልን በሽጉጥ ጭንቅላታቸውን ሶስት ቦታ በመምታት ሕይወታቸው እንዲያልፍ ያደረገው።

ነቢዩ ዘላለም አባቱ ላይ ያደረገውን የተመለከቱት እናቱና ጎረቤቶች ባሰሙት ጩኸት በአካባቢው የነበሩ የፀጥታ አካላት በቁጥጥር ስር አዋሉት።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ተጎጂው በሕይወት እንደሌሉ በማረጋገጥ ለምርመራ ከላከ በኋላ ወንጀለኛውን በቁጥጥር ስር በማዋል ወደ ማረፊያ ቤት ይወስደዋል። የሰነድና የሰው ማስረጃውን በአግባቡ ያጠናቀረው የወንጀል ምርመራ ቡድን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ፣ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ያቀርባል።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ወላጅ አባቱ የሆነውን በሽጉጥ ጭንቅላቱን በመምታት ሕይወቱ እንዲያልፍ ባደረገው ግለሰብ ላይ ክስ መስርቶበት በ22 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ አድርጓል። ተከሳሹ ከማህበራዊ አገልግሎት ለ5 ዓመት እንዲታገድ ሲልም ወስኖበታል። ተከሳሽ ዳኞችን በችሎት ፊት ውሳኔያችሁ የማይረባ ነው ከተፈታሁ በኋላ አሳያችኋለሁ በማለቱ ችሎቱ በተጨማሪነት በ 1 ዓመት ቀላል እስራት ቀጥቶታል፡፡

የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ነቢዩ ዘላለም ህዳር 12 ቀን 2013 ዓ.ም በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01፣ ቦሌ ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን ፊት ለፊት፣ ቴዲ ባር አካባቢ ወላጅ አባቱ ሟች ዘላለም ገ/ሚካኤልን በሽጉጥ ጭንቅላቱን ሶስት ቦታ ላይ በመምታት ህይወቱ እንዲያልፍ ያደረገ በመሆኑ የወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1) (ሀ) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ በከባድ የሰው መግደል ወንጀል ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶበታል፡፡

### ውሳኔ

ክርክሩን የመራው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ሲሆን ተከሳሹ ክሱ በችሎት ተነቦለት ድርጊቱን ስለመፈጸሙ ተጠይቆ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ዐቃቤ ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በበቂ ማስረጃ በማቅረብ አረጋግጧል።

ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑ በመረጋገጡ የጥፋተኝነት ፍርድ የሰጠው ፍርድ ቤት ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተከሳሹ ላይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በደረጃ 1 እርከን 38 ስር መነሻ ቅጣት በመያዝ፣ ተከሳሹ የወንጀል ሪከርድ የሌለበት በመሆኑ፣ 1 የቅጣት ማቅለያ ተይዞለት በእርከን 37 ስር በማሳረፍ ተከሳሽን ያርማል፤ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ያስተምራል ያለውን በተከሳሹ ላይ በ22 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣና ከማህበራዊ አገልግሎት ለ5 ዓመት እንዲታገድ ሲል ወስኖበታል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የመመረቂያ ጽሁፍ ገበያ

የትምህርት ነገር በሀገራችን ኢትዮጵያ በብርቱ ሕመምና ሥቃይ ውስጥ ከገባ ውሎ አድሯል። ነገረ ጉዳዬን ፈር ለማስያዝ ያግዘኝ ዘንድ ጥቂት ገጠመኞቼን ላስቀድም።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት አንዲት የሥራ ባልደረባዬ የሆነች ጓደኛዬ ስልክ ደውላልኝ- "እባክህ አንድ ጉዳይ ላማክርህ ፈልጌ ነበር፤" አለችኝ። የእኔን ዕርዳታና የምክር እገዛ የሚሻ ምን ጉዳይ አጋጥሟት ይሆን ይህች ወዳጄ በሚል ሥጋትና ፍርሃት ውስጥ ሆኜ - ምንድን ይሆን ጉዳዩ አልኳት። እንዲህ ስትል ጉዳዩዋን አጫወተችኝ።

"... ይኸውልህ ታናሽ እህቴ የሁለተኛ ዲግሪዋን በአንድ የግል ኮሌጅ እየተማረች ነው። እናም ለማስተርስ ዲግሪዋ ማሟያ የሚሆናትን የጥናት ወረቀት የሚሠራላት ሰው ትፈልጋለች። አንድ ሁለት ሰዎችን ጠይቃ ነበር ግን ከ 15 እስከ 20 ሺህ ብር ዋጋ ጠየቋት። መቼም የመንግሥት ቤት የደመወዝ ነገር ታውቃዋለህ... ዋጋው ተወደደባት እናም ቀነስ ባለ ዋጋ የሚሠራ አንተ የምታውቀው ተባባሪ ሰው ካለ እንድትጠቁመኝ ብዬ ነው፤" አለችኝ።

እኔም፤ እንዴ!? ለምን ይህን ያህል የዋጋ ድርድር ውስጥ ከምትገባ የሚከብዳትን ነገር ካለ እያገዝናት በራሷ ጥረት/ችሎታ የመመረቂያ ወረቀቷን ለመስራት አትሞክርም አልኳት። "አይ! ወንድሜ እሷ ከፕሮፖዛል ጀምሮ የመመረቂያ ወረቀቱን ሙሉውን ሠርቶ የሚያስረክባት ሰው ነው የምትፈልገው፤" አለችኝ። ደግሞስ አናውቅምና ነው እንዴ... ለመሆኑ ከጥቂት ተማሪዎች በቀር አብዛኛው ሰው የሌላ ሰው የመመረቂያ ወረቀት ርእሱን ብቻ እየቀየረ እያሰገባ አይደል እንዴ የሚመረቀው... ሲጀመርስ እዚህ አገር ወረቀት ይኑርህ እንጂ እውቀት ቦታና ስፍራ አለው እንዴ?! ወንድም ዓለም እህቴ አሁን የምትፈልገው ትንሽም ብትሆን የደረጃና የደመወዝ የዕድገት ምክንያት የሚሆን የዲግሪ ሰርተፊኬት በእጇ ላይ እንዲገባላት ብቻ ነው፤ ሌላው ሁሉ ትርፍ ነው፤" አለችኝ በምሬት ፈርጠም ብላ።

እህቴ ይቅርታ ይህ ሌላ ጉዳይ ነው.. እኔ ግን የዲግሪና የማስተርስ ወረቀት ንግድ ጉዳይ ውስጥ መግባት አልፈልግም፤ በየኮሌጁና በየዩኒቨርሲቲው ደጃፍ ያለ ምንም ሃፍረትና መሳቀቅ "የመመረቂያ ወረቀት በተመጣጣኝ ዋጋ እንሠራለን!" የሚሉ ማስታወቂያን የለጠፉ ብዙዎች አሉና እነሱኑ ብትደራደር/ብትለማመጥ ይሻላታል፤ ብያት ተለያየን። ከጥቂት ሳምንት በኋላ ይህችን የሥራ ባልደረባዬን አገኘኋትና እህቷ እንዴት እንደሆነች ጠየቅኳት።

"እባክህ ምን ይደረግ ብለህ ነው?! እንደምንም ተደራድረን በ 12 ሺህ ብር የማስተርስ ዲግሪ የመመረቂያ ወረቀቷን ሠርተው እንዳስረከቧት፤" ነገረችኝ። አሁን ደግሞ ይኸውልህ ለዲፌንስ የ Powerpoint ገለጻዋን በአማርኛ ተርጉሞ የሚያስረዳት ሰው እየፈለግን ነው፤ ብቻ እንደ ምንም ብላ በተገላገለች እኔንም ግራ አጋባችኝ እኮ...፤" ብላኝ እርፍ አለች።

እንግዲህ በሀገራችን የትምህርት ጥራት ጉዳይ ምን ያህል ማጣጣርና በጽኑ ሥቃይ ውስጥ እንዳለ ይህ አንድ ማሳያ ነው። በተመሳሳይም በዚሁ ዓመት በግሌ የማውቃቸው ከሌላ የግል ዩኒቨርሲቲ በሌላ ተማሪ የተሠራ/የተገለበጠ የጥናት ድርሳንን እንደገና እነርሱም ገልብጠው አቅርበው የተመረቁ ተማሪዎችን አውቃለሁ። የመመረቂያ ወረቀቶችን መሥራት ለነገሩ መሥራት ሳይሆን የአንዱን ከአንዱ እየገለበጡ መስጠት የጦፈና የሚያዋጣ ቢዝነስ ሆኗል። ሌላ መራር ገጠመኜን ላክል።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለተወሰነ ጊዜያት በሥራ በቆየሁበት አጋጣሚ በግል ኮሌጆች የሚማሩ ጥቂት የማይባሉ የኢሕአዴግ ሹመኞችና ካድሬዎች ከዩኒቨርሲቲው ቤተ-መጻሕፍት በተማሪዎች የተሠሩ የመመረቂያ ወረቀቶችን እያስወጡ የራሳቸው እንደሆነ አድርገው በማቅረብ ይመረቁ እንደነበር እነርሱም ያውቃሉ፤ እኛም እናውቃለን።

እንግዲህ በዚህ ዓይነት የወደቀ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለፉ መምህራንና የሥራ ኃላፊዎች ምን ዓይነት ተማሪዎችንና ዜጋን ሊያፈሩ እንደሚችሉ ማሰብ ነው... ለነገሩማ የነገረ-ገዳዩን አንዱን ስር ስንመዝ መንግሥት እንደ ጠበል በየክልሉ ካዳረሳቸው ዩኒቨርሲቲዎች ጀምሮ በየመንደሩ የተከፈቱ የግል ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎችን- የመምህራኑን የእውቀት ደረጃ፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ ቤተ-መጻሕፍትና ቤተ-ሙከራዎች ጥራት፣ ዘመናዊነትና ተደራሽነት ብንገመግም ተቋማቶቻችን ብዙ የሚያስደነግጡ ጉዶችን ተሸክመው ነው ያሉት።

ሌላው ትምህርትን እንደ አንድ በአቋራጭ የመክበሪያ/የቢዝነስ መንገድ አድርገው የዲግሪና የማስተርስ ወረቀቶችን የሚቸርችሩ ጥቂት የማይባሉ የግል ኮሌጆች ለመጀመሪያ ዲግሪም ሆነ የሁለተኛ ዲግሪ ለማስተማር የሚያበቃቸውን የጥራት ማረጋገጫ በእንዴት ባለ ማታለል፣ እጅ መንሻና ሙስና እንደሚያገኙት ብትሰሙና ብታዩ ትደነግጣላችሁ። አሳዛኙና አስደንጋጩ እውነታ ደግሞ እነዚህን የትምህርት ተቋማት በማቋቋም፣ ባለቤትነትም ሆነ በመምራት ረገድ ጥቂት የማይባሉ "ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች" መኖራቸው ብቻ ሳይሆን በዚህ ትውልድን የሚያመክን ሥራ ውስጥ ተሳታፊ መሆናቸውን ስትታዘቡ ድንጋጤያችሁንና ኀዘናችሁን ያከፋዋል።

ለመውጫ ያህልም፤ ሰለሞን በላይ ፋሪስ (ዶ/ር)፤ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ መመረቂያ የሆነውን የፒ.ኤቺ.ዲ የጥናትና ምርምር ድርሳናቸውን፤ "ከዶክተርነት ደብተራ እና ወልይነት" በሚል አርእስት ለንባብ አብቅተዋል። ዶክተር ሰለሞን በዚሁ ወደ አማርኛ ቋንቋ በተረጎሙት የዶክትሬት መመረቂያ ድርሳን/መጽሐፋቸው ውስጥ - ከሀገሩም ከውጭውም ሳይሆን ግራ ተጋብቶ ስላለው የትምህርት ሥርዓታችን ጉዳይ ለጥናት ሥራቸው መረጃ ለማሰባሰብ ከሀገረ ካናዳ መጥተው ያጋጠማቸውን እንዲህ በማለት በቁጭትና በኀዘን ይገልጹታል።

"... በመንግሥት ስር ያሉም ሆነ ከመንግሥት ውጪ ያሉ የትምህርት ባለሙያዎች ሙያቸውን የተመለከተ ቃለ-መጠይቅ ማድረግ አስቸጋሪና በጣሙን ፈታኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። አንድም ከመጀመሪያውኑ ሥርዓተ-ትምህርቱ አርቆና አሰላስሎ አሳቢ ስላላደረጋቸውና በሚናገሩበት ጉዳይ ላይም በቂ ሥልጠና/ችሎታ ስለሌላቸው መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር። ችግሩን የሚያከብደውና የሚያከፋው ደግሞ አጣምሞ ያሳደገን ትምህርት መጣመማችንን (መንገድ መሳታችንን) እንድናውቅ አለማድረጉና መጣመማችንን ደግሞ ልናቃናው ያለመቻላችን መርገምት ነው። የሀገራችንን/የዛሬውንና የነገውን ትውልድ ዕጣ ፈንታችንን የምንወስንበትን ትምህርትን የመሰለ ነገር ሥርዓቱን ማሻሻልና መመርመር ካልተጋን ውጤቱ ከዛሬውም በጣሙን የባሰና የከፋ ሊሆን እንደሚችል ነው...፤" ይሉናል ትዝብት አከል በሆነ መጽሐፋቸው።

እንግዲህ የዛሬው ከመቶ ሺዎች ተፈታኞች ሃያ ሺዎቹ ብቻ የማለፊያ ለውጤት የማግኘታቸው ብዙዎቻችንን ያስደነገጠ ዜና እንዲሁ የአንድ ጀምበር ክሥተት አይደለም። ከታች ጀምሮ እስከ ላይ የተበላሸው የትምህርት ሥርዓታችን የተንጋደደ አካሄድ ውጤት ነው፤ ብሎ መደምደም ይቻላል።

በአጠቃላይ የትምህርት ጉዳይ በጽኑ ሕመም እና በብርቱ ሥቃይ ውስጥ ነው ያለው፤ እናም እስከወዲያኛው ከማሸለቡ በፊት መንግሥት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት እና ምሁራን ቅድሚያ ትኩረት ሊቸሩት ይገባል። አፋጣኝ የሆኑ ተከታታይ ርምጃዎችም ሊወሰዱ ይገባል። በትምህርት ዘርፉ የተጀመሩትን የለውጥና የማሻሻል ሥራዎችንም አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል።

**እንደ መቆዘሚያ ያለ የውይይት ማጫሪያ ሐሳብ፤**

እንደ ሕዝብ ችግራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበ መሄዱ የሚከተለውን መሠረታዊ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያስገድደናል፤ "ዘመናዊ ትምህርታችን ድህነትን የምንቀርፍበትን ክህሎት፣ እውቀትና ስብእና ሊሰጠን አሊያም ሊያጎናጽፈን ለምን አልቻለም?!"

# ዓለም አቀፍ





## በርዕደ መሬት የሞቱ ሰዎች ቁጥር 20 ሺህ በላይ መድረሱ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሶሪያእና በቱርክ በተከሰተው ርዕደ መሬት የሟቾች ቁጥር 20 ሺህ በላይ መድረሱ ሮይተርስ አስነብቧል፡፡

100 ሺህ ያህሉ የነፍስ አድን ሰራተኞች አሁንም ድረስ የሰዎችን ሕይወት ለመታደግ የተለያዩ ጥረቶች በማድረግ ላይ ቢሆኑም ካለው ቀዝቃዛ የአየር ጠባይ ጋር ተዳምሮ ነገሮች ከባድ እየሆኑ መጥተዋል፡፡፡

በተጨማሪም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ውሃና ምግብ ሳያገኙ ለችግር መዳረጋቸውን የሚያመለክቱ ዘገባዎች እየወጡ ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአደጋው መጠንና ያስከተለው ጉዳት በግልጽ ለማወቅ አለመቻሉ ሁኔታውን አሳሳቢ አድርጎታል ብሏል።

በተለይም በጦርነት ስትታመስ በቆየችው ሶሪያ ላይ ያለው የአደጋ መጠን ማወቅ አለመቻሉን ተመድ ገልጾ፤ የተመድ ዋና ጸሃፊው አንቶኒዮ ጉቴሬዝ የአደጋው መጠን እጅግ ከባድ መሆኑ "አሁን እየተገለጠልን ነው" ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡፡

አሁን ላይ ከቱርክ ወደ ሰሜን ምዕራብ ሶሪያ ሰብዓዊ እርዳታ መላክ መጀመሩን የገለጹት ዋና ጸሃፊው፤ ድጋፉ በሌሎች መስመሮችም ጭምር እንዲገባ የጸጥታው ምክር ቤት ኃላፊነቱን እንዲወጣም አሳስበዋል፡፡ "አሁን አንድነት የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ነው ያለነው፤ ፖለቲካ የሚሰራበት ጊዜ አይደለም ፤ ሰፊ ድጋፍ እንደሚያስፈልገን ግልጽ ነው" ሲሉም ተደምጠዋል፡፡

ሮይተርስ የቱርክ ባለሥልጣናት መረጃን ጠቅሶ እንደዘገበው ርዕደ መሬቱን ተከትሎ እስካሁን 17 ሺህ 600 ሰዎች ሞተዋል፡፡ በሶሪያም እንዲሁ 3ሺህ 377 ያህሉ ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል፡፡

በሬክተር ስኬል 7.8 የተመዘገበው የአሁኑ አደጋ እንደፈረንጆቹ1999 በሰሜን ምዕራብ ቱርክ ካጋጠመውና የ17 ሺህ ሰዎች ሕይወት ከቀጠፈው አደጋ የከፋ መሆኑ እየተነገረ ነው፡፡ የቱርኩ ፕሬዚዳንት ረሲፕ ጣይብ ኤርዶአን በበኩላቸው በሀገሪቱ የደረሰውን ርዕደ መሬት "የክፍለ ዘመኑ አስከፊ አደጋ" ነው ሲሉ ገልጸውታል፡፡

አሁን ላይ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ቱርካውያን እና ሶሪያውያን በጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ከሰፈሩ አራት ቀናት ተቆጥረዋል፡፡ ካለው የአየር ሁኔታ ጠባይ አንጻር ለከፍተኛ ቅዝቃዜ ተጋልጠውም ይገኛሉ፡፡

## በሶሪያ ፍርስራሽ ውስጥ የተወለደችው ሕጻን የብዙዎችን ቀልብ ስባለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሰሜን ምዕራብ ሶሪያ ባለፈው ሰኞ የርዕደ መሬት ፍርስራሽ ውስጥ ገና በተወለደችበት ቅጽበት የተገኘችውንና በተአምር የተረፈችው ጨቅላ በጉዲፈቻነት ለማሳደግ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ጥያቄ እያቀረቡ ነው።

አያ (ትንግርት) የሚል የአረብኛ ስም የተሰጣት ይህቺ ጨቅላ ዕትብቷ ከእናቷ ጋር ገና ሳይቆረጥ ነበር በሞትና ሕይወት መሀል ሆና ሳለች ከፍርስራሽ ውስጥ የወጣች ሲሆን የጉድፈቻ ጥያቄ ከሶሪያweያን ብቻ ሳይሆን ከመላው ዓለም እየቀረበላት ነው፡፡

አያ ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል ብትደርስም በቅጡ እንኳ መተንፈስ የማትችል፥ የቆሳሰለችና እብጠቶች የነበሩባት እንቦቀቅላ ነበረች ሲሉ አሁን ባለችበት ሆስፒታል የሕጻናት ስፔሻሊስት የሆኑት ዶ/ር ማሩፍ ተናግረዋል።

የጨቅላዋ አያ አሁን ጥሩ ሁኔታ ላይ ስትሆን ከፍርስራሽ አፈር ለብሳ ስትወጣ የሚያሳየው ተአምራዊ ቪዲዮ በማህበራዊ ትስስር መድረክ ከተዛመተ በኋላ ነበር ወዲያውኑ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች እኛ እናሳድጋት ማለት የጀመሩት።

የጨቅላዋ እናትን ጨምሮ አባቷ እንዲሁም አራት ወንድም እህቶቿ በሙሉ በርዕደ መሬቱ ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን ካሊል አልሱዋዲ የሚባል የጨቅላዋ የሩቅ ዘመድ ነው አሁን ለጊዜው አብሯት ያለው። እሱም በርካታ የስልክ ጥሪዎች እየደረሱት እንደሆነና የብዙዎች ጥያቄም በጉዲፈቻነት ለመውሰድ እንደሆነ ተናግሯል።

አንዲት የኩዌት የቴሌቭዥን እውቅ ዜና አንባቢ ጨቅላዋን እኔ በተደላደለ ሁኔታ ላሳድጋት ይፈቀድልኝ ስትል ጠይቃለች።

አያ አሁን ያለችበት ሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ካሊድ አቲያህ በበኩላቸው በቀን ውስጥ በርካታ ጥሪዎች ከመላው ዓለም እንደሚደርሷቸውና የሁሉም ጥያቄ እኛ እናሳድጋት የሚል እንደሆነ ተናግረዋል።

በዚህ በሰሜን ምዕራብ ሶሪያ፣ ጂንዳይሪስ ከተማ በደረሰው ርዕደ መሬት አሁንም በርካታ ሕንጻዎች ፈራርሰው ሰዎችን ለማዳን ጥረቱ ቀጥሏል። መሐመድ አልአድናን የተባለ ጋዜጠኛ ለቢቢሲ እንደተናገረው አሁንም በሕይወት የሚኖሩ በርካታ ቤተሰቦች ከፍርስራሹ ሥር እንዳሉ ስለታወቀ እነሱን ለማዳን ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ነው።

# መጋቢ አዕምሮ

# በራስ መተማመንን እንዴት መገንባት ይቻላል?

አስናቀ ፀጋዬ

በራስ መተማመን ከፍም ዝቅም ይላል። ከፍ ባለ ጊዜ ሰዎች ለራሳቸው ያላቸው ግምትና ግንዛቤ ይጨምራል። ለራሳቸው የሚሰጡት ዋጋም ከፍ ያለ ነው። በሌሎች ሰዎች ዘንድ የሚሰጣቸው ቦታና ከበሬታም ያዛኑ ያህል ያድጋል። ያለማንም ተፅእኖና ጥገኝነት ስራቸውን በብቃት ያከናውናሉ፤ ስኬታማም ናቸው።

ይሁንና በራስ መተማመን ዝቅ ሲል ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ተቃራኒ ይሆናሉ። በራስ መተማመናቸው የወረደ ሰዎች በዚህ ምድር ላይ ምንም ነገር ማሳካት እንደማይችሉ ይሰማቸዋል። ዓለም ክፉ ትመስላቸዋለች። ሁሌም በራሳቸው ላይ ክፉ ነገር የሚደርስ ይመስላቸዋል። እጅና እግራቸው የታሰረ ፣ ምንም ነገር ማድረግ የማይችሉ ይመስላቸዋል።

በራስ መተማመናቸው የወረደ ሰዎች ሁሌም ቢሆን ስለራሳቸው ጥሩ ጥሩውን ሳይሆን መጥፎውን ብቻ ነው የሚናገሩት። በተደጋጋሚ «እኔ እኮ ደደብ ነኝ፣ አልረባም፣ አልችልም፣ ከሰው ያነስኩ ነኝ» ይላሉ። በራሳቸው ላይ የሚቀልዱት ቀልድ እራሱ አሉታዊና ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርግ ነው። በተለይ ደግሞ መጥፎ ነገር ካጋጠማቸው ሁሌም ራሳቸውን ይወቅሳሉ። ራሳቸውን ጥፋተኛ አድርገው ይቆጥራሉ። ሌሎች ሰዎች ከእነርሱ የተሻለ ነገር ማድረግ የሚችሉና የተሻለ ውሳኔ መወሰን የሚችሉም የመስላቸዋል።

እነርሱ የሌላቸው ነገር ሁሉ ሌሎች ሰዎች ያላቸው ይመስላቸዋል። ለእነርሱ ደስታ፣ ሳቅ ወይም መዝናናት የሚገባቸው አይመስላቸውም። ሁሌም እንደተቆለፉና ዝግት እንዳሉ ነው። ጭምትም ናቸው። ጥሩ ነገር ሲያደርጉና በሕይወታቸው አንድ ነገር ሲያሳኩ እንኳን ራሳቸውን አያሞግሱም። «ጀግና ነኝ፤ ጎበዝ ነኝ፤ አደረኩት፤ አሳካሁት» አይሉም። የሆነ ነገር ሆኖ ነው እንጂ እኔ እንዲህ አድርጌ አይደለም የተሳካልኝ ነው የሚሉት። የሚገባቸውን ክብርና ውዳሴ ለራሳቸው አይሰጡም። ይህም የመጀመሪያው በራስ ያለመተማመን ስሜት ነው።

በሁለተኛው ደረጃ ደግሞ በራስ መተማመናቸው የወረደ ሰዎች ራሳቸውን አያከብሩም። በማንነታቸውና ራሳቸውን በመሆናቸው ብቻ ፍቅር የሚገባቸው አይመስላቸውም። ሁሌም ቢሆን ደፋ ቀና የሚሉት ሰዎችን ለማስደሰት እንጂ ራሳቸውን ለማስደሰት አይደለም። የራሳቸውን ፍላጎት ትተው የሌሎችን ሰዎች ፍላጎት ለማሟላት ይታትራሉ። ሌሎች እንዲያንቋሽሿቸው፣ እንዲሰድቧቸው መረጋገጫያና መረመማመጃያ እንዲያደርጓቸው ይፈቅዳሉ።

ማድረግ የማይፈልጉትን ነገር ለሰዎች ሲሉ በይሉንታ ያደርጋሉ። የራሳቸው ወሰን የላቸውም። አይሆንም፣ አልፈልግም አያውቁም። የክብር፣ የመወደድ፣ የመፈቀር መብት ያላቸው አይመስላቸውም። በዚህም የተነሳ ግብስብሱን ሁሉ ይቀበላሉ። የሚስፈልጋቸውን ነገር አይመርጡም። ይህን ሁሉ ደግሞ የሚሰራው በጭንቅላታቸው ውስጥ ያለው አቋም ነው።

ሰዎች በየትኛውም የኑሮ ሁኔታ ላይ ቢሆኑ፤ ገቢያቸው አነሰም በዛ፣ ቆሸሹም ፀዱ፣ ከፍ አሉም ዝቅ አሉ፣ ስራ ኖራቸውም አልኖራቸው ፍቅርና ክብር ይገባቸዋል። ከማንም አያንሱም። እንዲያም ሆኖ ግን በራስ አለመተማመን ችግር እዛም እዚም ጎልቶ ይታያል። ታዲያ በራስ አለመተማመን ችግር እንዴት ሊመጣ ይችላል? የብዙዎች ጥያቄ ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ 90 ከመቶ የሚሆነውን በራስ አለመተማመን ችግር የሚመጣው ከአስተዳደግ ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ ባህልና አስተዳደጋችን ራሳችንን እንድንወድ፣ እንድናከብር፣ ጠንካራ እንድንሆን ሳይሆን እንድንፈራ፣ እንድንሸማቀቅ፣ እንድን
ሽቆጠቆጥና ሰው ምን ይለኛል ብለን አንገታችንን ደፍተን እንድንኖር ነው የሚያደርገን።

ለአብነት ሰዎች በልጅነት ጊዚያቸው በቤት ውስጥ በጣም የሚገረፉ ከሆነ፣ የሚሰደቡ ከሆነ፣ ጥሩ ነገር ሲያደርጉ የማይበረታቱና የማይታዩ ከሆነ፣ ትንሽ ሲያጠፉ ጓደኛውም ጎረቤቱም ተሰብስቦ በመደብደብ፣ በመስደብና፣ በመቅጣት፣ በማንቋሸሽ የሚረባረብ ከሆነ፣ አሳዳጊዎች ፍቅር የማይሰጡ ከሆነ፣ እንደው አናግረዋችሁም ከሆነ ያናገሩበት መንገድ የሚያጥላላና የሚያንቋሽሽ ከነበረ፣ ከሰው ጋር የሚያወዳድሯችሁ ከነበረ፣ እንደምታስጠሉና እንደማትረቡ ነግረዋችሁ ከነበረ ፣ ደካማ፣ ደነዝ ወይም የማትረቡና በራሳችሁ መቆም እንደማትችሉ እየተነገራችሁ አድጋችሁ ከነበረ እያደጉና ነብስ እያወቁ ሲመጡ በራስ መተማመናቸው እየወረደ ይመጣል።

> **ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ 90 ከመቶ የሚሆነውን በራስ አለመተማመን ችግር የሚመጣው ከአስተዳደግ ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ ባህልና አስተዳደጋችን ራሳችንን እንድንወድ፣ እንድናከብር፣ ጠንካራ እንድንሆን ሳይሆን እንድንፈራ፣ እንድንሸማቀቅ፣ እንድን ሽቆጠቆጥና ሰው ምን ይለኛል ብለን አንገታችንን ደፍተን እንድንኖር ነው የሚያደርገን**

በተመሳሳይ በትምህርት ቤት ውስጥም ታዳጊዎች መምህራኖቻቸው አልያም የክፍል ጓደኞቻውና ማህረሰቡም ጭምር የሚሳለቁባቸው፣ የሚሰድቧቸው፣ የሚያንቋሽሿቸው ከነበረ፣ የሚያዋርዷቸው ከነበረ፣ መደፈር ወይም ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸው ከነበረ፣ በትምህርት ጎበዝና በቶሎ የማይቀበሉ ብሎም የማይረዱ ከሆነ፣ በማህበረሰቡ በወጣ መስፈርት መሰረት ቆንጆ መስለው የማይታዩ ከነበረ፣ እንደሚያስጠሉና ማንም እንደማይፈልጋቸው ሲነገሩራቸው ከነበረ በቀጣይ ሕይወታቸው በራስ መተማመናቸው እጅጉን ወርዶ ይታያል።

ይህም በራስ መተማመን ዝቅተኛ እንዲሆን የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል። ንግግሮቹ ሰዎች ራሳቸውንና ማነታቸውን እንዲጠሉም ያደርጋሉ።

ዞሮ ዞሮ ግን ዋናው ነጥብ የወረደውን በራስ መተማመን እንዴት መመለስ እንደሚቻል ማወቁ ጠቃሚ ነው። የመጀመሪያው በራስ መተማመንን የመገንቢያ መንገድ ራስን መመርመር ወይም ማወቅ ነው። ለመሆኑ የራሳችሁን ባህሪይ ታውቁታላችሁ? ከላይ ከተጠቀሱት በራስ መተማመን መውረድ ባህሪይ ጋር የሚመሳሰለው የእርስዎ ባህሪ ምንድን ነው? መልስዎ «አዎ!» ከሆነ የእናንተ በራስ መተማመን ወረድ ያለ ነው ማለት ነው። ይህ ማለት ግን የወረደ በራስ መተማመን አላችሁና የዓለም ፍፃሜ ቀርቧል ማለት አይደለም። የእናንተ ጥፋትና ፈልጋችሁ ያመጣችሁት ነገር አይደለም። ካጋጠሟችሁና ከደረሱባችሁ ነገሮች ጋር ተያይዞና ተጠራቅሞ የመጣ ማንነት ነው።

በዚህም ልትኮሩ እንጂ ልታፍሩ አይገባም። ምክንያቱም በራስ የመተማመን አቅማችሁን ለመገንባት የመጀመሪያው መንደርደሪያ ራስን መመርመር ነውና። ማንነትዎን፣ ሕይወትዎንና ግንኙነትዎን የሚያበላሹትን ፀባዮችና ባህሪያት ለይቶ ማየትና ማወቅ ይኖርብዎታል። «ይሄ ችግር አለብኝ» ብሎ ለራስ መንገር ያስፈልጋል።

ሁለተኛው በራስ መተማመንን የመገንቢያ መንገድ ከራስዎ ጋር የሚያደርጉት ንግግር ነው። ይህ ሕይወትዎን የሚያስተካክለው ወይም የሚያበላሸው አንዱ መንገድ ነው። እስቲ ራስዎን እንዴት ነው የሚያናግሩት ? እስቲ መስታዎት ፊት ቆመው ከራስዎ ጋር እንዴት ነው የሚያወሩት? አስጠላለሁ ነው ወይስ አምራለሁ፣ እደብራለሁ ወይስ ደስተኛ ነኝ ነው የሚሉት? ወይም ደግሞ ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ ይጠሉኛል፤ ማንም የሚወደኝ ሰው የለም፤ ነገ ብሞት እንኳን ዞር ብሎ የሚያየኝ ሰው የለም ነው ብለው የሚያስቡት?

እንዲህ የሚያስብቡ ከሆነ ለምንድን ነው እነደዚህ የማስበው፣ ማነው እንደዚህ ያለኝ፣ ማነው እንደዚህ የነገረኝ ብለው ራስዎን ይጠይቁ። እነዚህ ነገሮች ምንአልባት ሰዎች የነገርዎት ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ራስዎ በጭንቅላትዎ የፈጠሯቸው ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ እርስዎ ማድረግ የሚገባዎ ነገር እንዲህ የሚያስበውን ጭንቅላትዎን አንድ በአንድ «ውሸት ነው» እያሉ አንድ በአንድ ፉርሽ ማድረግ ነው። እነዚህን አስተሳሰቦች ካፈረሱ በኋላ ደግሞ አዲስና እውነት በሆኑ ነገሮች አእምርዎን መሙላት ያስፈልጋል። ፍቅር እንደሚገባችሁ፣ ውብና መወደድ የምትችሉ ሰው እንደሆኑ ለራስዎ እየደጋገሙ መናገር አለብዎት።

በጭንቅላትዎ ውስጥ ያለው የራስዎ ድምፅ ከየትኛውም ድምፅ በላይ ይጮኻል። ከማንም ሰው በላይ ደግሞ ከራሳችን ጋር ነው ቀኑን ሙሉ የምናወራው። እርስዎም እንደዚሁ። ያ በአእምሮዎ ውስጥ ያለው ድምፅ ራስዎን እንዲጠሉና ራስዎን የበታች እንዲሆኑ የሚያደርጉ ከሆነ አይተርፉም። ሌሎች ሰዎች ከውጪ መጥተው ሲናገርዎት በወረደ የራስ መተማመንዎ ላይ ሌላ መወርድ ያመጣብዎታል። ነገር ግን በውስጥዎ ጥሩ ነገር ካለ፣ ሁሌም ለራስዎ የሚነግሩት ነገር ጥሩ ከሆነ፣ «እኔ ፍቅር ነኝ፣ እኔ ጥሩ ነኝ፣ ለእኔ ጥሩ ነገር ሁሉ ይገባኛል ካሉ ሰዎች የሚሉኝ ነገር ሁሉ እኔ አይደለሁም» ብለው ለራስዎ የሚነግሩ ከሆነ ከውጭ ያለው ጫጫታው ወደ አእምሮዎ አይገባም። ነጥሮ ነው የሚመለሰው። ምክንያቱም ከራሳችሁ ጋር አስቀድማችሁ ተስማምታችኋልና።

ሶስተኛው በራስ መተማመንን የመገንባት መንገድ ሲነገርዎ «ኡፍፍፍ...» ሊሉ ይችላሉ። ነገር ግን ሕይወትዎንና ማንነትዎን የመለወጥ ሃይል ያለው መንገድ ነው። እሱም አሁን ያለዎትንና ተፈጥሮ የሰጠዎትን ነገር ሁሉ አምኖና ወዶ መቀበል ነው። ሁልጊዜ ራስዎን በመስደብና በማዋረድ ፋንታ ሁሌም ያለዎትንና የሚወዱትን ነገር ሁሉ ያድንቁ። በሕይወትዎ ሊቀይሯቸው የማይችሉትን ነገሮች ደስተኛ ሊሆኑባቸው ይገባል። ሁሉም ሰው አንድ ነገሩን ሊወድ ይችላል። ምንአልባት ፀጉሩን፣ አይኑን፣ ከንፈሩን፣ አፍንጫውን፣ ጥርሱን፣ ቀለሙን አልያም የሰውነት አቋሙን። ደግነታችሁን፣ አነጋገራችሁን፣ ድምፃችሁን፣ ፍቅር ሰጪነታችሁን፣ አሳቢነታችሁን፣ ታማኝነታችሁን ልትወዱ ትችላላችሁ። ዞሮ ዞሮ ግን ሁሉም ሰው ቢያንስ ስለራሱ አንድ የሚወደው ነገር አለ።

እነዛ በሚወዷቸው ነገሮች ላይ ሲያተኩሩ የማይወዷቸው ነገሮች ከኋላ መደብዘዝ ይጀምራሉ። ነገር ግን አይ ይሄ ነገር ሕይወቴን እያበላሸ ነው፣ ራሴን እንድጠላ እያደረገኝ ነው ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ፤ ለምሳሌ ከመጠን በላይ ወፍራም ከሆኑና እነዚህን መሰል ችግር ቢጋጥምዎ ለራስዎ ደስታና ጤና ሲሉ መቀየር ይችላሉ። ነገር ግን ደግሞ አጭር ስለሆኑ ፈጣሪ ሆይ ለምን አጭር አደረከኝ ብለው ማማረር የለብዎትም። እጥረትዎን ውበት አድርጉት። በራስ መተማመን ሲጨመርበት ሁሉም ነገር ያምራል። መቀየር የማይችሏቸውን ነገሮች አምነው ሲቀበሏቸው በራስ መተማመንዎ ከፍ ይላል ሰዎችም እርስዎን የሚያዩበት መንገድ ይቀየራል።

አራተኛውና የመጨረሻው በራስ መተማመንን የመገንቢያ ዘዴ ለሕይወት ሃላፊነት መውሰድ ነው። ለሕይወት ሃላፊነት መውሰድ የብዙ ሰው ችግር ነው። በርካታ ሰዎች በሕይወታቸው ለሚፈጠርባቸው ክስተት በአብዛኛውን ሃላፊነት አይወስዱም። ሁሌም ሕይወት ለእርስዎ ጠማማ እንደሆነች የሚያስቡና አይሳካልኝም የሚሉ ከሆነ ለተፈጠረው ነገር ወይም ለውድቀትዎ «የኔ አስተዋፅኦ ምንድን ነው? ብለው ራስዎን ይመርምሩ።

ሁሌም «እኔ እኮ የሰው መጫወቻ ሆንኩ፣ ጥሩ ሰው ስለሆንኩ ሰዎች መጠቀሚያ አደረጉኝ» ብለው የሚያለቃቅሱ ከሆነ የሰዎች መጠቀሚያ የሆኑት እርስዎ ሁሉንም የሚጠቅሙና የሚረዱ ስለሆኑ ሳይሆኑ ለሰዎች በሰዎች ለመወደድ ካላችሁ ከፍተኛ ፍላጎትና ፍቅር አንፃር ነው። በሰዎች መወደድን የሕይወትዎ ትልቁ ስኬት ስላደረጉት ነው። ለሰዎች ምንጣፍ ሆነው ለራስዎ ዘብ የማይቆሙ ከሆነ፣ ሲጠርዎት አቤት ሲልክዎት ወዴት የሚሉ ከሆነ በርግጥም የሰዎች መጠቀሚያ ይሆናሉ።

ነገር ግን ለአንድ ደቂቃ ቆም ብለው «ይህም ያም ለምንድን ነው መጠቀሚያ የሚያደርገኝ? ነው ወይስ ችግሩ እኔ ጋር ነው?» ብለው ቢያዩ ለራስዎ ዘብ እንደማትቆሙ ፤ ራስዎን እንደማያስከብሩና ራስዎ ለራስዎ ዘብ መቆም እንዳለብዎ ይገባዎታል። ጥፋትዎ የቱጋር እንደሆነ ያዩታል። ያ ነው ለራስ ሃላፊነት መውሰድ ማለት። ለሚፈጠርብዎ መጥፎ ነገር በአብዛኛው የእርስዎም አስተዋፅኦ አለበት። በተጠቂነትና በተበዳይነት ስሜት ውስጥ መቆዘም ሳይሆን «አሃ ለካ እኔም ጥፋት አለብኝ፣ እኔም የችግሩ ተባባሪ ነበርኩ» ብለው ወደ ራስዎ ማየት ያስፈልጋል።

ለችግሩ ወይም ለደረሰው ጥፋት የእርስዎም እጅ እንዳለበት ሲያምኑ ከራስዎ ጋር በደምብ ይተዋወቃሉ። በቀጣዩ ጊዜም ጥፋቱን አይደግሙትም። ይህም በራስ መተማመንዎን ያጎለብተዋል። እንደዚህ አይነት የሚያሳምም ግልፅነትና ተጠያቂነት ከእርስዎ ጋር ያስታርቅዎታል፤ ያዋድድዎታል። እንዲህ አይነት አስተሳሰብ ደግሞ በራስ መተማመንዎን ጣራ ያስነካዋል።

ከዚህ በተረፈ ሁሌም ቢሆን ከራስዎ ጋር ጊዜ ያሳልፉ። ከራስዎ ጋር ያለውን ግንኙነት ይጨምሩ። ከራስዎ ጋር ይበልጥ ይተዋወቁ። የሚጠቅምዎትን ሃሳቦች ሁሉ በወረቀት ላይ ያስፍሩ። ደጋግመው ያንብቧቸው፤ ይጠቀሙባቸው። ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ሁሉ ለራስዎ ያድርጉ።



ኢኮኖሚ

# ስኬት

## የተቋቋመበትን አላማ እያሳካ ያለ አምራች ድርጅት

**ፍሬሕይወት አወቀ**





በሁሉም ዘርፍ የተጀመረውን አገራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን አምራች ኢንዱስትሪዎች ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ይታመናል። መንግስት አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታማነታቸውን እንዲጨምሩ፣ እንዲስፋፉ፣ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ወደ ዘርፉን እንዲቀላቀሉ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥረው፣ ድጋፍና ክትትል የሚያደርገውም ለእዚህ ነው።

በዘርፉ የተሰማሩ በርካታ የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ውጤት እያስመዘገቡ ይገኛሉ። አምራች ኢንዱስትሪዎቹ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ተኪ ምርቶችንና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ።

በአገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች ከተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከቻይና ባለሃብቶች ጋር ያቋቋመው "ደብረ ብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅት" አንዱ ነው። ከድርጅቱ ያገኘነው መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ በመነሳት ትርጉም ያለው ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል፤ በተለይ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ተኪ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን በማዳን እንዲሁም ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ይህን መሰረት በማድረግ የድርጅቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና የስኬት ጉዞ እንዲሁም የወደፊት ዕቅዱን በዛሬው የስኬት አምዳችሁ ልናስቃኛችሁ ወደናል።

በ2006 ዓ.ም ተቋቁሞ በ2007 ዓ.ም ወደ ማምረት ስራ የገባው ይህ ድርጅት፣ በአገሪቱ ኢኮኖሚ በተለይም የውጭ ምንዛሬን በማዳን ረገድ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል። በ2008 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ምርቶቹን ለሽያጭ ማቅረብ የጀመረው ደብረ ብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅት፣ በዋናነት የሚያመርተው ጣውላ መሆኑን የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ ባዩ ደጀኔ ይናገራሉ፡፡

ስራ አስኪያጁ እንደሚያስረዱት፤ በደብረ ብርሃን ከተማ የሚገኘው "ደብረ ብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅት" በአማራ ደን ኢንተርፕራይዝ 51 በመቶ እንዲሁም በቻይና የግል ባለሃብቶች 49 በመቶ ድርሻ የተመሰረተ ነው። በጥቅሉ ድርጅቱ በ80 ሚሊዮን ብር መነሻ ካፒታል የተቋቋመ የአማራ ክልላዊ መንግሥት የልማት ድርጅት ነው።

በክልሉ በርካታ የባህር ዛፍ ቁም ደን መኖሩን የጠቀሱት አቶ ባዩ፤ ቀደም ሲል ይህ የቁም ደን ለቤት መስሪያነትና ለማገዶነት ብቻ ያገለግል እንደነበር ያስታውሳሉ፤ ደኑ በአማራ ክልል ደን ኢንተርፕራይዝ ስር መተዳደር ከጀመረ በኋላ ለፋብሪካው ግብዓትነት እንዲውል ማድረግ ተችሏል ነው ያሉት።

እሳቸው እንዳሉት፤ የክልሉ መንግሥት ዕውቀትና ቴክኖሎጂን ከፍላጎት ጋር አጣምረው ከያዙ አገራት ጋር በመሆን ፋብሪካውን ለመቋቋም ሲወጥን በቀዳሚነት ያገኘው ቻይናውያን ባለሃብቶችን ነው። በዚህ ምክንያትም ከክልሉ ጋር ለመስራት ፍላጎት ካሳዩ ባለሃብቶች ጋር በመሆን ወደ ሥራ መግባት ችሏል፡፡

ድርጅቱ በዋናነት ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ጣውላ እያመረተ ይገኛል። በአካባቢው የሚገኘውን የቁም ደን ወይም ባህር ዛፍ በግብዓት የሚጠቀመው የደብረ ብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ ለኮንስትራክሽን እና ለፈርኒቸር አገልግሎት የሚውሉ ጥራት ያላቸውን የጣውላ ምርቶች ያመርታል፡፡

የድርጅቱን ምርቶች ለማምረት ከባህር ዛፍ በተጨማሪ ኬሚካል አስፈላጊ እንደሆነ የገለጹት አቶ ባዩ፤ ኬሚካሉ የሚመጣው ከውጭ አገር እንደሆነ ነው የተናገሩት። ጣውላውን ለማምረት በመጀመሪያ ዜኒር የተባለው ምርት ከባህር ዛፍ ይመረታል። ኬሚካሎቹን ደግሞ ከቻይና፣ ከኢንዶኔዥያ፣ ከግብጽና ከሳውዳረቢያ በማስመጣት ለኮንስትክሽን እና ለፈርኒቸር ምርት በዋነኛነት ግብዓት የሆነውን የጣውላ ምርት በማምረት ለገበያ ያቀርባል፡፡

ድርጅቱ ወደ ማምረት ስራ ከገባበት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም 262 ሺ 624 ነጥብ 93 ቁም ደን ወይም ባህር ዛፍ ገዝቶ ወደ ፋብሪካው አስገብቷል። በዚህም 104 ሺ 209 ኪዩብ ዜኒር ወይም ስስ ጣውላ ማምረት ችሏል። ይህንኑ ዜኒር ወይም ስስ ጣውላ በመጠቀም ደግሞ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ለኮንስትራክሽንና ለፈርኒቸር ግብዓት መሆን የሚችሉ ንብርብር ጣውላዎችን አምርቷል። ይህንኑ ጣውላ ለገበያ በማዋልም 864 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ሽያጭ በማከናወን 193 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር የተጣራ ትርፍ ማግኘት ችሏል።

በ80 ሚሊዮን ብር መነሻ ካፒታል የተቋቋመው ይህ ድርጅት፣ ገቢ በማመንጨት ውጤታማ እየሆነ መጥቷል፤ በአሁኑ ወቅትም ድርጅቱን ያቋቋሙት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና ቻይናውያን ባለሃብቶች የትርፍ ክፍፍል በማድረግ ድርሻቸውን መውሰድ እንደቻሉ አቶ ባዩ ተናግረዋል። ካፒታሉም አሁን ከ200 ሚሊዮን ብር በላይ የደረሰ ሲሆን፤ በየዓመቱም የሚገኘውን የትርፍ ትርፍም የክልሉ መንግሥትና ቻይናውያኑ እየተከፋፈሉ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እያሳካ መሆኑን የተናገሩት አቶ ባዩ፤ በቀዳሚነት ለአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ ዕድል በመፍጠር 361 የሚደርሱ ዜጎችን በሥራ ዕድሉ ተጠቃሚ አድርጓል። በሁለተኛ ደረጃ ዕውቀትና ቴክኖሎጂ እንዲሸጋገር በማድረግ ሙሉ ለሙሉ በኢትዮጵያውያን እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በመሆኑም የዕውቀት ሽግግር ማድረግ ተችሏል። የድርጅቱ ሌላኛው ዓላማ የውጭ ምንዛሪን ማዳን በመሆኑ እስካሁን ባለው ሂደት ከ25 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪን ማዳን መቻሉንም አቶ ባዩ አስረድተዋል፡፡

ለኮንስትራክሽን እና ለፈርኒቸር አገልግሎት በስፋት የሚውለው ክላውድ ወይም የተነባበረ ጣውላ ከውጭ ይመጣ እንደነበር ያነሱት አቶ ባዩ፤ የደብረ ብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ በአገር ውስጥ መቋቋሙ ይህን ምርት በሀገር ውስጥ በማምረት በኩል አበርክቶው የጎላ ነው ብለዋል። መሰል ድርጅቶችም ምርቱን ማምረት በመጀመራቸው ከውጭ ይገባ የነበረውን በማስቀረት የውጭ ምንዛሪ ማዳን በመቻሉ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ማበርከት እየተቻለ መሆኑን ነው ያብራሩት። በቀጣይም ይህንኑ አጠናክሮ በመቀጠል ከውጭ የሚገባውን የጣውላ ምርት ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ የመተካት ዕቅድ እንዳለም ይጠቁማሉ፡፡

በአገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ በተለይም ለምርቱ ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሪ በመቀነስ ረገድ የድርሻውን እየተወጣ ያለው የደብረ ብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ፣ ታማኝ ግብር ከፋይ እንደሆነም ነው የጠቀሱት። በዚህም ላለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት ተሸላሚ መሆን መቻሉን አቶ ባዩ ተናግረዋል።

ማህበራዊ ኃላፊነቱን በመወጣት ረገድም የጣውላ ምርት በሚመረትበት ወቅት በርካታ ተረፈ ምርቶች የሚገኙበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህንኑ ተረፈ ምርት በአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ለተደራጁ ወጣቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል ይላሉ። 2000 የሚጠጉ አቅመ ደካማ እናቶች ተረፈ ምርቱን በነጻ እንዲጠቀሙ በማድረግ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሆነ አቶ ባዩ አጫውተውናል።

የአማራ ደን ኢንተርፕራይዝ አንዱ ተልዕኮ ደንን ማልማት እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ባዩ፤ ኢንተርፕራይዙ የተለያዩ ችግኝ ጣቢያዎችና የማልሚያ ቦታዎች እንዳሉት እና የአካባቢውን ማህበረሰብ ጭምር በችግኝ ልማት እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

በደን ልማት ሰፊ ተሳትፎ ያለው የአማራ ደን ኢንተርፕራዝ በክልሉ መንግሥትና በቻይናውያን ባለሃብቶች ለተቋቋመው ድርጅት ደንበኛ በመሆን ቁም ደኑን የአካባቢውን ዋጋ መሰረት በማድረግ ያቀርባል። ፋብሪካው ከሚያገኘው ትርፍ ደግሞ የትርፍ ትርፍ ተከፋይ በመሆን ተጠቃሚ እየሆነ ነው፡፡

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የደን ልማቱን አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ እንደሆነ የገለጹት አቶ ባዩ፤ ለዚህም ክልሉ በርካታ ሥራዎችን እንደሚሰራም ይገልጻሉ። ድርጅቱ የሚጠቀመው ባህር ዛፍን ብቻ እንደመሆኑ ለባህር ዛፍ ደን ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል ይላሉ። ለአብነትም ባህር ዛፉ ሲቆረጥ በባለሙያ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ነው። ባህር ዛፍ ሲቆረጥ ሌላ ቅርንጫፍ በማውጣት የማበብ ዕድሉ ሰፊ በመሆኑም የደን መመናመን አያስከትልም ሲሉ ያብራራሉ።

በዓመት ከሁለት መቶ ሺ ጣውላ በላይ እያመረተ የሚገኘው ድርጅቱ፣ በቀጣይም በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ በመሆን ጥራቱን የጠበቀ ጣውላ በማምረት ወደ ውጭ ገበያ የመላክ ዕቅድ አለው። ይህም በአገሪቷ ያለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በማቃለል በኩል የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ያስችለዋል።

ምርቱን በስፋት ለማምረት ባህር ዛፍ ዋናው ግብዓት መሆኑን ጠቅሰው፣ ከውጭ የሚገቡ የተለያዩ ኬሚካሎች እንዳሉም ነው የሚናገሩት። እነዚህን ኬሚካሎች በስፋት በማምጣት እንዲሁም መለዋወጫ ማሽኖችን በማስገባት ምርቱን በስፋት በማምረት ከአገር ውስጥ ባለፈ ማስፋት እንደሚቻል አቶ ባዩ ይጠቁማሉ፡፡

በደብረ ብርሃን ከተማ ስድስት ነጥብ ሶስት ሄክታር ስፋት ባለው መሬት ላይ ያረፈው የደብረ ብርሃን ውድ ፕሮሰሲንግ ድርጅት በርካታ ማሽኖችን በውስጡ አቅፎ ይዟል። ከማሽኖቹ መካከልም ልጥና ቅርፊቱን ከሚለይ ከግንድ መላጫ ጀምሮ እስከ ፕላይድ መቁረጫ ድረስ ያሉ በጥቅሉ ከ30 የሚልቁ የተለያዩ ማሽኖች አሉ።

ድርጅቱ ምርቶቹን በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ እንደሚያደርግና ሰፊ ገበያ ያለው ግን በአዲስ አበባ ከተማ መሆኑን አቶ ባዩ ጠቁመዋል። የተለያዩ ግዙፍ የኮንስትራክሽን ሥራ የሚያካሂዱ ተቋራጮች ማለትም በሪልስቴት ዘርፍ የተሰማሩ ተቋማት ምርቱን በስፋት እንደሚገዙም ነው የተናገሩት። ለአብነትም ሀያት ሪልስቴት በዘንድሮ ዓመት ብቻ 47ሺ ጣውላዎችን ከድርጅቱ መግዛቱን አቶ ባዩ ጠቅሰዋል። ከኮንስትራክሽን ዘርፉ በተጨማሪ ፈርኒቸር አምራቾች ምርቱን በስፋት እንደሚጠቀሙ አስታውቀው፣ ገበያውን በመላው አገሪቱ ተደራሽ ማድረግ እንዲቻል ድርጅቱ በትጋት እየሰራ ይገኛል ይላሉ፡፡

ድርጅቱ ለልዩ ልዩ የግንባታ ሥራዎች እንዲሁም ለፈርኒቸር ምርቶች ሰፊ አገልግሎት የሚሰጠውን ንብርብር ጣውላ በስፋት አምርቶ ተደራሽ ከማድረግ በተጨማሪ የምርቶቹን አይነት የማስፋት ዕቅድ እንዳለውም አቶ ባዩ ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በተረፈ ምርት እና በሌሎች ግብዓቶች የተለያዩ ምርቶችን ማምረት ይቻላል። ለዚህም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ነው ያስረዱት፡፡

ምርቱ ጥራት ያለው በመሆኑ የገበያ ችግር ያለበት ያሉት አቶ ባዩ፤ በጥራት ማምረት በመቻሉ ገበያውን ሰብሮ መግባት እንደቻለና ተፈላጊነቱ ሰፊ እንደሆነ ነው ያብራሩት። በቀጣይም ምርቱን በስፋትና በጥራት በማምረት ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ በመገኘት የውጭ ምንዛሬን ማስቀረት ትልቁ አላማችን ነው የሚሉት አቶ ባዩ፤ የጣውላ ምርቱ በአገር ውስጥ መመረት በመቻሉ በዓመት ከሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት መቻሉን ነው የተናገሩት። ባለፈው ስድስት ወራትም ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬን ማዳን ተችሏል ብለዋል።

በቀጣይም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ጥራት ያለውን ምርት በማምረት ከውጭ የሚገባው የጣውላና ሌሎችም የግንባታ ምርቶችን በአገር ውስጥ የመተካት ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተናገሩት አቶ ባዩ፤ ድርጅቱም ለዚሁ ዝግጁ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የአንጋፋው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል የማስፋፊያ ፕሮጀክት

መላኩ ኤሮሴ

በአዲስ አበባ እምብርት ላይ የሚገኘው የእድሜ ባለጸጋው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ታካሚ ብዛትና ሆስፒታሉ ያለው የአልጋ ብዛት ባለመጣጣሙ ተገልጋዮች የህክምና አገልግሎትን በሚፈልጉት ወቅት እንዳያገኙ አድርጓቸው ቆይቷል። ለዚህም በሆስፒታሉ በተለይም በጨቅላ ህጻናት ክፍል እና ከድንገተኛ ህክምና አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚስታዋለው መጨናነቅ የተገልጋዮች እና የአልጋ አለመጣጣም ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በሆስፒታሉ ውስጥ ባለው የተገልጋይ እና አልጋ አለመጣጣም ምክንያት በአግዳሚ ወንበሮች ሆነው የሚታከሙ ተገልጋዮችን ማየት የተለመደ ነው። በአጠቃላይ አንጋፋው የዘውዲቱ ሆስፒታል ያለበት የአልጋ ጥበት ለዘመኑ የሚመጥን አገልግሎት እንዳይሰጥ ተግዳሮት ሆኖበት ለታካሚዎች የቅሬታ ምንጭ ከመሆኑም ባሻገር ሀኪሞችም ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዳይሰጡ እንቅፋት ሆኖባቸው መገኘቱን ከሆስፒታሉ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ ጌታቸው መንግስት እንደሚሉት፤ ሆስፒታሉ አሁን ያለው ቦታ በጣም የተጣበበ እና የተጨናነቀ በመሆኑ አገልግሎቱን ለሚሰጡ የህክምና ባለሙያዎችም ሆነ ለተገልጋዩ ምቹ አይደለም። በአልጋ እጥረት ምክንያት ለህክምና መስጫ ተብለው ያልተገነቡ ህንጻዎችን ለህክምና አገልግሎት እየተጠቀመም ይገኛል። ለአገልጋዩም ሆነ ለተገልጋይ ምቹ ባይሆንም ባለው ሁኔታም ቢሆን ቢያንስ ታማሚ ድኖ እንዲሄድ አገልግሎቱን እየሰጠ ነው።

ሆስፒታሉ በተለይም በሌሎች ሆስፒታሎች የማይሰጡ አገልግሎቶችን በመስጠት የሚታወቅ ከመሆኑም ባሻገር በከተማዋ ማዕከል ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ለትራንስፖርት ምቹ ነው። ትላልቅ ኩነቶች ለሚካሄድባቸው ለመስቀል አደባባይ እና ለስታዲየም ቅርብ ከመሆኑ፣ ሕዝባዊ በዓላት የሚከበርበት እና ትላልቅ መንግሥታዊ ተቋማት በሚገኙበት አካባቢ የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካቶች በሆስፒታሉ ለመጠቀም ያመቻቸዋል።

የሀገሪቱ ዋና ዋና ኩነቶች የሚካሄዱበት እና የሀገሪቱ ቁልፍ ተቋማት የሚገኙበት አካባቢ የሚገኝ ሆስፒታል እንደመሆኑ የተደራጀ የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት መስጫ እንዲኖረው የሚጠበቅ ቢሆንም በቦታ ጥበት ምክንያት የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት ሲቸገር መቆየቱን የጠቆሙት ምክትል ስራ አስኪያጁ፤ ለዚህም ሆስፒታሉ ካለበት ቦታ አንጻር እጅግ አስፈላጊ የሆነው ድንገተኛ አደጋ አገልግሎት መስጫ ክፍል አለመኖሩን እንደ አንድ ማሳያ አንስተዋል። ከድንገተኛ አደጋ ጋር ተያይዞ የሚታይ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ብቻ እንዳልሆነም ተናግረው፣ በከተማዋ የሚገኙ ሌሎች ሆስፒታሎችም የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት መስጫ እጥረት እንዳለባቸው ይገልጻሉ።

ሆስፒታሉ ያጋጥሙት የነበረውን የተገልጋይ እና አልጋ አለመጣጣም ችግርን ለመቅረፍ፣ አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ እንዲያደርግና ከተማዋን የጤና ቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ የተያዘውን ትልም ለማሳካት የማስፋፊያ ስራ እየተሰራ ነው። የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ ከሶስት ወር በፊት የተጀመረ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ከመሬት በታች የሚሰሩ አብዛኞቹ ስራዎች ተጠናቅቀዋል። የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ የሆስፒታሉን አገልግሎት ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ተስፋ ተጥሎበታል።

የሆስፒታሉ ምክትል ስራ አስኪያጅ እንደሚሉት፤ የአዲሱ ህንጻ ዋና ዓላማውም የድንገተኛ አገልግሎት መስጫ አገልግሎት መስጠት ነው። የህንጻው ሙሉ ቤዝመንቱ ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎት መስጫ የሚውል ይሆናል። ሆስፒታሉ የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት የልህቀት ማዕከል እንዲሆን ይጠበቃል።

የማስፋፊያ ግንባታው ከድንገተኛ አደጋ በተጨማሪ የሆስፒታሉን አቅም ከፍ ያደርገዋል። በአሁኑ ወቅት ሆስፒታሉ ወደ አራት መቶ አልጋዎች ያሉት ሲሆን፣ ይህንን የአልጋ ቁጥር ወደ ስምንት መቶ ከፍ ያደርገዋል፤ በእጥፍ ያሳድገዋል ነው።





የሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክቱ በአንድ ነጥብ አምስት ቢሊየን ብር እየተካሄደ ሲሆን፣ ለሆስፒታሉ 400 ተጨማሪ አልጋዎችን የሚያስገኝም ነው

ሆስፒታሉ የህጻናት ጽኑ ህሙማን ክፍል እንደሌለው ጠቅሰው፣ የህንጻው ግንባታ ሲጠናቀቅ ሆስፒታሉን የህጻናት ጽኑ ህሙማን ክፍል እንዲኖረው ያስችላል ይላሉ። የአዋቂዎች ጽኑ ህሙማን ክፍልም እንደሚኖረው ጠቁመዋል። የእናቶች እና ህጻናት የህክምና አገልግሎቱም እንዲሻሻል ተደርጎ አሁን ቴክኖሎጂው በደረሰበትና ዓለም አቀፍ ደረጃ ማሟላት ያለበት መስፈርት /ስታንዳርድን/ ባሟላ መልኩ ይዋቀራል ብለዋል።

ደረጃውን የጠበቀ የላውንደሪ አገልግሎት መስጫ፣ የጠበቀ የመመገቢያ አዳራሽ የሚኖረውም ይሆናል። ሆስፒታሉ ለሠራተኞች መሰብሰቢያ ሊውል የሚችል አዳራሽ እንደሌለው ጠቅሰው፣ ይህ ህንጻ ሲጠናቀቅ የሆስፒታሉ ሠራተኞች መሰብሰቢያ የሚሆን ትልቅ አዳራሽም ይኖረዋል ያሉት አቶ ጌታቸው፣ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ አሁን ላይ ያለውን የታካሚዎች እንግልት በመቀነስ የህብረተሰብ ጤናን እንደሚታደግ ይታመናል ይላሉ። የአገልግሎት ተደራሽነትን ከማስፋት በተጨማሪ የአገልግሎት ጥራት ላይ ለውጥ ለማምጣት እንደሚረዳና የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት እንደሚያስችልም አብራርተዋል።

የሆስፒታሉን የማስፋፊያ ፕሮጀክት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት በባለቤትነት እያስገነባ ይገኛል። በጽሕፈት ቤቱ የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ተጠሪ እና ተቆጣጣሪ የስነ ሕንጻ ባለሙያ ነጋሽ መሐመድ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ ጽህፈት ቤቱ በከተማዋ ውስጥ እያከናወናቸው ካሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች አንዱ ይህ የማስፋፊያ ግንባታ ነው። የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ ጥቅምት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ነው የተጀመረው። ፕሮጀክቱ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ፕሮጀክቶች አንዱ ነው። ለፕሮጀክቱ 1 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር በጀት የተያዘለት ሲሆን፤ ማስፋፊያው 1 ሺ800 ካሬ ሜትር ላይ የሚያርፍ ነው። ህንጻው፤ ከቤዝመንትና ግራውንድ በላይ ስምንት ወለሎች ይኖሩታል።

ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ አብዛኛው ከመሬት በታች የሚሰሩ ስራዎች ተሰርተዋል። ፊዚካል ግንባታው ከአምስት በመቶ በላይ ተጠናቋል። ቦታውን ለግንባታ የማመቻቸት ስራው ብዙ ጊዜ ፈጅቷል። ወደታች ላለው ግንባታ የሚደረገው ቁፋሮ በሆስፒታሉ ሌሎች ግንባታዎች ላይ ችግር እንዳያስከትል በከፍተኛ ጥንቃቄ የመቁረጥ ስራው ግንባታው ቶሎ እንዳይጀመር ምክንያት ነበር። በተጨማሪም በቦታው ከስር ውሃ የሚፈልቅበት በመሆኑ ውሃውን የማስወገድ ስራ ጊዜ ወስዷል። በቦታው የነበረውን የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር ማንሳትም እንዲሁ ብዙ ጊዜ መጠየቁንም አብራርተዋል።

በአጠቃላይ ቦታውን ለግንባታው አመቺ የማድረግ ሂደት በግንባታው ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን የጠቆሙት የፕሮጀክቱ ተጠሪና ተቆጣጣሪ፣ በኮንትራት ውሉ በቀን 16 ሰዓት በመስራት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ መታቀዱን አስታውቀዋል። ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የዘገየውን ግንባታ ለማካካስ እና በተያዘለት የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ በቀን 24 ሰዓት እየተሰራ ነው ብለዋል።

የማስፋፊያ ፕሮጀክቱን የዮሐንስ ኃይሌ ኮንስትራክሽን ድርጅት በማከናወን ላይ ይገኛል። የሆስፒታሉ ማስፋፊያ ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ማስተዋል ኃይለክርስቶስ እንደሚሉት፤ በ540 ቀን ወይም በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ውስጥ ለማጠናቀቅ እቅድ የተያዘለት ፕሮጀክት ነው። በተያዘለት ጊዜ ለመጨረስ ሌት ቀን እየተሰራ ነው።

ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ብቁ ባለሙያዎችን ወደ ስራ በማስገባት በተያዘለት ጊዜ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ግንባታውን ለመጨረስ እየተሰራ ይገኛል። የሚመለከታቸው አካላትም ድጋፍ እያደረጉ መሆናቸውን ጠቁመው፣ ጥራቱን የጠበቀ ግንባታ ለመገንባት ለግንባታው የሚውሉ ግብዓቶች ላይ ተገቢው ፍተሻ እየተካሄደ ስራ ላይ እየዋለ ነው ብለዋል።

የሲሚንቶ አቅርቦት ችግር ግንባታው እንዳይፋጠን እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን የጠቆሙት ኢንጂነር ማስተዋል፤ የሲሚንቶ እጥረት እየፈጠረ ያለውን እንቅፋት በመቋቋም ግንባታው እየተካሄደ መሆኑን አንስተዋል። በሲሚንቶ እጥረት ምክንያት ኮንክሪት በጣም ውድ በሆነ ዋጋ ሌላ ቦታ ተመርቶ እየመጣ መሆኑን አላስፈላጊ ወጪ ውስጥ እየገባ መሆኑን አንስተው፤ ሲሚንቶ ላይ ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባ ነው የገለጹት።

የሲሚንቶ እጥረት ለፕሮጀክቱ ግንባታ መፋጠን እንቅፋት እየሆነ ነው የሚለውን የኢንጂነር ማስተዋልን ሀሳብ የሚጋሩት የፕሮጀክቱ ተጠሪና ተቆጣጣሪ አርኪቴክት ነጋሽ መሃመድ፣ ችግሩን ለመቅረፍ ግን የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። የሲሚንቶ እጥረት ለመቅረፍ ሜጋ ፕሮጀክቶች የድጋፍ ደብዳቤዎችን ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች በመጻፍ የበኩሉን እየተወጣ መሆኑን ይገልጻሉ። ለሆስፒታሉ ማስፋፊያ ቅድሚያ እንዲሰጠው ለዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ሶስት ጊዜ ደብዳቤዎችን መጻፉን ጠቅሰው፣ ችግሩ እስኪቀረፍ ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል።

በፕሮጀክቱ ሦስት መቶ ለሚሆኑ ጊዜያዊ እና ሁለት መቶ ለሚሆኑ ቋሚ ሠራተኞች የስራ እድል መፈጠሩን የጠቆሙት ኢንጂነር ማስተዋል፤ በድርጅቱ ውስጥ በቋሚነት እና በጊዜያዊነት ተቀጥረው እየሰሩ ያሉ ሠራተኞችን ለማብቃት በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አመላክተዋል። በቀን ሠራተኝነት ተቀጥረው እየሰሩ ያሉ ጊዜያዊ ሠራተኞች ጭምር ባላቸው ዝንባሌ መሰረት የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ፣ ሙያቸውን እንዲያሳድጉ ለወደፊት ራሳቸውን ችለው መስራት የሚችሉ እንዲሆኑ ድርጅቱ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ነው ያስታወቁት።

እንደ ኢንጂነር ማስተዋል ማብራሪያ ፤ የከተማ አስተዳደሩ እና ክፍለ ከተማው ለፕሮጀክቱ ትልቅ ትኩረት ሰጥተው አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረጉ ነው። በቀን ቢያንስ አንድ ጊዜ እየተገናኙ ፕሮጀክቱ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በየጊዜው ስለሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ውይይት እየተካሄደ ማስተካከያ እርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው።

ፕሮጀክቱን የማማከር ስራ እየሰራ ያለው ሲጎር ኮንሰልት አማካሪ ነው። በሲጎር አማካሪ ድርጅት የዘውዲቱ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማናጀር ኢንጂነር ቻፒ ታደሰ እንዳሉት፤ ፕሮጀክቶችን ተቋማት በራሳቸው በሚያስገነቡበት ወቅት በኮንትራክተሩ እና በባለቤት ተቋም መካከል የቅንጅት ችግሮችን ማየት የተለመደ ነው። የቅንጅታዊ አሰራር ችግሮች ለፕሮጀክቶች መጓተት መንስኤ ሲሆኑም ይስተዋላል። የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት በሚያስገነባቸው ፕሮጀክቶች ላይ መሰል ችግሮች አይታዩም።

የዘውዲቱ መታሰቢያ ማስፋፊያን በባለቤትነት እያስገነባ ባለው የትላልቅ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት እና በኮንትራክተሩ በዮሐንስ ኃይሌ ኮንስትራክሽን ድርጅት እንዲሁም በግንባታው ላይ እየተሳተፉ ባሉ አካላት መካከል ጥሩ መናበብ አለ። ይህም በፕሮጀክቱ ግንባታ ላይ የሚስተዋሉ እንቅፋቶችን በአስቸኳይ ለመፍታት እያስቻለ ነው።

ፕሮጀክቱ በከንቲባዋ የቅርብ ክትትል የሚደረግለት ፕሮጀክት መሆኑን የጠቀሰው ቻፒ፤ የሆስፒታሎች ግንባታ ከየትኛውም ፕሮጀክት በላይ ከፍተኛ ጥራት እና ጥንቃቄ የሚሻ መሆኑን አንስቷል። በመሆኑም ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ ከሚደረገው ርብርብ ጎን ለጎን ጥራት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን ገልጿል። ከሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤትና ከኮንትራክተሩ ጋር በቅርበት እየሰራን ነውም ብሏል።

በፕሮጀክቱ የስራ እድል ከተፈጠረላቸው አንዷ የሆነችው ወይዘሪት ገላኔ ደበሳ በፕሮጀክቱ መረጃ ሰብሳቢ በመሆን በማገልገል ላይ ትገኛለች። በ2014 በኢንጂነሪንግ የትምህርት ዘርፍ የተመረቀችው ገላኔ፤ የዘውዲቱ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ስራዋ ነው። የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም በፕሮጀክቱ ውስጥ የተሰሩ ስራዎችን መረጃ በማሰባሰብ በየጊዜው ለኮንትራክተሩ ሪፖርት ታደርጋለች። ከዛ በተጨማሪ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችንም ትለያለች።

ያሰባሰበቻውን መረጃ በሶፍትዌር በመቀየር ለኮንትራክተሩ በሪፖርት መልክ ታቀርባለች። የራሷን ምክረ ሀሳቦችንም ታቀርባለች። በመጀመሪያ ስራዋ በአንጋፋው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ግንባታ ላይ ተሳታፊ በመሆኗ እድለኛ እንደሆነች የምትናገረው ወይዘሪት ገላኔ፣ በቀጣይ ለምትሰራቻው ስራዎች አጋዥ የሆኑ ብዙ ልምዶችን እየቀሰመች መሆኗን ነው የገለጸችው። በትብብር መስራት እንደሚቻልም ትምህርት መቅሰሟን ታብራራለች።

# ርዕሰ አንቀፅ




## ሰላማችንን ልንጠብቀው፤ ልናሳድገውና የነገዎቻችን መሰረት ልናደርገው ይገባል!

ሰላም ለአንድ ሃገርም ሆነ ማህበረሰብ ያለው ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ወሳኝ ነው። ያለ ሰላም ምንም ሊታሰብ፤ ሊደረግ አይችልም። ስለ ነገዎች ሳይሆን ስለሚቀጥሉት ደቂቃዎች እንኳን አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻለው ሰላም በሚፈጥረው አስቻይ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ነው። ይህ እውነታ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን በየዘመኑ ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ ከከፈልነው ተዘርዝሮ የማያልቅ ዋጋ አንጻር ፤ ለሰላም ያለን መሻት ከፍ ያለ ነው። ለዚህም ሁሌም ቢሆን ለሰላም ዋጋ ለመክፈል የተነቃቃ ማኅበራዊ፤ ባህላዊና መንፈሳዊ እሴቶች ባለቤቶች ነን። እንደ ሕዝብ ያሉን የቀደሙት ተቻችሎና ተከባብሮ የመኖር የረጅም ዘመናት ታሪኮቻችንም ለዚህ ህያው ምስክሮች ናቸው።

በየዘመኑ እንደ ሀገር የሚገዳደሩንን ችግሮች ተሻግሮ ለመሄድ እንደ ሕዝብ የተጓዝንባቸው መንገዶች ፣ ትናንቶችን ሳይሆን ነገዎችን ተስፋ አድርገው ፤ በሰላም መሰረት ላይ የተዋቀሩ፤ የሰላምን ትሩፋቶች ተሻግረው መመልከት የቻሉ ናቸው። ይህም እንደ ሕዝብ ያልተገቡ ተጨማሪ ዋጋዎችን እንዳንከፍል አድርጎናል። እንደ ሀገርና ሕዝብም ጸንተን እንድንቆም ረድቶናል።

ዛሬም ቢሆን እንደ ትናንቱ እንደሃገር እና ሕዝብ ጸንተን እንድንቀጥል ዋንኛ አቅም የሚሆነን ይሄው ስለ ሰላም ያለን የጸና መሻት እንደሚሆን ይታመናል። በተለይም ሰለማችንን በብዙ መልኩ የሚፈታተኑና ሰላማችንን የፖለቲካ መቆመሪያ ካርድ አድርገው ለመጠቀም የሚሺ ኃይሎች አደባባዮችን በሞሉበት በዚህ ወቅት ስለ ሰላማችን ዘብ መቆም የሁላችንም ትልቁ ኃላፊነት ነው።

አሁን ያለንበት ወቅትና ወቅቱ ይዞት የመጣውን ሃገራዊ ፈተና አሸንፎ ለመሻገር የቀደሙት አባቶቻችን ተመሳሳይ የታሪክ ክስተቶችን በጽናት ማለፍ የቻሉበትን ማኅበራዊ ፣ ባህላዊና መንፈሳዊ የሰላም እሴቶቻችንን ከጣልንባቸው ስፍራዎች ልናነሳ፤ አቧራቸውን ልናራግፍ ይገባል። በእሴቶቹ ዙሪያ ያለ ያልተስተካከለ አተያይ ከአእምሯችን ልንፍቅ ይገባል።

እስካሁንም ብዙ ዋጋ እያስከፈሉን ያሉት ችግሮቻችን ፤ አሸንፎ መሄድ ያልቻልነው ለዛ የሚሆን ሃገራዊ አቅም ስላጣን ሳይሆን ፤ያለንን አቅም በአግባቡ ተረድተን ፤አቅማችንን የችግሮቻችን ዋነኛ የመፍትሄ አካል ማድረግ ስላልቻልን ነው። ባልተገባ መንገድ እና ምልከታ የጣልናቸውን ሃገራዊ አቅሞቻችንን ጎንበስ ብለን ለማንሳት የዘገየን በመሆናችን ነው።

የወቅቱ ሀገራዊ እውነታ ከሁሉም በላይ የሚጠይቀን በቀደሙት ዘመናት አባቶቻችንን ከከፉ ቀናት ያሻገሯቸውን ማኅበራዊ ፣ ባህላዊና መንፈሳዊ የሰላም እሴቶቻችንን ከጣልንበት አንስተን ካለንበት አስቸጋሪ ወቅት የመሻገሪያ አቅም፤ የቀጣይ ሰላማችን ዋነኛ መሰረት እንድናደርግ ነው። ይህን ለማድረግ አለመፍቀድ በነገዎቻችን ላይ ጽልመት የማልበስ ያህል የሚቆጠር ነው።

ለአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት የማይመች ፤ለዚህ የሚሆን መደላድል የሌለው ነው ፤ ከዛ ይልቅ ለዘመናት ጥላ ሆነው ሲከተሉን ፤በመንገዳችን ሁሉ እንቅፋት እየደረደሩ መውደቃችንን በጽኑ ሲመኙ ለኖሩ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ምኞት ፤ ለሀገራችን በጎ ለማይመኙ የውስጥ ባንዳዎችም ፍላጎት ስኬት የተሻለ እድል የሚፈጥርላቸው ነው ።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር አሁን እንደሃገር መልካቸውን እየቀያየሩ እያጋጠሙን ያሉትን ችግሮች ለዘለቄታው ተሻግረን ፤የምንፈልጋትን ሰላማዊና የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር ከስሜትና ከእልህ ወጥተን በእጃችን ያለውን ሀገራዊ ሰላም ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ልንጠብቀው፤ ልናሳድገውና የነገዎቻችን ተስፋ መሰረት ልናደርገው ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# መስመር የሳተው የኢትዮጵያ ስፖርት ጉዞ

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ ስፖርት በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች እየተጓዘ አሁን ካለበት ይድረስ እንጂ የወደፊት ጉዞው ግን ውሉ እንደጠፋበት ልቃቂት የተዛባ ስለመሆኑ ለስፖርቱ ቅርብ የሆነ ሁሉ ሊታዘበው ይችላል። የወራሪውን ጣሊያን ቆይታ ተከትሎ ብቅ ብቅ ማለት የጀመረው ዘመናዊው ስፖርት በሂደት የስፖርት ማህበራትን በመመስረትና በበላይነት የሚመራውን ተቋም በማደራጀት እንዲሁም ሃገራት በሚወከሉባቸው ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ በመሳተፍ ሊጎለብት ችሏል። በመንግስት አደራጅነትም የልማት ድርጅቶች አምስትና ከዚያ በላይ በሆኑ ስፖርቶች ክለቦችን እንዲያቅፉ በመደረጉ የተሻለ እድገት አሳይቷል።

ይህ ህግ ተሽሮ የስፖርት ፖሊሲ ከተዘጋጀ በኋላ ግን ስፖርት ህዝባዊ ነው ከሚል ብሂል የዘለለ ለውጥ ሳያሳይ እነሆ ሶስት አስርት ዓመታትን ተሻግራል። ፖሊሲው የኢትዮጵያ ስፖርት በመንግስታዊ አካል እየተመራ በህዝባዊ አደረጃጀት እንዲስፋፋ እና ሃገርም የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ አቅጣጫ ቢያስቀምጥም ባለፉት ዓመታት ግን ይህ ተግባራዊ አልሆነም። በመሆኑም አዲስ ብሄራዊ ፍኖተ ካርታ በቅርቡ እንዲዘጋጅ አስገዳጅ ሆኖ ተገኝቷል። ነገር ግን ይህም በትክክል ተግባራዊ ሳይሆንና በየጊዜው እንደሚቀያየረው የስፖርት አመራር ውል ያለው አቅጣጫ ሳይዝ መድረሻውም በውል ሳታወቅ እያዘገመ ይገኛል።

በእርግጥ በግል ጥረታቸውም ሆነ ባላቸው ምቹ ሁኔታ ታግዘው ሃገርን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወክሉ በስኬታቸውም የኢትዮጵያን ሰንደቅ በክብር የሚያውለበልቡ ስፖርተኞች አልጠፉም። ይሁንና ዓለም ከደረሰበት ወቅታዊ ሁኔታ፣ ኢትዮጵያ ካላት ምቹ ሁኔታ እንዲሁም በዘርፉ ከሚገኘው ጥቅም አንጻር የዘርፉ ጉዞ የኋልዮሽ ነው። ለዚህ ደግሞ አብነት መሆን የሚችለው አሁናዊው ሁኔታ ነው::

ከ20 የሚልቁ የስፖርት ማህበራት ባላት ሃገር በተለይ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት የአትሌቲክስ እና እግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ሲሆኑ፤ ሌሎች በውጤት እምብዛም የማይታወቁ ነገር ግን በተሳትፎ ደረጃ ሃገራቸውን በማስተዋወቅ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ስፖርቶች ተሳትፏቸው በእጅጉ ቀንሷል። የተገኙ ተሳትፎዎችም ሃገርን እንደመወከላቸው የሚያግዛቸውና የሚደግፋቸው በማጣታቸው ብዙ ርቀት መጋዝ ሳይችሉ ቀርተዋል።

በአንድ አህጉራዊ ውድድር ላይ ተካፋይ የነበረ የቴኳንዶ ብሄራዊ ቡድን በገንዘብ እጦት ምክንያት ውድድር ከማቋረጥ አልፎ በሄደበት ሃገር ኑሯቸውን ባያደረጉ መልካም ኢትዮጵያዊያን ድጋፍ ወደ ሃገራቸው መመለሳቸውና ጉዳዩም በቀላሉ ተድበስብሶ ማለፉ በቅርቡ ነው የተሰማው። መሰል ሁኔታ እንዳይፈጠርባቸው ስጋት ያደረባቸውና ራሳቸውን ያልቻሉ የስፖርት ማህበራትም ዓለም አቀፍ ተሳትፏቸውን በመግታት በሃገር ውስጥ ውድድሮች ተገድበዋል። በመንግስታዊው አካል በተደጋጋሚ ለዚህ የሚነሳው ምክንያትም ሃገሪቷ ያሳለፈችውን እንዲሁም ያለችበትን አስቸጋሪ ወቅታዊ ሁኔታ ነው። ይህንንም የትኛውም ዜጋ ሊረዳው የሚችል ጉዳይ ቢሆንም ላልተሰሩት የቤት ስራዎች ሰበብ እንጂ አሳማኝ ነጥብ ግን ሊሆን አይችልም::

የኢትዮጵያ ስፖርት ውሉ እንደጠፋበት ልቃቂት አቅጣጫው ተዛብቷል የማለቴ ምክንያትም ይኸው ነው። ስፖርቱን አንድ እርምጃ ወደፊት ለማራመድ ይበጃል የተባለው አቅጣጫ በስፖርት ፍኖተ ካርታው በግልጽ ይቀመጥ እንጂ ተግባራዊ ሳይሆን የአንድ ወጣት እድሜን አስቆጥሯል። አሁንም የስፖርት ማህበራት አደረጃጀት የጠራ እና ከመንግስት ድጎማ የተላቀቀ አይደለም።

ይህንን በኃላፊነት የመምራትና የመቆጣጠር ስራው የመንግስታዊው አካል ሆኖ ሳለ በየዓመቱ በሚበጅትላቸው ጥቂት ገንዘብ ከመወሰን አላላቀቃቸውም፤ ከውጤታማነት አንጻርም ክትትል አይደረግባቸውም። ይህ ሁኔታ ታዲያ አንድ ቡድን ለዓለም አቀፍ ውድድር የገንዘብ ድጋፍ ከተደረገለት በኋላ የሃገርን አንገት የሚያስደፋ ተሳትፎ አድርጎ ቢመለስም እንኳን ተጠያቂ እስከማይሆንበት የሚዘልቅ ነው። ለዚህም በቶኪዮ ኦሊምፒክ የነበረውን ሁኔታ እና ከተሳትፎ መልስ የመንግስታዊው አካል ሚና የአሸማጋይነት እንጂ አጥፊዎችን ተጠያቂ አለማድረጉን ለአብነት ያህል ማንሳት ይቻላል።

ሌላው የሃገሪቷ ስፖርት ወደፊት የሚመራው ኮምፓስ አለመኖሩ በግልጽ አስረጂ የሆነ ጉዳይ በእግር ኳስ ስፖርት እየሆነ ያለው ነው። ተወዳጅ በሆነው ስፖርት ሃገር እስካሁን ድረስ ኪሳራ እንጂ ትርፍ ማግኘት አልቻለችም። ይባስ ብሎ በሃገር ውስጥ ዓለም አቀፍ ውድድር እንዳይካሄድ በመከልከሉ ምክንያት ወዲህ ጅምር ስታዲየሞችን ለመፈጸም ወዲያ ደግሞ ብሄራዊ ቡድኑ ውድድሮች ሲኖሩበት ለውሰት ሜዳዎች የውጪ ምንዛሬ ወጪ መንግስታዊው አካል ተወጥሯል። በዚህም እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ከመሰረተ ልማት ግንባታ ተነጥቆ ለዚህ ዓላማ ይውላል።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የችግሩ መንስኤ ራሱ መንግስታዊው አካል ነው ለማለት ያስደፍራል። ምክንያቱም ህዝባዊ የሆነውን ጉዳይ ለህዝብ ከመተውና አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ በድጎማና ድጋፍ የስፖርት ማህበራትም ሆኑ ክለቦች ራሳቸውን እንዳይችሉ አለማምዶ እዚህ አድርሷቸዋል። በኢትዮጵያ እግር ኳስ በአደራጃጀትም ሆነ በገንዘብ አቅም ትልቅ በሚባለው ፕሪምየር ሊግ ውስጥ «ክለብ» የሚለውን ስያሜ የሚያሟላ ቡድን የለም።

በሊጉ ከሚካፈሉ 16 ክለቦች ራሳቸውን የቻሉት ሁለቱ ሲሆኑ፤ የተቀሩት በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ ናቸው። በመሆኑም የራሳቸው የሆነ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ለመገንባት ቀርቶ የሚተዳደሩትም ከእነዚሁ አካላት በተገኘ ገቢ ነው። አጠቃላይ የእነዚህ ክለቦች ዓመታዊ ወጪ ሲሰላ ደግሞ 1 ቢሊየን ብር ይደርሳል። ይኸውም በአፍሪካ ካሉ ሊጎች በጥቂቶች የተበለጠ መሆኑን በቅርብ የተሰራ አንድ ጥናት አመላክቷል።

«ትበላው የላት ትከናነበው አማራት» ይሉት ዓይነት ብሂል የብሄራዊ ስታዲየምን ግንባታ ለማጠናቀቅ የተጠየቀውን ገንዘብ ቸግሯት ከቻይና መንግስት ጋር ምክክር የተቀመጠች ሃገር፤ ራሳቸውን መቻል ሲገባቸው ከልጅነታቸው አንላቀቅም ላሉ ክለቦች በቢሊየን የሚቆጠር ገንዘብ በየዓመቱ ታወጣለች።

ከስታዲየሞች ጋር በተገናኘ በግል ባለሃብት የተገነባውና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀው ዘመናዊው የወልዲያ ስታዲየም የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን(ካፍ) መስፈርትን ለማሟላት የጎደሉትን ጥቂት ነገሮች አሟልቶ ችግሩን መቅረፍ የሚቻል ቢሆንም ይህ ሳይሆን በሃገሪቷ በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ጉዳት አስተናግዷል። አሁንም ቢሆን ከ1 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ይህ ስታዲየም የደረሱበትን ጉዳቶች በመጠገን እንዲሁም የጎደሉትን መስፈርቶች በማሟላት ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሄ መስጠት ይቻላል::

እንደ ሩጫ ውድድር ግልጽ መነሻ፣ መድረሻ እንዲሁም ርቀቱን የሚሸፍንበት አቅጣጫ ያለው አካል መንገዱን ሊስት አይችልም። ሩጫውን ለመፈጸምም በሚሮጥበት መም ላይ የተቀመጠለትን ምልክት ሲከተል፤ ለአሸናፊነትም ሆነ ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ ደግሞ የራሱን የሩጫ ዘዴ ተግባራዊ ያደርጋል።

ስፖርቱን የሚመራው አካልም ማወዳደር ብቻም ሳይሆን ራሱን የሩጫው አካል በማድረግ ከሌላው ዓለም ጋር ራሱን መመዘን ይኖርበታል። እንደ ኮምፓስ የተቀመጠለትን ፍኖተ ካርታ በመከተልና በማስተግበርም ስፖርት የሃገርን ስም በማስጠራት እንዲሁም አንገብጋቢ ችግሮች ያሉባትን ሃገር በጀትም ከመሻማት ይልቅ የገቢ ምንጭ ማድረግ ይቻላል።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስለአስተያየቶቻችሁ፤ ስለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ጎዳናን የሚያስናፍቁ ቤቶች

ሰላማዊት ውቤ



"ቤት ገመና ነው" ሁሉን ነገራችንን በተለይ ለሌሎች ገልጠን የማናሳየውን ሁሉ የሚሸፍንልን ከትት አድርጎ የሚይዝን ነው። ምንም ሁሉም የሚኖርበት ቤት እንደ አቅም እንደ ኪሱ ጥራቱና ምቾቱ የተለያየ ቢሆንም አንገት አስገብቶ እግር አዘርግቶ ካሳደረ ግን ሁሉ ቤት ተብሎ ነው የሚጠራው:: አንዳንድ ቤቶች ቤት ይባሉ እንጂ የክረምቱን ዝናብ የበጋውን ጸሀይ ለመከላከል እንኳን ሲያቅማሙ ይታያሉ:: እንደዛም ሆኖ ደግሞ በተለይ ለመከራየት የሚጠራባቸው ዋጋ ጆሮን ጭው ያደርጋል::

እንዳንዴ ከቤቶቹ አቅመ ቢስነት የተነሳ ሰዎች ክረምት ላይ የሚዘንበውን ዝናብ ጨምሮ በብርድና ውርጭ የታጀበውን አስፋልት እየመረጡ ያሉበት ሁኔታ እየተበራከተ ነው። "ቤት በመጠኑም ቢሆን ለኑሮ ምቹ መሆን አለበት። ቢያንስ በመኝታ ለምናሳልፈው ሌሊት ምቹ ሊሆን ይገባል" የሚሉት አቶ ፈሩ ሰጤ በቤቶቹ ሁኔታ ከሚማረሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች አንዱ ናቸው። የሥራ ቦታቸውም ሆነ መኖሪያ አድራሻቸው ጎጃም በረንዳ አካባቢ ነው:: ጎጃም በረንዳ ብዙ የሕይወት ገጠመኞች እንደላትም ይናገራሉ:: እሳቸው እንደሚሉት በተለይ መውደቂያ ላጡ ምስኪኖች በጥቂት ብሮች ከተቻለ አልጋ ካልተቻለ ደግሞ ኬሻ በጠረባ ጥሎ ቀን በድካም የዛለ ሰውነትን ማሳረፍ ይቻላል:: 20 ብር ያለው ምስኪን አልጋ ተከራይቶ የበላይ ሆኖ እንቅልፉን ሲለጥጥ ማደር ይችላል:: ያልሆነለት ደግሞ አስር ብሩን ከፍሎ አልጋ ስር ጉዝጓዙን አንጥፎ ጎኑን ማሳረፍ ማንም አይከለክለውም:: ካልሆነም በሰባት ብር (አሁን ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተያይዞ አስር ገብቷል) ኬሻ በጠረባ ጥሎ መልካም ህልም ማለም ማንም አይከለክለውም:: አቶ ፈሩ እንደነገሩን ጎጃም በረንዳ ከመምጣታቸው በፊት አውቶቡስ ተራና ሰባተኛ በርካታ አመታትን አሳልፈዋል:: ከሀገራቸው በፈጣኑ አውቶቡስ መጥተው አዲስ አበባ የቀሩትም በድንገት ነው:: ለመቅረታቸው ዋናው ምክንያት ህክምና ነበር:: ለሕክምና ከገጠር እንደመጡ አውቶቡስ ተራ ሻንጣ አሸክመው የሚያድሩበትን እየፈለጉ ሳሉ የተሸከመላቸውና ‹‹ የሚያድሩበትን መኝታ አሳዮታለሁ› ያላቸው ልጅ ከነሻንጣው የያዙትን ገንዘብ በሙሉ ይዞባቸው ተሰወረ:: ያን ቀን ማታ እንደሞኝ የተሸከመላቸውን ልጅ በመፈለግ ሌሊቱን ሙሉ ማሳለፋቸውን እና ‹‹ያውና ይሄውና በማለት ማሾፊያ መሆናቸውን አይረሱትም:: የኋላ የኋላም አካባቢውንና የጉልበት ሥራውን እየተለማመዱት ሲመጡ ሰባተኛ አካባቢ ላሉ ማደሪያዎች በወር እየከፈሉ ማደር ጀመሩ:: እሳቸው በነዚሁ ቤቶች ጦስ ለወራት ታመው ራሳቸውን በመሳት መንገድ ዳር ወድቀው ያገኟቸው ሰዎች ሆስፒታል ወስደዋቸው መዳናቸውን ይናገራሉ:: ድነው ከሆስፒታል ከወጡ በኋላም ወደ ሥራቸው ተመለሱ ::

በኋላም አሁን ወዳሉበት ጎጃም በረንዳ አካባቢ መምጣታቸውንም ያነሳሉ:: ጎጃም በረንዳ ከመጡ በኋላም የጉልበት ሥራዎች በመሥራት ኑሯቸውን ይገፋሉ:: ሲገኝ ደህና አልጋ ተከራይተው ተመስገን ብለው በጥሩ ህልም የታጀበ ሌሊት ያሳልፋሉ:: ካልሆነም አልጋ ስር ተከራይተው አልጋው ላይ የተከራየውን ሰው እንቅስቃሴና ማንኮራፋት እያዳመጡ ተመስገን ብለው ጎናቸውን ያሳልፋሉ::

ጎጃም በረንዳ ሁሉንም ሰው በእኩልነት ታስተናግዳለች:: በአንድ አልጋ ከላይና ከስር ሆኖ ሳይተዋወቁ አድሮ መለያየትም የጎጃም በረንዳ አንዱ የሕይወት ክፍል ነው:: ሁሉም አልጋም ሆነ አልጋ ስር ተከራይ አረቄም ሆነ ጠጅ ቀማምሶ ስለሚመጣ አንዱ የአንዱን ሁኔታ የሚያስተውልበት ጊዜ የለም:: ሁሉም ‹‹ከመቼ ገብቼ በወደቅኩ›› ነው የሚለው::

አቶ ፈሩና መሰሎቻቸው በእዚህ አካባቢ ላይ ተከራይተው የሚያርፉባቸው ስማቸው ቤት የሚባሉት መጠለያዎች እጅግ የተጠጋጉ ወይም እንደ ልብ የማያንቀሳቅሱ ከመሆናቸውም በላይ ጣሪያውን ተጠግቶ ብዙ ሰዎች እንዲይዝ ታስቦም ፎቅና ምድር ተደርገው እንደሚሰሩም ሳቅ እያፈናቸው ይናገራሉ:: በለስ ቀንቷቸው ቀበሌ የፈቀደላቸው እነዚህኑ ቤቶች እስከ ሦስት ደረጃ የቆርቆሮ ቤቶች ወደላይ ተሰርተው ለኪራይ ያውላሉ:: አፓርታማ የሚል ቅጽል ስም ወጥቶላቸዋል::

አፓርትማንታዎቹ በኮምፐለሳቶ የተካፈሉና እጅግ ጠባቦች ናቸው:: በአንዱ ክፍል የሚሰራው በሌላው ክፍል በቀላሉ ይሰማል:: በስሱ የሚተነፈስ ትንፋሽ እንኳ በቀላሉ ይሰማል ይላሉ አቶ ፈሩ:: ሌላው አደጋ ደግሞ ደረጃ ተብሎ በቁርጥራጭ እንጨቶች የተሰራው መወጣጫ በዘዴ ካልተወጣበት ወደታችኛው ክፍል አምዘግዝጎ ይጥላል:: ተሰናክሎ መቅረት በራሱ ሳይበቃ በተከራዩ ላይ ቁርጥራጭ ቆርቆሮ ወይም እንጨትና ብረቶቹ የመቆራረጥ እንዲሁም በደንብ ባልተመቱት ሚስማሮቹ የመወጋጋት ተጨማሪ አደጋ ይደርሳል:: ከታች የተኛ ሰው ላይ መውደቅም ብዙ ጊዜ እንደሚያጋጥምም ይናገራሉ::

አቶ ፈሩ እንደሚያስረዱትም በቤቶቹ ውስጥ ያለው ፈተና በዚህ አያበቃም ኮርኒሳቸው አጭር በመሆኑ ዝናብ ሲጥል ብርዱ በጋ ሲሆን ሙቀቱ የምድር ገሃነብ ያደርጋቸዋል:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተለያዩ ሰዎች ሲበዙበት ደግሞ መጥፎ ጠረን የመፍጠራቸው ነገር ያየ ብቻ ነው ሊያውቀው የሚችለው::

እነዚህ የአከራዮቻቸው የእለት ጉርስ የተከራዮቻቸው ደግሞ የደከመ ጎን ማሳረፊያ የሆኑ አፓርታማ በቤቶች ለዘመናት በነተቡ አልጋዎቻቸው ይታወቃሉ:: አልጋው በቱሃን፤ በቁንጫና ቅማልና ሌሎች ተባዮች የተመላ ነው:: ጆንያ በለበሰ ወለል ላይ ብርድ ልብስና አንሶላ ጭምር ተጎዝጉዞባቸው የተሟላለት አልጋ ተብለው ይከራያሉ::

አቶ ፈሩ አላበቁም ብዙዎቹ ቤቶች በርና ቁልፍ የላቸውም፡፤ ቤቶቹ በርና ቁልፍ ያላቸውም ቢሆን እንደልብ ለመዝጋትም ሆነ ለመክፈት አይመቹም:: ደግሞ አልጋ ተከራዮቹ የሚመጡበት ሰዓት የተለያየ በመሆኑ ክፍታቸውን መቆየታቸው ግድ ነው:: ብዙዎቹ አልጋዎች ከሌሊቱ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ባሉት ሰዓታት ይከራያሉ:: አልጋዎቹ ተከራይተው እንዳበቁ የቤቶቹ አከራዮች ከውጭ ቆልፈው አስፋልት ላይ ሌሊቱን ያነጋሉ:: እሳት ቢነሳ እንኳን አብሮ ከማረር ውጭ ማምለጫ የለም::

**ቤቶቹ በርና ቁልፍ ያላቸውም ቢሆን እንደልብ ለመዝጋትም ሆነ ለመክፈት አይመቹም:: ደግሞ አልጋ ተከራዮቹ የሚመጡበት ሰዓት የተለያየ በመሆኑ ክፍታቸውን መቆየታቸው ግድ ነው:: ብዙዎቹ አልጋዎች ከሌሊቱ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ባሉት ሰዓታት ይከራያሉ:: አልጋዎቹ ተከራይተው እንዳበቁ የቤቶቹ አከራዮች ከውጭ ቆልፈው አስፋልት ላይ ሌሊቱን ያነጋሉ:: እሳት ቢነሳ እንኳን አብሮ ከማረር ውጭ ማምለጫ የለም**

አልጋዎቻቸውን አከራይተው አስፋልት ላይ ያደሩትም አከራዮች ጠዋት 12 ሰዓት መጥተው በሮቹን በመክፈት ተከራዮቻቸውን ማሰናበት ይጀምራሉ:: ቀኑም በሌላ አዲስ ሕይወት ይቀጥላል::

እዚህም ግን ሌላ ምቾት የሚነሳ ነገር ማጋጠሙ አልቀረም እንቅልፍ ሲጥላቸው ጠብቆ ቀን የለፉበትን ገንዘብ ለመውሰድ የሚሻና እሳቸው ውስጥ አዋቂ ነው የሚሉት ወሮበላ አንገት ለአንገት በመተናነቅ ጭምር ገንዘብ የሚዘርፍም አለ:: ሆኖም ከዘራፊዎቹ ጋር እየተለማመዱ ሲመጡና ቤተኛ መሆናቸው ሲረጋገጥ ዝርፊያው ይቆማል::

‹‹ቀስ በቀስ ወሮበላዎቹ እያወቁንና እየለመዱን ሲመጡ ዘረፋውን ተውን›› የሚሉት አቶ ፈሩ ንፁህ አየር እየተነፈሱ ያለምንም ኮሽታ ተኝተው የሚያድሩ መሆናቸውንም ፈጣሪያቸውን ከማመስገን ጋር ይናገራሉ:: አንዳንድ ጊዜ ከቁንጫው መብዛት፤ ከሰው መተፋፈግ በሚፈጠር መጥፎ ጠረንና ከኪስ ብርበራና ዘረፋ ጋር ተያይዞ ከቤቶቹ ይልቅ ጎዳና አሥር እጅ እንደሚመረጥና የተሻለ መሆኑንም ደጋግመው ያረጋግጣሉ:: ከተከራዩበት አልጋ ቤት ለቀው በጠፍ ጨረቃ አስፋልት ላይ ወጥተው የተኙባቸው አጋጣሚዎችም በርካቶች መሆናቸውን ይናገራሉ::

ስማቸውን መግለፅ ያልፈለጉት ሌላው የአቶ ፈሩ ጓደኛ ከአልጋ ቤቶቹ ይልቅ የጎዳና ሕይወት የተሻለ መሆኑን ያምናሉ:: በተለይ የቁንጫው ነገር በጣም አማራሪ መሆኑን ይናገራሉ:: ‹‹ቁንጫ ቢሉህ ቁንጫ እንዳይመስልህ፤ ደም የጠገበ ነው:: ሲመጠምጥህ ይሉንታ የለውም›› ይላሉ የአልጋ ቤቶችን ሁኔታ የኋሊት እያስታወሱ:: በዚህ ላይ ደግሞ ለአልጋ የሚከፈል ገንዘብ ስታጣና ኬሻ በጠረባ ስትከራይ የበረታ ስቃይ ያጋጥምሃል:: ሰው በዝቶ ወለሉ ሁሉ ሲጨናነቅ በአንድ ጎንህ ብቻ ለመተኛት ትገደዳለህ:: ልገላበጥ ብትል እንኳ ቦታ ስለሌለ እንደ እንጨት ተገጥረህ ታድራለህ:: ልገላበጥ ብትል እንኳን ከጎንህ ከተኙት ጋር ጸብ ከማትረፍ ውጭ ዕድል የለህም:: ስለዚህ እግርህ እንደታጠፈ ጀርባህ መሬት ሳይነካ አድረህ ትነሳለህ::‹‹ቆመህ እንዳደርክ›› ቁጠርው ይላሉ እየተንገፈገፉ::

እሳቸው እንደሚሉትም በአልጋ ቤቶች ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተማረው ጎዳናን ከመረጡ አምስት አመታት አልፏቸዋል:: አሁን ጎዳናን ቤታቸው አድርገው ኑሮን ተያይዘውታል:: ሆኖም ጎዳናም ቢሆን ችግር አያጣውም:: ‹‹.... ክረምት ሲሆን ከባድ ችግር ይደርስብናል:: አሁን ያለንበት ሥፍራ ለጎርፍ ተጋላጭ በመሆኑ ቦታ ክረምት ሲመጣ ቦታ እንደሚቀይሩ ይናገራሉ:: ብርዱም እጅግ ይፈትናቸዋል::

ባለፈው ክረምት ግን ጎርፉ ወደ ሌላ አካባቢ ተቀይሶ የሚሄድበትን ቦይ በመሥራታቸው ተገላግለዋል:: ከላይ የሚመጣውን ዝናብ ለመከላከልም ጥሩ ላስቲክ ወጥረው ነው ያሳለፉት:: ቢሆንም ደንቦች በተደጋጋሚ እያፈረሱባቸው ተቸግረው ቆይተዋል:: አሁን ግን በጋ በመሆኑ ላስቲክም ሆነ ሌላ ነገር ሳይወጥሩ ጎዳና ላይ በነፃነት ያድራሉ:: ለሥራ ወዲያ ወዲህ ሲሯሯጡ ዕቃቸውንም በላስቲክ አስረው እዛው ማደሪያ ቦታቸው ላይ ያኖራሉ:: አሁን በአካባቢው ስለታወቁና በአብዛኞቹም እንደቤተኛ ስለሚታዩ ማንም አይነካባቸውም:: እሳቸውም እንደ አቶ ፈሩ ለረጅም ዓመታት በስቃይ ከኖሩባቸው አስቀያሚ ቤቶች ይሄ ጎዳና እንደሚሻል ያነሳሉ:: ከምንም በላይ ለሚተነፍሱት ንፁህ አየር ደጋግመው ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ::

‹‹በነዛ ቤቶች እኖር በነበርኩበት ጊዜ ልብሴና ቀን ስሸቅል የዋልኩት ገንዘብ በተደጋጋሚ ይሰረቅ ነበር›› ሲሉም ያስታውሳሉ:: እዚህ ግን እሰረቃለሁ የሚል ስጋት በፍፁም የላቸውም፡፤ ለዓመታት በጎዳናው ሲያድሩና በላስቲክ ጠርዘው ትተውት ሲሄዱ አንድም ሰው ንክች አድርጎባቸው አያውቅም::

እንዲህም ሆኖ በአካባቢው ንጽህናው የተጠበቀና ለኑሮ በተነፃፃሪም ቢሆን አመቺ ቤት ቢያገኙ ተከራይተው የመኖር ፍላጎት አላቸው:: ቢሆንም እንዲህ ያሉት የግል ኪራይ ቤቶች ከጎጃም በረንዳ እስከ አውቶቡስ ተራ ባለው አካባቢ ዋጋው የሚቀመስ አይደለም:: የዕለት ሕይወታቸውን የሚገፉበት በመሆኑም ከእዚህ አካባቢ ደግሞ መራቅ አይፈልጉም::

ስለዚህም ለአቶ ፈሩም ሆነ ለጓደኛቸው ጎጃም በረንዳ ሕይወታቸው ናት:: ጎጆ ባይቀልሱም፤ ትዳር ባይመሰርቱም ጎጃም በረንዳ ሁሉንም ሆና ተስተናግዳቸዋለች::

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንና ፌስቡክ ገጾችን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ቅዳሜ ስፖርት

አዲስ ዘመን

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ስደተኛው የሸገር ደርቢ

ቦጋለ አበበ

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ሕዝባዊ መሰረት ካላቸው ጥቂት ክለቦች መካከል አንጋፋው ቅዱስ ጊዮርጊስና ኢትዮጵያ ቡና ግንባር ቀደም ናቸው። ፈረሰኞቹና ቡናማዎቹ የኢትዮጵያ እግር ኳስ የጀርባ አጥንት በመሆን ባለፉት በርካታ ዓመታት ተፅእኗቸው ጎልቶ መውጣት ችሏል። መሰረታቸውን አዲስ አበባ ያደረጉት ሁለቱ የኢትዮጵያ ሃያል ክለቦች ከየትኛውም ክለብ በላይ የደጋፊ ሀብት አላቸው። እነዚህ ውብ ደጋፊዎቻቸውም የመቀመጫቸው አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን እንደ አጠቃላይ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ድምቀት በመሆን የተለየ ክብር ይሰጣቸዋል። ይህ ድምቀታቸው ደግሞ ጎልቶ የሚወጣው በእርስ በእርስ ግንኙነት "ሸገር ደርቢ" ጨዋታ ነው።



ሁለቱን የአንድ ከተማ ተቀናቃኝ ክለቦች የሚያገናኝ ጨዋታ ሁሌም ተጠባቂ ነው። አዲስ አበባም በሁለቱ ታላላቅ ክለቦች ጨዋታ የተለየ ድምቀት ትላበሳለች። ባለፉት ሶስት ዓመታት ግን የሁለቱ ክለቦች በርካታ ውብ ደጋፊዎች በጉጉት የሚጠብቁትን ፍልሚያ በመዲናቸው ካምቦሎጆ ታድመው ለመመልከት አልታደሉም። ቀጣዩን ጨዋታ ጨምሮ የሸገር ደርቢ በስደት ድሬደዋ፣ ሐዋሳ፣ አዳማ ለ3 ጊዜያት የተካሄደ ሲሆን የአሁኑ ለ4ኛ ጊዜ ነው ከከተማቸው ውጭ የሚደረገው።

ዛሬም ታላቁ የሸገር ደርቢ ስደት ላይ ነው። ሁለቱ ክለቦችም ዛሬ ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ላይ በድሬዳዋ ስቴድየም በፕሪምየር ሊጉ ለ45ኛ ጊዜ እርስ በርስ ሲገናኙ ዘንድሮ በሁለቱም ክለብ ደጋፊዎች በኩል የፈዘዘው ደርቢ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

ዛሬ በ12ኛው ሳምንት ተስተካካይ የቤቲንግ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታ የሚገናኙትን ሁለቱን ክለቦች ፍልሚያ ኢንተርናሽናል አልቢትሮች ይመሩታል ተብሎ ይጠበቃል። በዚህም ዋና ዳኛ ኃይለየሱስ ባዘዘው ከረዳቶቹ ትግል ግዛው እና ፋሲካ የኋላሸት እንዲሁን አራተኛ ዳኛው ለሚ ንጉሴ ጋር በመሆን በጋራ ጨዋታውን እንደሚመሩ መረጃዎች ጠቁመዋል።

ሁለቱ ክለቦች በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ላይ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ 44 ጊዜ እርስ በርስ ተገናኝተዋል። በእነዚህ ግንኙነቶችም ቅዱስ ጊዮርጊስ 21 ጊዜ ድል ሲቀናው ቡና ደግሞ 7 ጊዜ አሸንፏል ፤ 16 ጊዜ ደግሞ አቻ ተለያይተዋል።

በ44ቱ የሁለቱ ቡድኖች ግንኙነት በድምሩ 88 ግቦች መረብ ላይ አርፈዋል። 60ውን ግብ በማስቆጠር ፈረሰኞቹ ቀዳሚ ሲሆኑ ቡናማዎቹ ደግሞ 28 ኳሶችን ከመረብ አዋህደዋል።

የወቅቱ የሊጉ ቻምፒዮን የሆኑት ፈረሰኞቹ አምና በተቀናቃኛቸው ላይ የነበራቸው የበላይነት ዘንድሮስ ይቀጥላል? የስፖርት ቤተሰቡ በጉጉት የሚጠብቀው ጉዳይ ነው። ፈረሰኞቹ በአምናው የውድድር ዓመት ቡናማዎቹን በሊጉ በገጠሙባቸው ሁለት ጨዋታዎች አራት ለአንድና አራት ለዜሮ በሆነ ውጤት በማሸነፍ የበላይነት ነበራቸው።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በዘንድሮው የውድድር ዓመት ባለፉት 12 ጨዋታዎች 7ቱን አሸንፎ 4 አቻ ወጥቶ በአንዱ ብቻ ነው የተሸነፈው። ኢትዮጵያ ቡና በአንፃሩ ካባለፉት 12 ጨዋታዎች መካከል ማሸነፍ የቻለው 5ቱን ብቻ ሲሆን፤ በ5ቱ ጨዋታዎች ሽንፈት ገጥሞታል። ቀሪ ሁለት ጨዋታዎችን ደግሞ በአቻ ውጤት ደምድሟል።

በኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ላይ 25 ጊዜ መሳተፍ የቻሉት ፈረሰኞቹ አስራ አምስት ጊዜ የዋንጫ ድል በማሳካት ከሁሉም ከፍ ብሎ የሚነገር ታሪክ አላቸው። ዘንድሮም የፕሪሚየር ሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ ላይ 2ኛ ሆነው ተቀምጠዋል።

ኢትዮጵያ ቡና በፕሪሚየር ሊጉ ሃያ ስድስት ጊዜ በመሳተፍ ከፈረሰኞቹ በአንድ የተሻለ ታሪክ ቢኖራቸውም የፕሪሚየር ሊጉን ድል አንድ ጊዜ ዋንጫ በማንሳት 2003 ላይ ብቻ ነው ማጣጣም የቻሉት። በዘንድሮው የውድድር ዓመትም በሊጉ የደረጃ ሰንጠረዥ ዘጠነኛ ላይ ተቀምጠው ነው የከተማ ተቀናቃኞቻቸውን የሚገጥሙት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
ETHIOPIAN INSTITUTION OF THE OMBUDSMAN
ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
ጋር በመተባበር በየሣምንቱ የሚታተም

# መልካም አስተዳደርን በማስፈን የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

ራስወርቅ ሙሉጌታ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55/15 መሠረት በሕግ የተደነገጉ የዜጎች መብቶችና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን ነው። በዚህም መሰረት በቅርቡ በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት በመንግሥት ለሕዝብ አገልግሎትና ጠቀሜታ የሚገነቡ የግንባታ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ከመልካም አስተዳደር አኳያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ቁጥጥር አካሂዷል። የተካሄደው ቁጥጥር በክልሉ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮና በቤቶች ልማትና የመንግሥት ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ላይ ነው። ለዛሬው ዝግጅታችን በቁጥጥሩ ወቅት የተለዩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች እንዲሁም በቀጣይ እንዲስተካከሉ በተቋሙ የተሰጡትን ግብረ መልሶች እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

በቁጥጥሩ ወቅት የተስተዋሉ ጠንካራ ጎኖች አንደኛ በክልሉ በሚገነቡ ወይም በሚከናወኑ ፕሮጀክት ከዲዛይን ጀምሮ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ጠንካራ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር መኖሩ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃም በክልሉ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የሶስትዮች የውይይት መድረኮች መኖራቸው ነው።

በሌላ በኩል በቁጥጥሩ ወቅት የተለዩ የአሰራር ክፍተቶች የሚከተሉት ሆነው ተገኝተዋል።

- ከግንባታ ፕሮጀክት ጥራት ጋር በተያያዘ የሕንፃ ተቋራጮች በኮንስትራክሽን ላይ የሚቀጥሯቸው በግንባታ ቦታዎች (site) ባለሙያዎች (ሠራተኞች) እንደ ሙያቸው በአግባቡ ሥልጠናና የሙያ ማረጋገጫ ወስዶ የሙያ ፈቃድ ተሰጥቶቸው (certified) ሆኖ ሳይሆን በልምድ የሚሰሩ እና የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ የሌላቸው እንዲሁም በእውቀትና በክህሎት እንዲሁም በሙያ ላይ ተመስረተውና ሕጋዊ ሆነው እየሰሩ ባለመሆናቸው አልፎ አልፎ የጥራት ችግሮች እንዲከሰቱ ምክንያት መሆኑ፣ (አናፂ እና ግንበኛ፣ ብረት ሰራተኞች፣ ኤሌክትሪክ ሠራተኞች፣ ለሳኝ እና ወዘተ)
- አብዛኛው የግንባታ ፕሮጀክቶች የሥራ ተቋራጮች ተቋማዊ በሆነ መንገድ በድርጅት ደረጃ ፈቃድ ወስደው የሚሰሩበት ሥርዓት ቢኖርም ባለሙያዎች ሳይኖራቸው እንደአላቸው አስመስለው በድርጅት እንደሚንቀሳቀሱ አድርገው ፈቃድ የሚያገኙ በመሆናቸው ድርጅታቸውን በአግባቡ ሳያጠናክሩ በግለሰብ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ እና ተቋማዊ በሆነ (እንደ ድርጅት) የተጠናከረ ባለመሆኑ ግለሰቡ ችግር ሲገጥመው ፕሮጀክቱም አብሮ የሚቋረጥበት ሁኔታ መኖሩ፣
- አልፎ አልፎ የግንባታ ፕሮጀክት ባለቤቶች የግንባታ ቦታውን ዝግጁ ሳይደርጉ በቦታው ላይ የተለያዩ ችግሮች እያሉበት እና የመብራት ፖል፣ የውሃ መስመር ፣ ቴሌ፣ መንገድ የመሳሰሉት በአጠቃላይ መሰረተ ልማት ባልተሟላበት ሁኔታ ከሥራ ተቋራጮች ጋር ውል የሚፈራረሙበት ሁኔታ በመኖሩ የግንባታው ሂደት በተፈለገው ጊዜ አለመጠናቀቅና መጓተት ችግሮች መሆናቸው፣
- የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎችን ወይም ሼዶች የክልሉ መንግሥት ሲገነባቸው ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችን አደራጅቶ በተለያዩ መንገዶች ምርቶች እንዲሸጡና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታስቦ የተሰሩ ቢሆንም ለወጣቶች ለመስጠት መሟላት የነበረባቸውን ፋይናንስ እና የተለያዩ መሰረታዊ የሆኑ መንቀሳቀሻ ነገሮች ያላሟሉና ጥናት ተደርጎባቸው የተሰሩ ባለመሆናቸው አማሬሳና ደከር ላይ ያሉ ሼዶች (ማምረቻ ቦታዎች) ተገንብተው ወደ ስራ ያልገቡ እና ለታለመለት ዓላማ ያልዋሉ መሆናቸው፣
- ግንባታ ፕሮክቶች አካባቢ ለሰራተኞች የደህንነት (safety) መጠበቂያ ቁሳቁስ (ጫማ ፣ ጃኬት፣ ሄልሜት የመሳሰሉት) የተሟላላቸው አለመሆን እና ሰራተኞች ደህንነታቸው ጠብቆ በመስራት ላይ ባለመገኘታቸው ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር አለመኖር፣
- ግንባታ ፕሮጀክት ሲቀረፅ ባለቤት መስሪያ ቤቶች ፍላጎታቸውን በሚገባ ለይቶ የሚያስፈልገውን ፍላጎትና በጀት ያማከለ በቂ በጀት (ወጪ) አለመያዝ፣
- በግንባታ ወይም ኮንስትራክሽን ዙሪያ ያሉ ባለድርሻ አካላቶች (ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር፣ ሕንፃ ሹም፣ ፕላንና ልማት ኮሚሽን እና ሌሎች የመሳሰሉት ተቋማት) ቅንጅታዊ አሰራር ማነስ፣

ተቋሙ ከላይ የተዘረዘሩትን ጠንካራ ጎኖችና በአሰራር ወቅት የተለዩ ክፍተቶች መነሻ በማድረግ በቀጣይ እንዲስተካከሉ የሚከተለውን ምክረ ሃሳብ አቅርቧል።

1. ጥራቱን ሙሉ በሙሉ ለማስጠበቅ እውቀት ያለው (Skilled) የሆነ የሳይት ባለሙያ በሙያ መስካቸው ቴክኒክና ሙያ ሰልጥነው ብቃቱ የተረጋገጠ ባለሙያ ማስማራት ይገባል፣ (ለምሳሌ ግንበኛ፣ኤሌክትሪሺያን ፣የብረት ሰራተኛ ፣ አናፂ የመሳሰሉት)
2. ለሥራ ተቋራጮች የሚሰጣቸው ፈቃድ በእውቀትና በሙያ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ከማሽነሪ መርህ ወደ ባለሙያ መርህ መቀየር እንዲሁም ተቋማዊ በሆነ መንገድ ፈቃድ ወስደው የሚሰሩበት ሥርዓት በመዘርጋት የወጡት አዲስ መመሪያዎች በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውሉ በህንፃ ሹምና በሌሎች በሚመለከታቸው አካላቶች ክትትል ቢደረግ፣
3. የክልሉ መንግሥት የማምረቻና የመሸጫ ሼዶች ሲገነባ ስራ አጥ የሆኑ ወጣቶችን አደራጅቶ በተለያዩ መንገዶች በውስጡ ገብተው ምርቶች እንዲሸጡና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ካስፈለገ ፋይናንስ እና መሰረታዊ መንቀሳቀሻ ነገሮች አሟልቶ ወደ ስራ እንዲገቡና ወጣቱን ማህበረሰብ የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፣
4. ለግንባታ ፕሮጀክቶች መዘግየት ቁልፍ ችግሮች የሆኑ ምክንያቶችን በተለይ የግንባታ ባለቤት መስሪያ ቤቶች ለግንባታ የሚፈለጉ ቦታዎች ላይ ወደ ግንባታ ከመገባቱ በፊት የመብራት ፖል፣ የውሃ መስመር ፣ቴሌ ፣ መንገድ የመሳሰሉት ዋና ዋና መሠረተ ልማቶችን አስቀድሞ ቢሟላ የግንባታ ሂደቱን የሚያፋጥን በመሆኑ ትኩረት ቢሰጠው፣
5. በአገር አቀፍ ደረጃ እና ክልሎች በመተባበር በግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ የዋጋ ጥናት ጊዜ ተወስዶ በተከታታይነት በደንብ ዝግጅት በማድረግ በአግባቡ ወደ ስራ የሚገባበት ሥርዓት ቢፈጠር፣
6. ፕሮጀክት ሲቀረፅ የባለቤት ፍላጎት በሚገባ ተለይቶ የሚያስፈልገውን በጀት (ወጪ) እንዲያዝ ማድረግ ያስፈልጋል፣
7. ከፕሮጀክት ቀረፃ ጀምሮ የሚመለከታቸው አካላት (የህንፃ ሹምን) ጨምሮ በቅንጅት ሊሰራ ይገባል።